**የጎልማሶች ሰንበት ትምህርት፡የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መምሪያ**

መደበኛ እትም

# ለመጨረሻው ጊዜ መዘጋጀት

የትምህርቱ አዘጋጅች፡ **ኖርማን ጉሌይ**

**ዘላለም አስረስ እንደተረጎመው**

ይህ የጎልማሶች ሰንበት ትምህርት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መምሪያ የሚዘጋጀው በሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተ ክርስቲያን ዋና መስሪያ ቤት በሆነው በጀነራል ኮንፍረንስ ውስጥ ሆኖ፤ የጎልማሶች የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መምሪያን በሚያዘጋጀው ቢሮ ነው፡፡ መምሪያዎቹ የሚዘጋጁት የጀነራል ኮንፈረንስ አስተዳደር ኮሚቴ ንዑስ ኮሚቴ በሆነውና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መምሪያዎችን በሚያሳትመው የሰንበት ትምህርት ሕትመት ቦርድ ነው፡፡ የታተመው መምሪያ በውስጡ ዓለም አቀፋዊ የሆነ የምዘና ኮሚቴ ሀሳቦችንና የሰንበት ትምህርት ሕትመት ቦርድን ማረጋገጫ ስለሚያንጸባርቅ የአዘጋጁን (የአዘጋጆችን) ሀሳብ ብቻ የሚወክል አይደለም፡፡

*በተለየ ካልተጠቀሰ በቀር በዚህ ሰንበት ትምህርት ጥቅም ላይ የዋሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በሙሉ የተወሰዱት ከአዲሱ መደበኛ ትርጉም ነው፡፡*

*በኢትዮጵያ አድቬንቲስት ማተሚያ ቤት ታተመ*

*2ኛ ሩብ ዓመት*

ከመጋቢት 22 - ሰኔ 22፣ 2010 ዓ.ም

# ማውጫ

**አርዕስት** **ቀን** ☐☐

1.ዩኒቨርስ አቀፉ ተቃርኖ ——————---ከመጋቢት 22 -28 ------»—-------6

2. ዳንኤልና የመጨረሻው ጊዜ ——--- ከመጋቢት 29 - ሚያዝያ 5 -----»——17

3. የሱስ እና የራዕይ መጽሐፍ -------------—ከሚያዝያ 6 – 12 --------»——--28

4. ደኅንነት እና የመጨረሻው ጊዜ------------ከሚያዝያ 13 – 19 --------»——--38

5. ክርስቶስ በሰማያዊው መቅደስ -------------ከሚያዝያ 20 – 26------»——--50

6. የሕግ “መለወጥ” ---------------------ከሚያዝያ 27 - ግንቦት 3 -----»——--61

7.የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 24 - 25---------ከግንቦት 4- 10 -------»———---73

8.ፈጣሪን ማምለክ -------------------------ከግንቦት 11 – 17 -------»————--85

9. የመጨረሻው ጊዜ ማታለያዎች -----------ከግንቦት 18- 24 -------»———--96

10.አሜሪካ እና ባቢሎን --------------------ከግንቦት 25 -- ሰኔ 1-----»---------108

11.የእግዚአብሔር ማኅተም ወይስ-----------ከሰኔ 2 – 8 ------------»-----------121
የአውሬው ምልክት?

12.ባቢሎን እና አርማጌዶን------------------ ከሰኔ 9 – 15 -------»--------------133

13.የጌታችን የየሱስ ዳግም ምጽአት---------ከሰኔ 16 - 22 -------»--------------144

# መግቢያ

## ክርስቶስ እና የመጨረሻዎቹ ቀናት

የሱስ ሰብዓዊውን ሥጋ ለብሶ በምድር በተመላለሰባቸው በእነዚያ የመጨረሻዎቹ ሰዓታት የሚከተሉትን የማጽናኛ ቃላት ለደቀ መዛሙርቱ ነግሯቸው ነበር፡

"ልባችሁ አይጨነቅ፤ በእግዚአብሔር እመኑ፤ በእኔም ደግሞ እመኑ፡፡ በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፤ ይህ ባይሆንማ ኖሮ እነግራችሁ ነበር፤ የምሄደውም ስፍራ ላዘጋጅላችሁ ነው፡፡ ሄጄም ስፍራ ካዘጋጀሁላችሁ በኋላ፣ እኔ ባለሁበት እናንተም ከእኔ ጋር እንድትሆኑ ልወስዳችሁ ዳግመኛ እመጣለሁ፡፡ እኔ ወደምሄድበትም ስፍራ የሚያደርሰውን መንገድ ታውቃላችሁ፡፡ " (ዮሐ. 14፡1-4)፡፡

ምንም እንኳ የሱስ የተናገራቸውን ቃላት ትርጓሜ ወይም ትንቢቱ የሚፈጸምበትን ጊዜ ሙሉ ለሙሉ በእርግጠኝነት ማስተዋል ባይችሉም፤ ከዚህ መልእክት መጽናናት ማግኘታቸው ግን እሙን ነበር፡፡ በአባቱ ቤት ስላለው መኖሪያ? የሱስ ራሱ እያዘጋጀላቸው ስለሚገኘው ስፍራ? እነዚህ ነገሮች በወቅቱ በዚህ ምድር በራሳቸው ሊያገኙ ከሚችሏቸው ማናቸውም ነገሮች ይልቅ የተሻሉ ይሆናሉ፡፡

የሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር አረፍ ባለ ጊዜ ከዳግም መገለጡ አስቀድሞ ስለሚከሰቱት ነገሮች በወፍ በረር ነግሯቸው ነበር፡፡ ይህ "ትንቢተ ታሪክ" እምብዛም መሳጭ ወይም አስደሳች ይዘት አልነበረውም፡፡ ጦርነት፣ ጦርነትን የሚያናፍስ ወሬ፣ የሕዝብ በሕዝብ ላይ መነሳት፣ የመሬት መንቀጥቀጥ፡፡ "ይህ ሁሉ ግን የምጡ መጀመሪያ" ሲሆን--ስደት፣ ክህደት፣ መሳት እና ፈተና የዚሁ ክስተት አካል ናቸው፡፡

ዛሬ እኛ ከትንቢት የታሪክ ፍሰት አኳያ ምቹ ዘመን ላይ የምንገኝ እንደመሆናችን የሱስ በማስጠንቀቂያነት ካስቀመጣቸው ነጥቦች መሃል አብዛኞቹ ገቢራዊ መሆናቸውን መመልከት እንችላለን፡፡ ለአብነት ያህል የሁለት ዐበይት ትንቢቶችን ፍጻሜ መመልከቱ በቂ መሆን ይችላል፡፡ የመጀመሪያው በዳን. 7፡25 "ለዘመን፣ ለዘመናት፣ ለዘመን እኩሌታም" በሚል የተጠቀሰው (በተጨማሪ፡ ራእ. 12:6፣ 14፣ 13:5፣ ዘኁ. 14:34) እና በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በ(538 ዓ.ም.) ጀምሮ በአሥራ ስምንተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ በ(1798 ዓ.ም.) ያበቃው ሲሆን፤ ሌላው ረጅም ዘመናት ያስቆጠረውና በዳን. 8፡14 የምናገኘው የ2300 ቀናት ትንቢት ደግሞ በ1844 ዓ.ም. ላይ ፍጻሜ አግኝቶአል፡፡

ዛሬ እኛ "በቀኖቹ መጨረሻ" (ዳን. 12፡13) እየኖርን መሆኑ እሙን ነው፡፡ ሰብዓዊ ፍጡራን ክርስቶስ ዳግም ተገልጦ የምድር ታሪክ የሚዘጋባት ያቺ ዕለት መቼ እንደሆነች አናውቅም--እንደውም ማወቁም አያስፈልገንም! ይልቁንም ያቺ ዕለት ጊዜዋን ጠብቃ ከተፍ እንደምትልና ለዚያች ቀን ተዘጋጅተን መገኘት የሚገባን መሆኑን ብቻ ማወቅ ይገባናል፣ ያስፈልገናልም፡፡ ግን እንዴት? ምናልባት የሚከተለው ጥቅስ ለዚህ ጥያቄ ምርጥ መልስ መሆን ይችላል፡ "እንግዲህ ጌታ ክርስቶስ ኢየሱስን እንደተቀበላችሁት እንዲሁ በእርሱ ኑሩ" (ቆለ. 2፡6)፡፡ በሌላ አነጋገር ትኩረታችንን ለየዕለቱ ዝግጅታችን በብቸኝነት ቁልፍ በሆነው በራሱ በክርስቶስ ላይ በማድረግ ፋንታ--ከፍተኛ መጠን ባላቸው የዳግም ምጽአቱ ምልክቶች በሆኑት የመጨረሻው ዘመን ክስተቶች፣ ርዕሰ ዜናዎችና ንድፈ ሃሳቦች ላይ ብቻ አብልጦ መጠመድ በቀላሉ ከእቅፉ ሾልኮ የመጥፋት አደጋ ሊያስከትል ይችላል፡፡

የዚህ ሩብ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በመጨረሻው ዘመን ላይ ትኩረት ቢያደርግም፤ ከዚያ ውጪ ያሉ ጽንሰ ሃሳቦችንም ይዳስሳል፡፡ የትምህርቱ ዋንኛ ትኩረት የሆነውን የሱስ--ከመጨረሻው ዘመን ዐውድ እና ከምናደርጋቸው

ዝግጅቶች አኳያ እንመለከተዋለን፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ከታሪክና ታሪካዊ ክስተቶች አኳያ ስለ መጨረሻው ዘመን የሚናገር እንደመሆኑ--በታሪክ የተቀመጡ ቀናቶችን፣ ክስተቶችንና ራሱን ታሪክን በጥልቀት እንፈትሻለን፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ የሱስ፣ ስለ ማንነቱ፣ ለእኛ ስላደረገው ነገር፣ በእኛ ውስጥ ሆኖ ስለሚሠራው ሥራ እንዲሁም ለሁለተኛ ጊዜ ሲገለጥ ስለሚተገብራቸው ነገሮች በራሱ በዚህ ዐውድ ይነግረናል፡፡ ራሱ የተሰቀለው ክርስቶስ የእምነታችን ማዕከል ሊሆን የግድ ነው፡፡ ወይም ጳውሎስ እንደተናገረው "በመካከላችሁ ሳለሁ ኢየሱስ ክርስቶስን ያውም የተሰቀለውን፣ እርሱን ብቻ እንጂ ሌላ እንዳላውቅ ወስኜ ነበር" (፤ቆሮ. 2፥2)፡፡ ትኩረታችን አብልጦ በእርሱ ላይ በሆነ ቁጥር ይበልጥ እርሱን እየመሰልንና እየታዘዝን በመሄድ ለሚጠብቀን ነገር በላቀ የተዘጋጀን እንሆናለን፡፡ ይኸውም ከመጨረሻው በፊት እንዲሁም በመጨረሻ ላይ የሱስ ለሚወዱት ባዘጋጀው "ቦታ" ስንገባ ነው፡፡

**ኖርማን አር. ጉሌይ (ፒኤች.ዲ.) በሳውዘርን አድቬንቲስት ዩኒቨርሲቲ የነገረ መለኮት ተመራማሪ ፕሮፌሰር ናቸው**

# አንደኛ ትምህርት

ከመጋቢት 22 -28

## ዩኒቨርስ አቀፉ ተቃርኖ

### ሰንበት ከሰዓት

***ለዚህ ሳምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡--*** *ሕዝ. 28:1-2፣ 11 –17፣ ዘፍ. 3:1–7፣ ራእ. 12:1–17፣ ሮሜ 8:31–39፣ ራእ. 14:12፡፡*

ሀቀኛ ገወ ተነታ ቷኒፀገሪ

**"ዘንዶውም በሴቲቱ ላይ ተቆጣ፤ ከቀረት ልጆቿም ጋር ሊዋጋ ሄደ፤ እነርሱ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁና የኢየሱስን ምስክር አጥብቀው የያዙ ናቸው፡፡"**

ዓለም ከመጽሐፍ ቅዱስ ምልከታ ስትቃኝ በታላቅና ጽኑ ውዝግብ መሃል ትገኛለች፡፡ ኃጢአት፣ ሥቃይ፣ ሞት፣ የመንግሥታት መነሳትና መውደቅ፣ የወንጌል መሰራጨት፣ የመጨረሻው ዘመን ክስተቶች-- እነዚህ ሁሉ ከዩኒቨርስ አቀፍ ተቃርኖ ዐውድ ገቢራዊ በመሆን ላይ ይገኛሉ፡፡

ነገር ከሥሩ፤ ውሃ ከጥሩ--እንደሚባለው ተቃርኖው የጀመረባቸውን ወሳኝ ስፍራዎች በዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችን እንመለከታለን፡፡ እነሆ ዐመጻ ፍጹም ሆኖ በተፈጠረው ሉሲፈር ልብ በስውር ተጠነሰሰ፡፡ እርሱም ይህንኑ ዐመጻ ወደ ምድር ይዞ በመውረድ ፍጹም ወደ ነበሩት አዳምና ሔዋን አስተላለፈ፡፡ በእነዚህ ሁለት አበይት መነሾዎች፤ ማለትም በሉሲፈር እና በመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችን ውድቀት መንስኤ ታላቁ ውዝግብ ስር መስደድ ጀመረና ይኸው እስከ ዛሬ ቁጣና መአት መሃል እንገኛለን፡፡ እኛ እያንዳንዳችን የዚያ ዩኒቨርስ አቀፍ ተውኔት አካል ነን፡፡

አንድ ቀን ይህ ምድራዊ ሰቆቃ ማክተም ብቻ ሳይሆን ሰይጣን ሙሉ ለሙሉ በክርስቶስ ድል ተመትቶ ውዝግቡ በድል መጠናቀቁ መልካም የምስራች ሲሆን፤

የሱስ በመስቀል ላይ የሠራውን ፍጹምና የተሟላ የጽድቅ *ሥራ* ተከትሎ ሁላችንም የድሉ ተጋሪዎች መሆናችን ደግሞ ከሁሉ የላቀው የምስራች ነው፡፡ በየሱስ የተሰጠንን ተስፋ በልባችን ሰንቀን ምጽአቱ የተረጋገጠውን ጌታ እየተጠባበቅን፤ እንደ አንድ የድሉ አካል በእርሱ ላይ እምነት እንዲኖረንና እንድንታዘዘው እግዚአብሔር ጥሪ ያደርግልናል፡፡

## እሑድ መጋቢት 23

## ፍጹም የነበረው ፍጡር አወዳደቅ

አጽናፈ ሰማይን (ዩኒቨርስን) ያማከለው ውዝግብ የመጽሐፍ ቅዱስን ዓለማቀፋዊ ገጽታ ታሪካዊ ዳራ ቅርጽ የሚሰጠን ከሆነ--ጉዳዩ ወደ ብዙ ጥያቄዎች ይመራናል፡፡ ከእነዚህም አንዱና ዋንኛው *ይህ ሁሉ እንዴት ተጀመረ?* የሚለው ይሆናል፡፡ መጀመሪያ አፍቃሪው አምላክ የፈጠረው ፍጹም የሆነውን አጽናፈ ሰማይ እንደመሆኑ ክፋት፣ አመጻ፣ ግፍ እና ቅራኔ የፍጥረት *ሥራ*ው አካል አልነበሩም፡፡ ስለዚህ ውዝግቡ የተከሰተው ከቀደመው የፍጥረት *ሥራ*ው ተነጥሎ፣ ኋላ ላይ እንደመሆኑ የእጆቹ *ሥራ* ውጤት ተደርጎ መቆጠር አይችልም፡፡ የሆነው ሆኖ በዚህ ምድር እየተስተዋለ ያለው ውዝግብ ተጨባጭና ሁላችንንም ያካተተ ነው፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡--ሕዝ. 28፡1-2፣ 11--17፣ ኢሳ. 14፡12--14፡፡ ስለ ሉሲፈር ውድቀትና ስለ ክፋት መነሳት ምን ያስተምሩናል?**

ሉሲፈር በሰማይ የሚኖር ፍጹም ፍጡር ነበር፡፡ በተለይ በእንደዚያ ዓይነት ፍጹም ስፍራ እየተመላለሰ ክፋት እንዴት ከእርሱ ተነሳ? በእርግጥ ስለዚህ ጉዳይ የምናውቀው ነገር የለም፡፡ እንደውም፣ ምናልባት መጽሐፍ ቅዱስ "የዐመፅ ምስጢር" (2ተሰ. 2፡7) ብሎ የሚጠራው ለዚህ ይሆን?

እግዚአብሔር የማሰብ ችሎታ ላላቸው ሁሉም ፍጥረቶቹ ከሰጠው ተጨባጭ የመምረጥ ነጻነት ውጪ ለሉሲፈር ውድቀት እንደ መንስኤ የሚቆጠር አንድም ምክንያት የለም፡፡ “ኃጢአት እንዴት እንደተጠነሰሰ ለመግለጽ ለአብሮነቱ ምክንያት የመስጠትን ያህል አዳጋች ነው… ኃጢአት ሰርጎ ገብ እንደመሆኑ ለአብሮነቱ አንዳች ምክንያት መስጠት አይቻልም፡፡ ኃጢአት ምስጢራዊና ከተጠያቂነት አፈንጋጭ ባህሪ ያለው እንደመሆኑ ለእርሱ ሰበብ መስጠት--ለራሱ ለኃጢአት ዘብ እንደመቆም ይቆጠራል፡፡ ስለዚህ ለኃጢአት ሰበብ ሲቀርብ ወይም ለመከሰቱ ምክንያት ሲቀመጥ --ኃጢአት እንደ ኃጢአትነት መታየቱ ይቀራል፡፡”—*The Great Controversy*, pp. 492, 493.

ኃጢአት የተሰኘውን ቃል ክፉ በሚለው ብንተካው ከላይ የተመለከትነው የሀሳብ ፍቺ አይፋለስም፡፡ ክፋት እንዴት እንደተጠነሰሰ ለመግለጽ ለአብሮነቱ ምክንያት የመስጠትን ያህል አዳጋች ነው… ክፉው ሰርጎ ገብ እንደመሆኑ ለአብሮነቱ አንዳች ምክንያት መስጠት አይቻልም፡፡ ክፉው ምስጢራዊና ከተጠያቂነት አፈንጋጭ ባህሪ ያለው እንደመሆኑ ለእርሱ ሰበብ መስጠት--ለራሱ ክፉው ዘብ እንደመቆም ይቆጠራል፡፡ ስለዚህ ለክፉው ሰበብ ሲቀርብ ወይም ለመከሰቱ ምክንያት ሲቀመጥ--ክፉው እንደ ክፉነቱ መታየቱ ይቀራል፡፡

የግል ተሞክሮዎን ከተጨባጩ የመምረጥ ነጻነትዎ አኳያ አሰብ ያድርጉ፡፡ የተሰጠንን ነፃ የመምረጥ ችሎታ በጸሎትና በጥንቃቄ ጥቅም ላይ ማዋል ያለብን ለምንድን ነው?

## ሰኞ መጋቢት 24

## ሊመራ ከሚችለው ዕውቀት በላይ

ምንም እንኳ ክፉው ለምን እንደተከሰተ ማብራራት ባንችልም (ለህልዎቱ ተገቢ ምክንያት እስከሌለ ድረስ) ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በሰማይ በሉሲፈር ልብ ውስጥ መጠንሰሱን ይፋ ያደርግልናል፡፡ ከኤለን ጂ. ኋይት ሥራዎች ከምናገኛቸው

አስገራሚ ተጨማሪ ብርሃኖች (ለምሳሌ በ "ታላቁ ተጋድሎ" መጽሐፍ "የክፉው አጀማመር" በሚል የቀረበው ምዕራፍ) ውጪ መጽሐፍ ቅዱስ ኃጢአት በሰማይ እንዴት እንደተጠነሰሰ እምብዛም ሲነግረን አይስተዋልም፡፡ ሆኖም የምድር አነሳሱን አስመልክቶ ግን የእግዚአብሔር ቃል ይበልጥ ግልጽ መልእክት ይሰጠናል፡፡

**ጥቅሱን ያንብቡ፡--ዘፍ. 3፡1-7፡፡ ወደ ብርሃን ሲመጣ፤ አዳምና ሔዋንን ተወቃሽ አድርጎ ያሳየ ምን ነገር ተከሰተ?**

---

---

ሔዋን እግዚአብሔር የነገራቸውን በሚገባ የምታወቅ መሆኗ ጉዳዩን በእጅጉ አሳዛኝ ያደርገዋል፡፡ እንደውም የተነገሯቸውን እነዚያኑ ቃላት ደግማ እንደ ተናገረች እንመለከታለን "ነገር ግን እግዚአብሔር 'በአትክልቱ ስፍራ መካከል ከሚገኘው ዛፍ ፍሬ እንዳትበሉ፤ እንዳትነኩትም፤ አለበለዚያ ትሞታላችሁ' ብሎአል" (ዘፍ. 3፡3)፡፡ ከጥቅሱ እንደምንመለከተው ከፍሬው መብላት ሞት ሊያስከትል እንደሚችል በሚገባ ታውቅ ነበር፡፡

በዚህ ጊዜ ሰይጣን እግዚአብሔር የተናገራቸውን ቃላት በግልጽ እና በጉልህ ተቃረነ "እባቡም ሴቲቱን እንዲህ አላት 'መሞት እንኳ አትሞቱም'" (ዘፍ. 3፡4)፡፡

ምን ያህል የተራራቀ ንጽጽር ነው? ሰይጣን ጮሌ የሆነውን አቀራረብ የተጠቀመው መጀመሪያ ላይ ነበር፡፡ ሆኖም አንዴ ትኩረቷን ካገኘ በኋላ ግን እንደማትቋቋመው በመመልከቱ የጌታን ትእዛዝ በግልጽ ጥሶ ለማቅረብ ደፈረ፡፡ ሔዋን ዕውቀት እያላት ይህ መከሰቱ ጉዳዩን ልብ የሚሰብር ያደርገዋል፡፡ እንግዲህ "አላወቅኩም ነበር" አትል ነገር--በሚገባ ታውቅ ነበር፡፡

ሔዋን ይህ ዕውቀት እየነበራት የሆነው ሆነና እርሷ ግን ተሳሳተች፡፡ ፍጹም ድባብ ሰፍኖበት በነበረው ኤደን ዕውቀት በራሱ ሔዋን (እውነትን ያውቅ የነበረውን አዳም ጨምሮ) ኃጢአት እንዳትሠራ ለመጠበቅ በቂ አልነበረም፡፡ እኛም ብንሆን

እውነትን ማወቃችን ወይም በእውነት ላይ ያለን ዕውቀት ብቻውን ዛሬ እኛን ለማዳን በቂ ነው ብለን በማሰብ ራሳችንን ማታለል የለብንም፡፡ በእርግጥ የእግዚአብሔር ቃል የሚነግረንን ማወቅ ያስፈልገናል፡፡ ነገር ግን ቃሉን ከማወቃችን በተጨማሪ የሚነግረንን ለመታዘዝ ራሳችንን ለእርሱ ማስገዛት ይጠበቅብናል፡፡

እግዚአብሔር አንድ ነገር ሲናገር ሰይጣን ደግሞ ሌላ ነገር ተናገረ፡፡ አዳምና ሔዋን የአምላካዊው ቃል ዕውቀት የነበራቸው ቢሆንም ነገር ግን ምርጫቸው ሰይጣንን ማድመጥ ሆነ፡፡ ባለፉት ሺህ ዓመታት ምን ያህል አነስተኛ ለውጦች እንደተስተዋሉ ያስቡ፡፡ እኛም ተመሳሳይ ስህተት ላለመሥራት ምን ማድረግ እንችላለን?

## ማክሰኞ መጋቢት 25

## ጦርነት በሰማይና በምድር

በመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችን ላይ የደረሰው ውድቀት ይህችን ዓለም በኃጢአት፣ በክፉው እና በሞት ጥላ ስር እንድትወድቅ አደረጋት፡፡ ምናልባት ውድቀትን ተከትሎ በተከሰተው ሁኔታ ወይም የማን ስህተት በመሆኑ ዙሪያ አንዳንዶች ላይስማሙ ቢችሉም ነገር ግን ዙሪያችንን እያወከ ያለውን አመጻ፣ ብጥብጥና ውዝግብ ማን ሊክድ ይችላል?

በአጽናፈ ሰማይ ስለተነሳው ተቃርኖ መነጋገራችን መልካም ነው፤ እውነትም ነው፡፡ ነገር ግን የግጭቱ መንስኤ ምንም ይሁን ምን በዚህም ምድር እየተካሄደ ነው፡፡ በእርግጥ ከዔድን ውድቀት አንስቶ እስከ መጨረሻዎቹ ክስተቶች ብሎም የየሱስ የዳግም ምጽአት ያለው አብዛኛው ግዙፉ የተቃርኖ ታሪክ የመጽሐፍ ቅዱስ አካል ነው፡፡ እኛም የምንኖረው በዚህ ተቃርኖ ውስጥ ነው፡፡ ከዚህ ሁሉ እንቅስቃሴ ጀርባ ስላለው ነገር የእግዚአብሔር ቃል ማብራሪያ ይሰጠናል፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ እንዴት ወደ ፍጻሜ እንደሚመጣ ይፋ ያደርግልናል፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡--ራእ. 12፡ 1-17፡፡ ምዕራፉ በሰማይና በምድር ስለ ተከሰቱት ምን ዓይነት ጦርነቶች እየነገረን ነው?**

---

---

በሰማይ የተካሄደውን ጦርነት እና ምድራዊዎቹን ጦርነቶች በጥቅሱ እንመለከታለን፡፡ የመጀመሪያው ጦርነት የተደረገው በዘንዶው (ሰይጣን፣ ራእ. 12፡7 -9) እና በሚካኤል (የዕብራይስጥ ትርጉሙ፡ "እንደ እግዚአብሔር ያለ ማን ነው?") መካከል ነበር፡፡ ሰይጣን (ጠላት፣ ባለጋራ) በሚል ስያሜ መታወቅ የጀመረው አመጸኛው ሉሲፈር--ዘላለማዊ ፈጣሪ የሆነውን የሱስ የሚዋጋ ፍጡር ሆነ (ዕብ. 1፡1 -2፣ ዮሐ. 1፡1-4)፡፡

ሉሲፈር በፈጣሪው ላይ እያመጸ ነበር፡፡ ታላቁ ተቃርኖ በአማልክት መካከል የተፈጠረ የከረረ ጸብ ሳይሆን በፈጣሪው ላይ ያመጸው ፍጡር ዐመጹን ፍጥረታትን በማጥቃት ጭምር እያሳየ ያለበት ትዕይንት ነው፡፡

ከክርስቶስ ጋር በሰማይ ባደረገው ግጥሚያ ሽንፈት የቀመሰው ሰይጣን፤ የሱስ ሰብዓዊውን ሥጋ ለብሶ ወደዚህ ምድር ሲመጣ ሊያጠቃው ተመኝቶ ነበር (ራእ. 12፡4)፡፡ አሁንም በክርስቶስ ውልደት ወቅት የውጊያ እቅዱ የከሸፈበት ሰይጣን፤ የሱስ በጾም በደከመበት በምድረበዳ፣ ኋላም በቀራኒዮ መስቀል ላይ ጽኑና የማይቀለበስ የሽንፈት ጽዋ ለመጎንጨት ተገደደ፡፡ ሰይጣን ከዚህ በኋላ በክርስቶስ ሕዝቦች ላይ ብርቱ ጦርነት ከፈተ፡፡ ይህ አብዛኛውን የክርስትና ታሪክ የሚሸፍነው ቁጣና መአት (ራእ. 12፡6፣ 14-16) እስከ ምድር ፍጻሜ የሚቀጥል ሲሆን (ራእ. 12፡17) ይኸውም በየሱስ ዳግም ምጽአት ሌላ ሽንፈት እስኪቀምስ ነው፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡--ራእ. 12፡10-12፡፡ በሌሎቹ ጥቅሶች ከተመለከትናቸው ውዝግቦችና ተቃርኖዎች አኳያ በእነዚህ ጥቅሶች የምናገኘው ተስፋ ምን ይመስላል?**

## ረቡዕ መጋቢት 26

## እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ

የራእይ መጽሐፍ የእግዚአብሔር ሕዝቦች በዘመናት የሚደርስባቸውን ስደት በየአብያተ ክርስቲያናቱ ታሪክ ጥሩ አድርጎ በመከፋፈል በትንቢት አስቀምጧል፡፡ በራእ. 12፡6 የምናገኘው 1260 ትንቢታዊ ቀናት (በተጨማሪ ራእ. 12፡14 ይመልከቱ) በቤተ ክርስቲያን ላይ የደረሰውን 1260 ዓመታት የፈጀ የስደት ዘመን ያመለክታል፡፡

*"እነዚህ ሐዋርያው ጳውሎስ ሰማዕት በሆነባቸው፣ በንጉሠ ነገሥት ኔሮ የግዛት ዘመን የጀመሩት የስደትና የመዐት ዘመናት አንዴ እየጋሙ ሌላ ጊዜ ደግሞ እየቀዘቀዙ ለአያሌ መቶ ዓመታት ቀጥለው ነበር፡፡ ክርስቲያኖች እጅግ አስከፊ ጥፋት የፈጸሙ ይመስል በሐሰት ተወነጀሉ፡፡ በምድር ላይ ለሚደርስ መቅሰፍት፣ ረሃብ፣ ቸነፈርና መሬት መንቀጥቀጥ እንደ ምክንያት ተቆጠሩ፡፡ ሁሉም በጥላቻና በጥርጣሬ ዐይን የሚመለከታቸው መሆናቸውን ተከትሎ ወሬ አቀባዮች ለጥቅማቸው ሲሉ ንጹሃኑን ለመካድ ዝግጁ ነበሩ፡፡ እንደ ሥርዓቱ አማጺ ተቆጥረው ተኮነኑ፣ በኃይማኖት ጠላትነት ተፈረጁ፣ በማኅበረሰቡ ላይ መዐት እንደሚያወርዱ ተምቾች ታዩ፡፡ እንደ ዛሬው ስታዲየም ክብ ሆነው በተገነቡ ትዕይነት ማሳያዎች ከፍተኛ ቁጥር የነበራቸው ክርስቲያኖች ለተራቡ አውሬዎች ተወረወሩ፣ በቁማቸውም ተቃጠሉ፡፡"—The Great Controversy,* p. 40.

በዚሁ ጊዜ ሴቲቱ (ቤተ ክርስቲያን) ወደ ምድረ በዳ ሸሸች (ራእ. 12፡6)፡፡ ሴቲቱ ሁለት ክንፎች እንዳሉት ንስር ሆና ተጠቅሳለች፡፡ ይህ ደግሞ እርዳታ ልታገኝ ወደምትችልበት ስፍራ በርራ መሄድ የመቻሏ ተምሳሌት ነው፡፡ ሴቲቱ በምድረ በዳ እንክብካቤ እየተደረገላት ስለነበር እባቡ ወይም ሰይጣን ሊደርስባት አልቻለም

(ራእ. 12፡14)፡፡ ብርቱ ስደት በተከሰተ ጊዜ እግዚአብሔር ሁሌም ትሩፋኑን ታድጓል፡፡ ደግሞም እስከ መጨረሻው ይህን ያደርጋል፡፡

ክርስቶስ በመጨረሻዎቹ ዘመናት ገቢራዊ በሚሆኑት በአደጋ የተሞሉ ሁናቴዎች ዐውድ ለሕዝቡ እንዲህ ብሎአል "እኔም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ" (ማቴ. 28፡20)፡፡ ከፍተኛ ቁጥር የነበራቸው ተከታዮቹ ሰማዕት ከሆኑበት ክስተት አኳያ ይህን ግሩም ተስፋ የምናስተውለው እንዴት ነው? (ሮሜ. 8:31–39፣ ማቴ. 10:28.)፡፡

---

---

ስደት፣ ረሃብ ወይም ሞት እንኳ ቢሆን ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን አይችልም፡፡ ክርስቶስ አብሮን በመሆኑ አሁንም ሆነ በመጨረሻዎቹ ጊዜያቶች ህመም፣ ሥቃይ፣ መከራ አልፎ ተርፎም ሞት አይደርስብንም ማለት አይደለም፡፡ በዚህኛው ሕይወት ከእነዚህ ነገሮች ነፃ ናችሁ የሚል ተስፋ አልተሰጠንም፡፡ ይኸውም በየሱስ እና እርሱ ለእኛ ባደረገልን ነገር እየተማመን፤ በመከራ ወቅት እግዚአብሔር ከእኛ ጋር እንዳለ የተሰጠንን የተስፋ ቃል እያስታወስን በአዲስ ሰማይና ምድር ተስፋ መኖር እንችላለን ማለት ነው፡፡ በዚህ ምድር በየትኛውም አስቸጋሪ ሁናቴ ውስጥ ብናልፍ እርሱን ተስፋ በማድረግ እየተመላለስን እንደ ጳውሎስ እንዲህ ማለት እንችላለን፡ "ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፤ ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ በዚያ ቀን ለእኔ ይሰጠኛል፤ ደግሞም ለእኔ ብቻ ሳይሆን፣ የእርሱን መገለጥ ለናፈቁ ሁሉ ነው" (2ጢሞቴ. 4፡8)፡፡ እኛ መገለጡን የምንናፍቅ ሁሉ ይህን ተስፋ የግላችን ማድረግ እንችላለን፡፡

## ሐሙስ መጋቢት 27

## ሕግ እና ወንጌል

እንደ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስትነታችን ስማችን አብልጦ የምናምንበትን ነገር መሰረት ይዞአል፡፡ *ሰባተኛ ቀን* የሚለው የመጠሪያ ስማችን አካል፤ አንዱን ትእዛዝ ይኸውም ሰባተኛውን ቀን ብቻ ሳይሆን አሥሩንም ትእዛዛት የመጠበቃችንን አንደምታ ያሳያል፡፡ *አድቬንቲስት* የሚለው የስማችን ክፍል በየሱስ ዳግም ምጽአት ላይ ያለንን እምነት ያመላክታል፡፡ የዚህ እውነት ብቸኛ ህልውና ክርስቶስ በመጀመሪያው ምጽአቱ ለኃጢአት ሥርየት የከፈለው ዋጋ ነው፡፡ በዚህ የተነሳ *ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት* የተሰኘው ስያሜያችን ሁለት መሰረታዊና የማይለያዩ ወቅታዊ እውነታዎችን ይዞአል፡ ሕግ እና ወንጌል፡፡

ሕግ እና ወንጌል ምን ያህል በቅርብ የተሳሰሩ መሆናቸውን እነዚህ ጥቅሶች እንዴት ያሳዩናል?

ኤር. 44:23 ______________________________

ሮሜ 3:20–26___________________________

ሮሜ. 7:7________________________________

ወንጌል የምስራች ነው፡፡ ምንም እንኳ ኃጢአተኞችና የእግዚአብሔርን ሕግ የተላለፍን በደለኞች ብንሆንም፤ ክርስቶስ እዳችንን በመስቀል ላይ መክፈሉን በእምነት መቀበላችንና ይቅርታ ማግኘታችን መልካም የምስራች ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አምላካዊውን ሕግ ሙሉ ለሙሉ የምንታዘዝበትም ኃይል እንዲሁ ተሰጥቶናል፡፡

የምድር ታሪክ በሚቋጭባቸው የመጨረሻዎቹ ጊዜያቶች በብርሃንና ጨለማ መሃል ያለው ታላቁ ተቃርኖ በብርቱ ቁጣና መዐት በሚጦዝበት በዚያን ወቅት የእግዚአብሔር ሕዝቦች በተለየ ዐውድ መቅረባቸው ብዙም ላይገርም ይችላል፡፡

በራእ. 14፡12 የምናገኘው ጥቅስ በሕግና በወንጌል መካከል ያለውን ግንኙነት እንዴት ያሳየናል?

---

---

የእግዚአብሔርን ሕግ መታዘዝ እንዳለባቸውና ይህን እንደሚያምኑ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስትነታችን--ሕጉን መታዘዝ ሕጋዊነት ሳይሆን እግዚአብሔርን በመውደድና በእርሱ በመዳን የሚገኝ ተፈጥሮአዊ ውጤት መሆኑን ለሌሎች ማሳየት የምንችለው እንዴት ነው? እንደ ዘዳ. 11፡1 እና 1ዮሐ. 5፡3 ያሉት ጥቅሶች ይህን ነጥብ በምን መልኩ ይደግፉታል?

## አርብ መጋቢት 28

**ተጨማሪ ሃሳብ፡** ራእ. 12፡ 9-12፤ *የኃይማኖት አባቶችና ነቢያት* ከተሰኘው መጽሐፍ “ኃጢአት ለምን ተፈቀደ?” ከገጽ 22-34 ያንብቡ፡፡

“ሁሉም ፍጡራን የፍቅርን ታማኝነት እስከተረዱ ድረስ በእግዚአብሔር ዩኒቨርስ ላይ የተስተካከለ መጣጣም ነበር፡፡ የፈጣሪያቸውን ዓላማ ማሳካት የሰማይ መላዕክት ደስታ ነበር፡፡ ክብሩን በማንጸባረቅና ምስጋናውን በመስጠትም ሐሴት ያደርጉ ነበር፡፡ የእግዚአብሔር ፍቅር ከሁሉም በላይ ሲሆን የእርስ በእርስ ፍቅርም ጠንካራና በስስት ያልተሞላ ነበር፡፡ ሰማያዊውን ፍቅር የሚያጎድፍ ያለመግባባትም አልነበረም፡፡ ሆኖም በዚህ ደስታን በተመላ መንግሥት ውስጥ ለውጥ ተከሰተ፡፡ እግዚአብሔር ለፍጡራኑ የሰጠውን ነጻነት በተሳሳተ አቅጣጫ የተረጎመ አንድ ፍጡር ብቅ አለ፡፡ ከክርስቶስ ቀጥሎ እጅግ በተከበረውና በሰማይ ነዋሪዎች ዘንድ ከፍ ያለ ኃይልና ግርማ በተሰጠው ሉሲፈር ኃጢአት ተጠነሰሰ፡፡” (የኃይማኖት አባቶችና ነቢያት ገጽ 24፡፡)

ኤለን ኋይት “የፍቅርን ታማኝነት” በሚል የጠቀሰቻቸውን ቃላት ልብ ይበሉ፡፡

ይህ ጠንካራ ፍቺ የያዘ ብርቱ ሃረግ ፍቅር ወደ ታማኝነት የመምራቱን ሐቅ ያመላክታል፡፡ የትዳር ጓደኛውን የሚወድ ወይም የምትወድ ተጓዳኝ ፍቅሯን የምትገልጸው ታማኝ በመሆን ነው፡፡ ይህ በሰማይ ፍጡራን እንደሆነ እኛም በምድር ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት ተመሳሳይ መርኅ የተከተለ ሊሆን ይገባል፡፡

## የመወያያ ጥያቄዎች፡

1. ሰይጣን በታላቁ ተቃርኖ ውስጥ ስላለው ሚና በተጨባጭ የሚያመላክት ምን ዓይነት የመጽሐፍ ቅዱስ ድጋፍ አለን? ክፉውን ነገር በሰይጣን ከመመሰል ባሻገር ሰይጣን በተጨባጭ መኖሩን ሰዎች ማስተዋል እንዲችሉ ልንረዳ የምንችለው እንዴት ነው?
2. እንደ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስትነታችን ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነት አኳያ በከፍተኛ ዕውቀት ተባርከናል፡፡ ምንም እንኳ ይህ ዕውቀት እጅግ አስደናቂ ቢሆንም እኛን ለማዳን በቂ ያልሆነው ለምንድን ነው? ከአእምሮ ዕውቀት በላቀ ምን ያስፈልገናል?
3. ዛሬ የሱስ በሕይወትዎ መኖሩን የተለማመዱባቸው መንገዶች የትኞቹ ናቸው? ማንኛውም ዓይነት አስቸጋሪ ሁናቴ ሲገጥምዎ እነዚህ ተሞክሮዎች እንዴት ሊረዱዎት ይችላሉ?
4. በሰንበት ትምህርት ጥናት ክፍለ ጊዜ "የፍቅርን ታማኝነት" በሚለው ሃረግ ላይ በደንብ ተነጋገሩ፡፡ ይህ ጽንሰ ሃሳብ በሕግ እና በጸጋ እንዲሁም በእምነትና በመታዘዝ መሃል ያለውን ግንኙነት በተሻለ እንድናስተውል የሚረዳን እንዴት ነው? በአጠቃላዩ የፍቅር ጽንሰ ሃሳብ ተፈጥሮ ውስጥ ስላለው ነጻነት ምን ያስተምረናል? አሁንም እንኳ "የፍቅርን ታማኝነት" ልንገልጽ የምንችልባቸው መንገዶች የትኞቹ ናቸው?

# ሁለተኛ ትምህርት

ከመጋቢት 29 - ሚያዝያ 5

## ዳንኤል እና የመጨረሻው ጊዜ

### ሰንበት ከሰዓት

***ለዚህ ሳምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡–*** *ሉቃ. 16:10፣ ዳን. 1፣ 2፣ 3:1–6፣ ራእ. 13:11–15፣ ዳን. 3:13–18፣ ዮሐ. 3:7፣ ዳን. 4፣ 6፡፡*

**የሳምንቱ ጥናት መሪ ጥቅስ**

***"ንጉሡም ዳንኤልን፣ ' ይህን ምስጢር ልትገልጥ ችለሃልና፣ በእውነት አምላካችሁ የአማልክት አምላክና የነገሥታት ጌታ፣ ምስጢርንም ገላጭ ነው' አለው፡፡" (ዳን. 2፡47)፡፡***

ጌታ ለጥንቷ እስራኤል ታላላቅ እቅዶች ነበሩት፡፡ "እናንተ ለእኔ የመንግሥት ካህናት የተቀደሰ ሕዝብ ትሆናላችሁ" (ዘፀ. 19፡6)፡፡ ይህ ቅዱስ ሕዝብ እና የካህናት ግዛት ያህዌ ብቸኛ አምላክ መሆኑን ለዓለም እንዲመሰክር ተጠርቶ ነበር (ኢሳ. 43፡10-12)፡፡ የሚያሳዝነው ሕዝቡ እግዚአብሔር ከሰጠው ቅዱስ ጥሪ ጋር ተጣጥሞ መራመድ ሳይችል በመቅረቱ ውሎ አድሮ በባቢሎን ምርኮ ግዞት ስር ለመውደቅ በቃ፡፡

እስራኤላውያን በአስከፊ ምርኮ ስር ቢወድቁም እግዚአብሔር ግን አሁንም አንዳንድ አይሁዳውያንን ምስክሮቹ አድርጎ መጠቀሙ ደስ የሚያሰኝ ክስተት ነበር፡፡ በሌላ አነጋገር ቀደም ብሎ በእስራኤልና በይሁዳ አማካይነት መሠራት ያልቻለው ነገር አሁን በዳንኤልና ሦስቱ አብረውት በምርኮ የወደቁ ጓደኞቹ ታማኝነት በተወሰነ ደረጃ መሠራት የሚችል ሆነ፡፡ በአንድ በኩል እነዚህ ሰዎች እስራኤል እንደ አገር ልትሆንና ልታደርግ ይገባት ለነበረው ነገር ምሳሌዎች ነበሩ፡፡

አዎን የእነዚህ ወገኖች ታሪክ ከመጨረሻዎቹ ቀናት እጅግ ርቀው ይገኙ በነበሩ ጊዜያቶችና ቦታዎች ተገለጡ፡፡ ዳንኤልና ጓደኞቹ በባቢሎን ቅጥር ይኖሩ ለነበሩ እግዚአብሔርን ለማያውቁ ጣኦት አምላኪዎች ምስክር እንደሆኑ ሁሉ፤ እኛ ዛሬ በመጨረሻዎቹ ጊዜያቶች የምንኖር ሕዝቦችም ምሳሌ መሆን የሚችል ጸባይና ባህሪ ከእነርሱ ማግኘት እንችላለን፡፡

## እሑድ መጋቢት 30

## በትንሽ ነገር ታማኝ መሆን

**"'በትንሽ ነገር ታማኝ የሆነ በትልቁም ይታመናል፤ በትንሽ ነገር ያልታመነ በትልቁም አይታመንም ' "** (ሉቃ. 16:10)፡፡

የሱስ የተናገራቸውን ቃላቶች ልብ ይበሉ፡፡ በጥቅሱ እንደምንመለከተው ለትንሹ ነገር መታመን ያን ያህል ከባድ ሳይሆን ቀላል ነው፡፡ ችግሩ ያለው በራሱ "በትንሽ ነገር" ላይ መታመን ያን ያህል አሳሳቢ መሆኑ ላይ አይደለም፡፡ አብዛኞቻችን በግል ተሞክሮአችንም ሆነ ከሌሎች ባገኘነው ምሳሌ (ወይም በሁለቱም) እንደምንገነዘበው ለመጀመሪያው ነገር የምናደርገው የድርድር አካሄድ ወደ ሌላኛው ይመራናል፡፡ ሌላኛው ደግሞ ወደ ሌላው እያለ በመጨረሻ " 'በትልቁም አይታመንም' " እስከ ሚለው መድረስ ይመጣል፡፡ ይህን ሃሳብ በአእምሮአችን እንደያዝን በባቢሎን ምርኮ ስር የነበሩትን የአራቱን አይሁዳውያን ተሞክሮ በዳን. ምዕ. 1 ላይ እንመልከት፡፡

**ከትንቢተ ዳንኤል መጽሐፍ ምዕ. 1 ያንብቡ፡፡ የጥንቷ እስራኤል አቋም እንደ ዳንኤል፣ አናንያ፣ ሚሳኤልና አዛርያ ሆኖ ሊንጸባረቅ የተገባ የነበረው እንዴት ነው? ዘዳ. 4፡6-8፣ ዘካ. 8፡23፡፡**

ምንም እንኳ ጥቅሱ (ዳን. 1፡20) ዳንኤልና ጓደኞቹ ከሌሎቹ "ዐሥር እጅ በልጠው" ለተገኙበት "ጥበብና ማስተዋል ጉዳይ" ይመገቡ የነበረውን ምግብ በቀጥታ ባያስተሳስረውም፤ ሆኖም ተያያዥነት እንደነበረው ግን በግልጽ መመልከት ይቻላል፡፡ ምዕራፉ በተጨማሪ እግዚአብሔር ይህንን እውቀት እና ጥበብ እንደ ሰጣቸው ይናገራል፡፡ ዳንኤልና ጓደኞቹ የባቢሎንን ንጹህ ያልሆኑ ምግቦች ለመመገብ በመቃወማቸውና በታማኝነታቸው በመጽናታቸው ጌታ ከእነርሱ ጋር መሥራት ችሎ ነበር፡፡ ወጣቶቹ ታዛዦች ሆኑ፤ እግዚአብሔርም ይህን መታዘዛቸውን ባረከ፡፡ እነዚያ ጥንታዊ እስራኤላውያን አራቱ ወጣቶች እንዳደረጉት ታማኝና ለአምላካዊው አስተምህሮ ጥብቅ ቢሆኑ ኖሮ እግዚአብሔር ለእነርሱ ያደረገውን ለሕዝቡም አያደርገውም ነበር? በእርግጥ ያደርገው ነበር! እኛም በመጨረሻው ዘመን የምንኖር፤ ታማኝ እስከሆንን ድረስ ለእነዚያ አራት ወጣቶች ያደረገውን ለእኛስ ቢሆን አያደርገውም?

**በጣም ብዙ ብርሃንና እውነት የተቀበልን ሕዝቦች እንደመሆናችን እንደ ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ብለን ራሳችንን መጠየቅ ይኖርብናል፡ ለተሰጠን ነገር ታማኝና ታዛዥ ኖረናል? እያንዳንዳችን በግል ለእግዚአብሔር ብርቱ ምስክር ለመሆን የሚያስችለንን አቋም መያዝ የምንችለው እንዴት ነው?**

## ሰኞ ሚያዝያ 1

## የዳንኤል ትህትና

በዳን. ምዕ 2 የሚገኘው መልእክት በመላው ዓለም እንዲህ ተብሎ የማይገለጹ ሕዝቦች በመጽሐፍ ቅዱሳዊው አምላክ እንዲያምኑ እረድቶአል፡፡ ምዕራፉ ስለ እግዚአብሔር ሕልዎት ብቻ ሳይሆን እርሱ የወደፊቱን አስቀድሞ የሚያውቅ አምላክ መሆኑን ጭምር እጅግ ምክንያታዊ በሆነ ማስረጃ ያቀርብልናል፡፡

ዳን. ምዕ. 2 ያንብቡ፡፡ ምዕራፉ እግዚአብሔር በተጨባጭ የነበረ፣ ያለና የሚኖር አምላክ መሆኑን በአሳማኝ ማስረጃ የሚያቀርበው እንዴት ነው? በዳን. 2፡40-43 በቀረበው መሰረት የዛሬውን አውሮፓ ይመልከቱ፡፡ ከሁለት ሺ ስድስት መቶ ዓመታት በፊት ይኖር የነበረ ይህ ሰው ከመለኮታዊ መገለጥ በስተቀር የነበረውን ሁናቴ እንዴት በትክክል መግለጽ ቻለ?

---

---

---

ዳንኤል ለተገለጠለት ነገር ተገቢውን ክብርና ዝና በግልጽና ያለ አንዳች ሐፍረት ለእግዚአብሔር ሰጠ፡፡ የንጉሡን ሕልም በማወቁ ብቻ ሳይሆን ፍቺውንም በመስጠቱ ይህን ጥበብ የግል ችሎታው በማስመሰል ራሱን በቀላሉ መኮፈስ ይችል ነበር፡፡ ነገር ግን ዳንኤል ከዚያ በተሻለ የሚያስተውል ሰው ነበር፡፡ እርሱና ሌሎች የጸለዩት ጸሎት (ዳን. 2፡17-23) በእግዚአብሔር ላይ የነበራቸውን መተማመን የሚያሳይ ነበር፡፡ ያለበለዚያማ ከተቀሩት ኮከብ ቆጣሪዎች ጋር በተገደሉ ነበር፡፡

ንጉሡ የጠየቀውን ምስጢር ከጠንቋዮቹ፣ ከአስማተኞቹም ሆኑ ከኮከብ ቆጣሪዎቹ መሃል አንዳቸውም ሊነግሩት እንደማይችሉ ዳንኤል ለንጉሡ ነግሮት ነበር፡፡ በተቃራኒው ብቸኛውና እውነተኛው ሰማያዊ አምላክ እግዚአብሔር ምስጢርን መግለጥ እንደሚችል ገለጸለት፡፡

ዳንኤል ከነበረው ትህትናና በእግዚአብሔር ላይ መታመን የተነሳ ብርቱ ምስክር ለመሆን ቻለ፡፡ በዚያ ዘመን የነበረው ዳንኤል ያን ትህትና ካሳየ እኛ በዚህ ዘመን የምንገኝ ወገኖች ምን ያህል የበለጠ ማሳየት ይኖርብን ይሆን? ደግሞስ እኛ ለዳንኤል ያልተገለጠው የደኅንነት እቅድ ተገልጦልን የለ? እንደው ምንም ነገር ትሑት ሊያደርገን ባይችል እንኳ የሱስ በመስቀል ላይ ያደረገውን ማወቃችን

ብቻውን በቂ ምክንያት ሊሆነን ይገባል፡፡

**መስቀሉ ስለ ትህትና ምን ሊያስተምረን ይገባል? ኃጢአተኞች ስለመሆናችን ብቻ ሳይሆን ለደኅንነታችን በእግዚአብሔር ላይ መተማመን እንደሚገባን አስመልክቶ ምን ይነግረናል? እርስዎ ያለ መስቀሉ የት ሊገኙ ይችሉ እንደ ነበር አሰብ ያድርጉ፡፡ ስለዚህ ከመስቀሉ ውጪ ሌላ በምን ሊመኩ ይችላሉ? ገላ. 6፡14፡፡**

## ማክሰኞ ሚያዝያ 2

## የወርቁ ምስል

የመጽሐፍ ቅዱስ አጥኚዎች በዳን. ምዕ. 3 የምናገኘውን ሦስቱ ዕብራውያን በዱራ ሜዳ የተጋፈጡትን ነገር በምድር ታሪክ መዝጊያ ወቅት የእግዚአብሔር ሕዝቦች ከሚገጥማቸውና በራእ. ምዕ. 13 ከቀረበው የግድያ ትዕይንት ጋር ያዛምዱታል፡፡

እነዚህን ሁለት ጥቅሶች ያስተያዩ፡--ዳን. 3፡1-6፣ ራእ. 13፡11-15፡፡ በሁለቱ ጥቅሶች (በዳንኤልና በራእይ) መሃል የምናገኛቸው ተዛምዶዎች ምንድን ናቸው?

---

---

አምልኮ የሁለቱም ርዕሰ ጉዳዮች ማዕከላዊ ክፍል ሲሆን የግዳጅ አምልኮ በሁለቱም መልእክቶች ቀርቦአል፡፡ ይህ ደግሞ ማናለብኝ የፖለቲካዊ ኃይሎች ለጌታ ብቻ የተመደበውን አምልኮ ለራሳቸው መጠየቃቸው ነው፡፡

**ይህን ጥቅስ ያንብቡ፡ ዳን. 3፡13-18፡፡ ታሪኩ በመጨረሻው ጊዜ ስለ ምንጋፈጠው ነገር ብቻ ሳይሆን ሊመጣ ያለውን ነገር እንዴት ማስተዋል እንደሚኖርብን ሊረዳን የሚችለው በምን መልኩ ነው?**

---

የወቅቱ ብቸኛ ልዕለ ኃያል አገር ንጉሥ የነበረው ናቡከደነፆር "ታዲያ ከእጄ ሊያድናችሁ የሚችል አምላክ ማን ነው?" ሲል በእነርሱና በሚያመልኩት እግዚአብሔር ላይ ተሳለቀ፡፡ ሆኖም ያ አምላክ ማን እንደሆነ ለራሱ ማወቅ የነበረበት ናቡከደነፆር ብዙም ሳይቆይ እንዲህ ሲል ምስክርነቱን ሰጠ፡ "መልአኩን ልኮ አገልጋዮቹን ያዳነ፣ የሲድራቅ፣ የሚሳቅና የአብደናጎ አምላክ ይባረክ፤ በእርሱ በመታመን የንጉሡን ትእዛዝ ጥሰው፣ ከአምላካቸው በቀር ሌላ አምላክ ለማገልገልም ሆነ ለእርሱ ለመስገድ ፈቃደኛ ባለመሆን ሕይወታቸውን አሳልፈው ሰጥተዋልና፡፡" (ዳን. 3፡28)፡፡

ንጉሡ እንደዚያ ዓይነቱን ታምራት ከተመለከተ በኋላ እነዚህ ሰዎች በሚያመልኩት አምላክ ዙሪያ አንድ የተለየ ነገር መኖሩን ለማመን አለመቸገሩ ብዙም አያጠያይቅም፡፡

ምናልባት እነዚህ ወጣቶች ከሚነደው እሳት ባይድኑም እንኳ በእግዚአብሔር ላይ የነበራቸው እምነት ጽኑ ነበር (ዳን. 3፡18)፡፡ እሳቱ ውስጥ በቁማቸው ገብተው ቢቃጠሉ እንኳ የንጉሡን ትእዛዝ ሳይሆን ትክክለኛውን ነገር ብቻ ማድረግ የነበረባቸው ለምንድን ነው? ይህ ታሪክ ምንም ይምጣ ምን ወጣቶቹ ባመኑበት ጸንተው ለመቆም ስለነበራቸው ቁርጠኝነት ብርቱ ምስክርነት ይሰጠናል፡፡

**በመጨረሻዎቹ ዘመናት ከአምልኮ ጋር ተያያዥነት ያለው ጉዳይ ሲከሰት እንደ እነርሱ በታማኝነት መቆም ለመቻላችን ምን ያህል እርግጠኞች መሆን እንችላለን? ዛሬ "በትንሹ ነገር" ታማኝ ሳንሆን እንደ መጨረሻዎቹ ዘመናት ያሉ ታላላቅ ቀውሶች ሲከሰቱ ታማኝ ሆነን እንገኛለን ብለን እንዴት ልናስብ እንችላለን?**

## ረቡዕ ሚያዝያ 3

## ከአሕዛብነት መለወጥ

ዳን. ምዕ. 3 የሚያበቃው ናቡከደነፆር የእውነተኛውን አምላክ ህልዎት እና ኃይል መቀበል ከነገረን በኋላ ነው፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔርንና የእርሱን ኃይል ማወቅ ዳግም ከመወለድ ተሞክሮ ጋር ተመሳሳይ አለመሆኑን አስመልክቶ የሱስ የተናገረው በጣም ወሳኝ ነጥብ ነው (ዮሐ. 3፡7)፡፡ በእርግጥ በዳን. 4፡30 የቀረበው ሰው ምንም ይሁን ምን እውነተኛውን አምላክ የተቀበለ ነፍስ ነው፡፡

**ጥቅሱን ያንብቡ፡ ዳን. 4፡30፡፡ የዚህ ሰው ችግር ምን ነበር? በተጨማሪ የሚከተሉትን ጥቅሶች ይመልከቱ፡ ዮሐ. 15:5፣ ሐዋ. 17:28፣ ዳን. 5:23፡፡**

---

---

አራተኛው ምዕራፍ በተገባደደበት ወቅት ማንኛውም እውነተኛ ኃይል የእግዚአብሔር መሆኑንና ያለዚህ አምላክ እርሱ ምንም መሆኑን በአስቸጋሪ መንገድም ቢሆን ናቡከደነፆር ትምህርት አግኝቶ ነበር፡፡

“በአንድ ወቅት በኩራት ታብዮ የነበረው ንጉሥ ትሑት የእግዚአብሔር ልጅ ሆነ፡፡ አምባገነኑና የሌሎችን ሀሳብ ይንቅ የነበረው ገዢ ጥበበኛና ርኅሩኅ ንጉሥ ወጣው፡፡ የሰማይ አምላክን አርክሶና ተሳድቦ የነበረው ይህ ሰው አሁን ግን የልዑል አምላክን ኃያልነት ተቀበለ፡፡ የእግዚአብሔር ሞገስና የተከታዮቹ ደስታ ይበልጥ እንዲንሰራፋ የማድረግ ጽኑ ምኞትም አደረበት፡፡ ናቡከደነፃር ከነገሥታት ንጉሥና ከጌቶች ጌታ ባገኘው ግሳጼ በመጨረሻ ገዢዎች ሁሉ ሊማሩት የሚገባውን ትምህርት ያገኘ ሲሆን ይኸውም--እውነተኛ ታላቅነት የእውነተኛ

መልካምነት አካል መሆኑን ነበር፡፡ የሕያው እግዚአብሔርን ሕልውና በመቀበል እንዲህ አለ፡ 'እኔ ናቡከደነፆር እርሱን አወድሰዋለሁ፤ ከፍ ከፍ አደርገዋለሁ፤ አከብረዋለሁም፤ እርሱም በትዕቢት የሚመላለሱትን ማዋረድ ይችላል፡፡' "— Ellen G. White, *Prophets and Kings*, p. 521.

**ጥቅሱን ያንብቡ፡ ዳን. 4፡35፡፡ ናቡከደነፆር እግዚአብሔርን አስመልክቶ ምን ዓይነት እውነቶችን ገለጠ**

___

___

___

አሕዛብ የነበረው ሰው ለዕብራውያኑ አምላክ ሥልጣን፣ ግዛት እና ኃይል እውቅና ከሰጠ በኋላ ዳንኤል ምዕ. 4 ይጠናቀቃል፡፡ ይህ ሁኔታ ኋላ ላይ በአይሁዳውያን ምስክርነትና በእግዚአብሔር ኃይል ቤተ ክርስቲያን ስትዋቀር አሕዛብ ስለ ጌታ እውነትን ተምረው ያን የተማሩትን እውነት መልሰው ለዓለም መስበክ ለጀመሩበት ትዕይንት ፈር ቀዳጅ ነበር፡፡

**ጥቅሱን ያንብቡ፡ ዮሐ. 3፡7፡፡ ምንም እንኳ የመጨረሻውን ጊዜ ክስተቶች--ከሞት ዐዋጅ፣ ከአምልኮ እና ከስደት አኳያ ብናስበውም፤ ነገር ግን ከሁሉም በላይና ባሻገር ሕዝቡን ለመጨረሻው ጊዜ ስለሚያዘጋጀው ነገር የሱስ ምን ይላል?**

## ሐሙስ ሚያዝያ 4

## የዳንኤል ታማኝነት

**ዳን. ምዕ. 6 ካነበቡ በኋላ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይመልሱ፡**

1. ዳን. 6፡4-5 ስለ ዳንኤል ጸባይ ምን ይገልጽልናል? እንዴት ልንታይ እንደሚገባ አስመልክቶ ከእነዚህ ጥቅሶች ምን ዓይነት ትምህርቶች መውሰድ እንችላለን

______________________________________________

______________________________________________

2. በዚህ ምዕራፍ በራእይ መጽሐፍ ከቀረበው የመጨረሻው ዘመን ክስተቶች ጋር ተወራራሽነት ያላቸው ምን ዓይነት ክስተቶችን እናገኛለን? **ራእ.** 13:4፣ 8፣ 11–17፡፡

______________________________________________

______________________________________________

3. እስቲ ራስዎን ዳንኤል ይገኝበት በነበረው ሁናቴ ውስጥ ያኑሩ፡፡ ላለመጸለይ ምን ዓይነት ምክንያት ወይም የመከራከሪያ ሃሳብ ማቅረብ ይችል ነበር? ማለትም ያደረገውን ነገር ላለማድረግ እንዴት አድርጎ የማስመሰያ ነጥብ አንስቶ ራሱን ከአናብስት ጉድጓድ መታደግ ይችል ነበር?

______________________________________________

______________________________________________

4. ዳንኤል ያን ያህል መጸለይ ባያስፈልገውም እርሱ ግን እንደ ሁል ጊዜው መጸለዩን የቀጠለው ለምን ይመስሎታል?

______________________________________________

______________________________________________

5. ዳንኤል ወደ አንበሶች ጉድጓድ ከመጣሉ አስቀድሞም ቢሆን ስለ እርሱ አምላክ አንዳች የሚያውቀው ነገር እንደ ነበር በሚገልጥ መልኩ ንጉሥ ዳርዮስ ምን አለ (ዳን. 6፡16)፡፡ ዳንኤል ያመልከውና ያገለግለው ስለነበረው አምላክ አስመልክቶ

የራሱን ምስክርነት ፍንትው አድርገው የሚያሳዩ ምን ዓይነት ቃላቶች ተጠቀመ?

## አርብ ሚያዝያ 5

**ተጨማሪ ሃሳብ፡** “ወደ ዓለም ታሪክ መቋጫ እየተቃረብን ስንመጣ በትንቢተ ዳንኤል የቀረቡት ትንቢቶች እየኖርን ካለንበት ዘመን ጋር ካላቸው መስተጋብር አኳያ የተለየ ትኩረት ይጠይቃሉ፡፡ ከአዲስ ኪዳን መጻሕፍት መሃል የመጨረሻው መጽሐፍ ከእነዚህ ትንቢቶች ጋር ትስስር ሊፈጥር የተገባ ነው፡፡ ሰይጣን የዳንኤል እና የዮሐንስ ራእይ ትንቢታዊ መጻሕፍት ሊስተዋሉ የማይችሉ ናቸው በማለት ብዙዎችን አስቶአል፡፡ ነገር ግን እነዚህን መጻሕፍት የሚያጠኑ ልዩ በረከት እንደሚያገኙ ግልጽ የሆነ አምላካዊ ቃል ተሰጥቶአል፡፡ “ጠቢባን ግን ያስተውላሉ” (ዳን. 12፡10) በሚል በትንቢተ ዳንኤል የተነገሩት ቃላት ታትሞ የነበረው የመጽሐፉ ቃል በዚህ  የመጨረሻ ዘመን መከፈቱን ያመለክታሉ፡፡ በዘመናት ለእግዚአብሔር ሕዝቦች ምሪት ይሆን ዘንድ ክርስቶስ እንዲህ ሲል ለአገልጋዩ ዮሐንስ ገልጦለታል ‘ዘመኑ ቀርቦአል፤ እንግዲህ ይህን የትንቢት ቃል የሚያነብ ብፁዕ ነው፤ የሚሰሙትና የተጻፈውንም የሚጠብቁ ብፁአን ናቸው’ ራእ. 1:3”—Ellen G. White, *Prophets and Kings,* p. 547, 548.

ምንም እንኳ የዳንኤልን መጽሐፍ ከመንግሥታት መነሳትና መውደቅ፣ ከፍርድ (ዳን. 7፡22፣ 26፣ 8፡14) እና በታላቁ የመከራ ጊዜ ገቢራዊ ከሚሆነው የእግዚአብሔር ሕዝቦች መዳን አኳያ አብልጠን ብንመለከተውም (ዳን. 12፡1)፤ በዚህ ሣምንት ጥናታችን--ሊመጣ ላለው ፈተና እና ስደት በግል መዘጋጀት ምን ማለት እንደሆነ መጽሐፉ ሊሰጠን የሚችለውን ምሳሌ ተመልክተናል፡፡ ታሪኮቹ በዚህ መልኩ ለመጨረሻው ዘመን ገጣሚነት ያላቸውን አንገብጋቢ መልእክቶች

ይሰጡናል፡፡ “የአውሬው ምልክት”፣ አስጨናቂው “የመከራ ጊዜ” እና ስደትን አስመልክቶ አንዳንድ ነጥቦችን መመልከቱና ማወቁ ጠቃሚ ነው፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ሊኖረን የሚገባውንና በእጅጉ አስፈላጊያችን የሆነውን የግንኙነት ተሞክሮ ከወዲሁ መመስረት ካልቻልን ይህ ሁሉ ዕውቀት እኛን ከመኮነን ውጪ ሌላ የሚፈይደው ነገር አይኖርም፡፡ ከማንኛውም ነገር በላይ ናቡከደነፆርን ጨምሮ ዳንኤልና ሌሎቹ የነበራቸው ዓይነት የ“ዳግመኛ መወለድ” ተሞክሮ ሊኖረን ይገባል፡፡

***የመወያያ ጥያቄዎች:***

1. በዳን. 9፡3-19 የቀረበውን የዳንኤል ጸሎት ያንብቡ፡፡ እግዚአብሔር ከርኅራኄው የተነሳ የሚወደንና የሚዋጀን አምላክ እንደመሆኑ ከማንኛውም በመልካም ሥራም ሆነ በበጎነት ጽድቅ አገኛለሁ ከሚል እሳቤ በተቃራኒ ዳንኤል አምላካዊውን ጸጋ ማስተዋሉን ይህ ጸሎቱ እንዴት ያሳየናል? ይህ እውነት ለማስተዋል ሳይሆን ለመለማመድ በእጅጉ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?

2. በሰንበት ትምህርት ጥናትና ውይይታችሁ የፖለቲካ ባለሥልጣናት ሦስቱ ዕብራውያን (ዳን. 3) እና ዳንኤል (ዳን. 6) ለኃይማኖታዊ እሴቶቻቸው በጽናት እንዳይቆሙ በፈጠሩባቸው ተግዳሮቶች ዙሪያ ተወያዩ፡፡ ከላይ በቀረቡት በሁለቱ ሃሳቦች መሃል ምን ዓይነት መመሳሰል ያገኛሉ? ልዩነትስ? ታማኝነታችን እንዴት ብርቱ ምስክሮች ሊያደርገን እንደሚችል አስመልክቶ ከእነዚህ ሁለት ነጥቦች ምን መማር እንችላለን?

# ስስተኛ ትምህርት ከሚያዝያ 6 – 12

## የሱስ እና የራዕይ መጽሐፍ

### ሰንበት ከሰዓት

***ለዚህ ሳምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡*** *1ቆሮ. 10:1–11፤ ራእ. 12:1–17፤ 19:11–15፤ ኤፌ. 1:20፤ ራእ. 11:19፤ 1:10–18፡፡*

**የመታሰቢያ ጥቅስ:**

"እኔ ድል ነሥቼ ከአባቴ ጋር በእርሱ ዙፋን ላይ እንደ ተቀመጥሁ፣ ድል የሚነሳውንም ከእኔ ጋር ዙፋኔ ላይ እንዲቀመጥ አደርገዋለሁ።" (ራእ. 3፡21)። "

አዲስ ኪዳንን ላይ ላዩን በፍጥነት እንኳ ብናነብ አንድ አስፈላጊ እውነት ይገልጥልናል፤ አዎ አዲስ ኪዳን ከብሉይ ኪዳን ጋር ቀጥተኛ ትስስር አለው፡፡ ወንጌል እና በደብዳቤ መልክ የቀረቡት የአዲስ ኪዳን መልእክቶች የብሉይ ኪዳንን ታሪኮች በቀጥተኛ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ በማመሳከሪያነት ጥቅም ላይ ሲያውሉ ይስተዋላሉ፡፡ የሱስ ከራሱና ከአገልግሎቱ ጋር እያነጻጸረ ስለ ብሉይ ኪዳን ትንቢቶችን ፍጻሜ ማግኘት ስንት ጊዜ ተናግሯል (ማቴ. 26:54፣ 56፣ ማር. 14:49፣ ዮሐ. 13:18፣ 17:12)?

ለዮሐንስ ራእይ መጽሐፍም እንዲሁ ከዚህ ተመሳሳይ ሊባል ይችላል፡፡ በእርግጥ የራዕይን መጽሐፍ ከብሉይ ኪዳን በተለይም ከዳንኤል መጽሐፍ መነጠል መልእክቱ ትርጉም እንዲያጣ ያደርገዋል፡፡ ሁለቱን መጻሕፍት በተናጥል ሳይሆን በአንድነት የምናጠናበት አንዱ ምክንያት ይኸው ነው፡፡

በራእይ መጽሐፍ የምናገኛቸው አበይት ገጽታ የተላበሱ የብሉይ ኪዳን ማጣቀሻዎች ከቀሪው የመጽሐፉ አካል ጋር በመሆን የሱስን ገልጠው ያሳያሉ፡፡ መላው የራእይ መጽሐፍ ገጾች ስለ የሱስ ይኸውም ስለ ማንነቱ፣ ለሕዝቡ ስለከፈለው ውለታ እንዲሁም በመጨረሻው ጊዜ ስለሚያደርግልን ነገር ይነግረናል፡፡ ማንኛውም በመጨረሻው ጊዜያቶች ላይ የሚደረግ ትኩረት በራእይ መጽሐፍ በትክክል እንደቀረበው የሱስን የጉዳዩ ፊትና ማዕከል ማድረጉ የግድ ይሆናል፡፡ የዚህ ሣምንት ትምህርት በራእይ መጽሐፍ የሱስ ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡

## እሑድ ሚያዝያ 7

## የራእይ መጽሐፍ አወቃቀር

የዳንኤልና የራእይ መጽሐፍ በጋራ ከያዟቸው በርካታ ነገሮች መሃል ሁለቱ ክፍሎች ማለትም ታሪክን መሰረት ያደረገው አቀራረብ እና የመጨረሻው ጊዜ ክስተቶች በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ እነዚህ ሁለቱም ጽንሰ ሃሳቦች የተወሳሰበ ተፈጥሮ ይዘው፤ ነገር ግን እርስ በርስ ተሳስረው በሁለቱም መጻሕፍት ይገኛሉ፡፡ ምንም እንኳ በመጨረሻው ጊዜ ገቢራዊ ከሚሆኑት ታላላቅ ክስተቶች አኳያ በአነስተኛ መጠን ቢቀርቡም፤ ታሪካዊዎቹን ክስተቶች እንደ ግንባር ቀደሞች ወይም ምሳሌዎች አድርገን ልንመለከታቸው እንችላለን፡፡ ቀደም ብሎ በብሉይ ኪዳን ታሪክ ተከስተው የነበሩ ነገሮችን በማጥናት በእኛ ዘመንና ባሻገር በሚኖረው ሁናቴ ላይ ብርሃን ማግኘት እንችላለን፡፡ የሆነው ሆኖ ይህ መርኅ በዳንኤል እና በራእይ መጽሐፎች ብቻ የተወሰነ አይደለም፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ 1ቆሮ. 10፡ 1-11፡፡ ከላይ የተነጋገርንባቸውን መርኅዎች በእነዚህ ቁጥሮች እንዴት እንመለከታቸዋለን?**

ባለፈው ሣምንት ጥናታችን በዳንኤል መጽሐፍ (ዳን. 3:6፣ 15፣ 27፣ 6:6–9፣ 21-22) ከተመለከትናቸው ታሪኮች ውስጥ አንዳንዶቹ ዓለማቀፋዊ አንደምታ ባይኖራቸውም ነገር ግን በተወሰነ ደረጃ በራእይ መጽሐፍ የተገለጹትን የመጨረሻውን ጊዜ ክስተቶች ያንጸባርቃሉ፡፡ እነዚህን ታሪኮች በማጥናት በመጨረሻ ላይ የእግዚአብሔር ሕዝቦች በስፋት ከሚጋፈጧቸው ነገሮች መሃል የአንዳንዶቹን ውጪያዊና ውስጣዊ ሁኔታ እንመለከታለን፡፡ ዛሬ የምንገኝበት ሁናቴ ምንም ይሁን ምን ምናልባት በጣም አስፈላጊው ነጥብ በመጨረሻ የድነት ባለቤት ስለ መሆናችን የተሰጠን ማረጋገጫ ነው፡፡ የራእይ መጽሐፍ የቱንም ዓይነት ተጨማሪ ትምህርት ቢያስተምር፤ ለታማኙ ባለ ድልነት ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡

የዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ ሁለት ክፍሎች ያሉት ሲሆን እነርሱም ከምዕ. 1-11--ታሪክ ነክ፤ ከምዕ. 13-22 ደግሞ የመጨረሻው ጊዜ መልእክቶች ናቸው፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 12፡1-17፡፡ ይህን ምዕራፍ የት ላይ እንመድበው--ታሪክ ነክ ወይስ የመጨረሻው ጊዜ ክስተት--ለምን?**

እንደምንመለከተው ይህ ምዕራፍ ከሁለቱም ክፍሎች ይመደባል፡፡ ለምን? ምክንያቱም ስለ ታሪካዊ ሁነቶች ስለሚያወራ--ስለ ሰይጣን ከሰማይ መባረር (ራእ. 12፡7-9)፣ ሰይጣን በህፃኑ የሱስ ላይ ሊፈጽም ስለነበረው ጥቃት (ራእ. 12፡14)፣ እንዲሁም ተከታታይነት ስለ ነበረው የቤተክርስቲያን ስደት ታሪክ (ራእ. 12፡14-16) ከተናገረ በኋላ በመጨረሻው ጊዜ በትሩፋኗ (ቅሬታዋ) ቤተ ክርስቲያን ላይ ዲያብሎስ ስለሚሰነዝረው ጥቃት ይገልጻል (ራእ. 12፡17)፡፡

ከታሪክ ከምንማራቸው ትምህርቶች አንዱ፤ ከታሪክ ፈጽሞ አለመማራችን ነው--የሚል አባባል አለ፡፡ ሀሳቡ--ምንም ያህል ቢሆን ሰዎች ተመሳሳይ ስህተቶችን መሥራታቸውን ይቀጥላሉ የሚል አንደምታ አለው፡፡ ትምህርት ልንቀስምበት የሚያስችለን የታሪክ ክምችት ከበስተኋላችን እያለልን ተመሳሳይ ስህተቶችን ማስወገድ የምንችለው እንዴት ነው?

# ሰኞ ሚያዝያ 8

## የየሱስ ምስሎች

የየሱስን የተለያዩ ስሞች የያዙትን የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡፡ ስሞቹ እርሱ ስላደረገው፣ እያደረገ ስላለው ወይም ስለሚያደርገው ነገር እርሱን ይገልጣሉ፡፡ ጥቅሶቹ ስለ የሱስ ምን ያስተምሩናል?

ራእ. 1:5________________________________________________

ራእ. 1:18_______________________________________________

ራእ. 5:8________________________________________________

ራእ. 19:11–15___________________________________________

ራእ. 21:6_______________________________________________

በራእይ መጽሐፍ የሱስን በተለያዩ ሚናዎች እና ተግባራት ከሚገልጹ በርካታ ጥቅሶች መካከል እነዚህ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ እርሱ ራሱን የኃጢአት መሥዋዕት አድርጎ ስላቀረበበት የመጀመሪያው ምጽአቱ ለመጠቆም እንደ በግ ተጠቅሶአል፡ “አሁን ያለ እርሾ እንደሆናችሁ ሁሉ አዲስ ሊጥ እንድትሆኑ አሮጌውን እርሾ አስወግዱ፤ የፋሲካ በጋችን የሆነው ክርስቶስ ተሰውቶአልና” (1ቆሮ. 5፡7)፡፡ እንዲሁም “እኔ ሕያው ነኝ፤ ሞቼ ነበር፤ እነሆ አሁን ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ነኝ” (ራእ. 1፡18) በማለት ስለ ሞቱና ትንሳኤው ግልጽ ማመሳከሪያ ይሰጠናል፡፡ “እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል፤ ክርስቶስ መከራን ይቀበላል፤ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ይነሳል” (ሉቃ. 24፡46)፡፡ እንዲሁም በራእ. 19፡11-15 በታላቅ ኃይል፣ ግርማ እና ፍርድ ወደ ምድር ሲመለስ በዳግም ምጽአቱ ከሚኖረው

ሚና አኳያ ተገልጾአል፡፡ "'የሰው ልጅ በአባቱ ክብር ከመላእክት ጋር ይመጣል፤ ለእያንዳንዱም ሰው እንደ ሥራው ዋጋውን ይከፍለዋል' " (ማቴ. 16:27) ሕይወትን፣ ሞትን፣ ትንሳኤን እና የየሱስን ዳግም ምጽአት የህልውናችን ማዕከላዊ ክፍል እና የግብረገባዊ ምርጫችን መሰረት እያደረግን በየዕለት ሕይወታችን መማር የምንችለው እንዴት ነው?

## ማክሰኞ ሚያዝያ 9

## በራእይ መጽሐፍ የቀረበው የቤተ መቅደሱ ንድፍ

በራእይ መጽሐፍ የቀረበው መቅደስ ከዕብራውያኑ ሁለቱ ዐቢይ ክፍሎች በተጨማሪ በመቅደሱ ዙሪያ የተገነባ ሌላ ቅጥር አለው፡፡ ይህ ክፍል በሁለቱ ዋና ዋና ክፍሎች ዙሪያ ከማለፍ ውጪ በአንዳቸውም አይገድብም፡፡

ምድራዊው ቤተ መቅደስ ለኃጢአት ሥርየት የመጣው እንስሳ ታርዶ የሚቃጠል መሥዋዕት በሚቀርብበትና መሠዊያው በሚገኝበት ቅጥር ይጀምራል፡፡ እንስሳው ታርዶ ከሞተ በኋላ ካኅኑ ወደ መጀመሪያው የመቅደሱ ቅጥር ይገባል ይኸውም በመስቀሉ ተምሳሌት መሰረት የሱስ ከእርገቱ በኋላ ወደ ሰማያዊው መቅደስ በመግባት የተወው ምሳሌ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ የሱስ በመቅረዞቹ መካከል መራመዱን ያመለክታል (ራእ. 1፡13)፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 4፡1-2፡፡ የተከፈተው በር ምን ይወክላል? ይህ ትዕይንት የሚገኘው የት ነው? ሐዋ. 2:33፣ 5:31፣ ኤፌ. 1:20፣ ዕብ. 10:12-13፣ መዝ. 110:1፣ ራእ. 12:5፡፡

---

ክርስቶስ በዚህ ለመጀመሪያ ጊዜ በተከፈተ በር ወደ ሰማይ እንዳረገ በሰማያዊው መቅደስ ቅዱስ ክፍል ከበረ፡፡ ክርስቶስ ለመጀመሪያ ጊዜ በራእይ መጽሐፍ የታየው በሰማያዊው መቅደስ የመጀመሪያው ክፍል ከመቅረዙ ፊት ቆሞ ነው (ራእ. 1፡10-18)

፡፡

ጥቅሱን ያንብቡ፡ ራእ. 11፡19፡፡ በሰማይ ያለው ቤተ መቅደስ ሲከፈት ዮሐንስ ልክ በምድራዊው ሁለተኛ ክፍል የተቀመጠ የሚመስለውን--የኪዳኑን ታቦት ማየት የቻለበት እውነታ አንደምታው ምንድን ነው? (ዘሌዋ. 16፡12-14)

---

---

በሰማያዊው ቤተ መቅደስ ውስጥ የሚስተዋለው የኪዳኑ ታቦት ምስል ለቅድስተ ቅዱሳኑ ወይም ለሰማያዊው መቅደስ ሁለተኛው ክፍል የማያጠራጥር ማስረጃ ነው፡፡ በራእይ መጽሐፍ መመልከት የምንችለው የየሱስን የሁለቱን ክፍሎች አገልግሎት ብቻ አይደለም፡፡ ይልቁንም በሰማይ እና በምድር ያሉ ክስተቶች የመተሳሰራቸውን ወሳኝና አጽናኝ ነጥብ እንመለከታለን፡፡ የክርስትና ታሪክ መከራ የበዛበት--የመጨረሻው ጊዜ ክስተቶችም በራእይ መጽሐፍ እንደተገለጹት ቢሆንም "መላው ሰማይ ሕዝቡ ለጌታ ቀን እንዲዘጋጅ በማድረግ ሥራ መጠመዱ እና በሰማይና በምድር ያለው ግንኙነት በጣም የተሳሰረ መምሰሉ" ለእኛ መልካም ተስፋ ነው፡፡ —Ellen G. White, *My Life Today*, p. 307.

ረቡዕ ሚያዝያ 10

## ክርስቶስ በራእይ መጽሐፍ፡ ክፍል አንድ

የራእይ መጽሐፍ ከመልእክት አወቃቀሩ እስከ ይዘቱ አንድ ብቻ ዓላማ አለው፡ የሱስ ክርስቶስን መግለጥ፡፡

በዚህ የተነሳ መጽሐፉ የሚጀምርባቸው ቃላት "የኢየሱስ ክርስቶስ ራእይ" የሚሉ ናቸው፡፡ ይኸውም በአጠቃላይ "የኢየሱስ ክርስቶስ ራእይ" ወይም "ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ" (ራእ. 1፡2) በሚል ይስተዋላል፡፡ የመልእክቱ በ "ራእይ" መልክ መሰጠት የራእይ መጽሐፍን ለማስተዋል በጣም ከባድ አድርገው የሚያምኑትን

ይሞግታል፡፡ ጌታ መጽሐፉን በሚያነቡት እንዲስተዋል እቅዱ ባይሆን'ማ ለምን የመጽሐፍ ቅዱስ አካል ያደርገው ነበር?

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ 1፡1-8፡፡ ጥቅሶቹ ስለ የሱስ ምን ያስተምሩናል?**

---

---

በራእይ መጽሐፍ ክርስቶስ "የምድር ነገሥታት ገዥ" (ራእ. 1፡5) በሚል የቀረበ ሲሆን በዚሁ መጽሐፍ መጨረሻ አካባቢ ደግሞ "የነገሥታት ንጉሥ" (ራእ. 19፡16) የሚል ስያሜ ተሰጥቶት እንመለከታለን፡፡ ምድር ምስቅልቅሏ ቢወጣና ግራ ብትጋባም ነገር ግን ሁሉም ነገር እስከ መጨረሻው በሚወደን ጌታና አዳኛችን ቁጥጥር ሥር የመሆኑ ማረጋገጫ ለእኛ ታላቅ የምስራች ነው፡፡

በራእ. 1፡5 ክርስቶስ ቤዛችን ለመሆኑ ግልጽ ማጣቀሻ ተሰጥቶናል፡፡ "ለወደደንና ከኃጢአታችንም በደሙ ነፃ ላወጣን" የሚለው ሀረግ ለዓለም ቤዛ የሆነበትን የመስቀል ላይ ሞቱን ያመለክታል፡፡ እኛን ማጽደቅ ብቻ ሳይሆን ቀድሶናልም (1ቆሮ. 6፡11)፡፡ ኃጢአታችንን በብቸኝነት የሚያጥበው የሱስ መሆኑን በብቸኝነት በሚያሳዩን በእንደነዚህ ዓይነቶቹ ጥቅሶች የደኅንነት ማረጋገጫ ማግኘት እንችላለን፡፡ በእርግጥ እኛ በራሳችን ይህን ለማድረግ የማይታሰብ ነው፡፡

**ጥቅሱን ያንብቡ፡--ራእ. 1፡7፡፡ መልእክቱ ስለ የሱስ ምን ያስተምረናል?**

---

---

የክርስቶስ "በደመና መገለጥ" ዳግም ምጽአት ተስፋ የሁሉም የክርስትና እምነት ተቋማት ማዕከላዊ ክፍል ነው፡፡ የሱስ ዳግም በሚገለጥበት ጊዜ ዐይን ሁሉ ያየዋል፡፡ የዳግም ምጽአቱ ክስተት ማንኛውንም የዚህን ዓለም ሥቃይ፣ ምስቅልቅልና ውድመት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንዲያከትም በማድረግ ሁሉንም ዘላለማዊ ተስፋዎች ይዞ ከተፍ ይላል፡፡

ራእ. 1፡8 ስለ የሱስ ምን ያስተምረናል? ምንም ዓይነት አስቸጋሪ ሁኔታ እየተጋፈጥን ቢሆንም በዚህ ሁኔታችን መጽናናት ሊሰጠን የሚችል ምን ዓይነት ተስፋ በጥቅሱ ማግኘት እንችላለን?

## ሐሙስ ሚያዝያ 11

## ክርስቶስ በራእይ መጽሐፍ፡ ክፍል ሁለት

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 1፡10-18፡፡ **የሱስ ስለ ራሱ ምን ይላል?**

---

ከጥቅሶቹ እንደምንመለከተው የሱስ በሰማያዊው መቅደስ የመጀመሪያ ክፍል ቆሞአል፡፡ የሱስ በዚህ ስፍራ ከነበረው ሚና አኳያ የተገለጠበት ራእይ እጅግ ብርቱ በመሆኑ ዮሐንስ በፍርሐት እግሮቹ ስር ወደቀ፡፡ ነገር ግን ሁሌም አጽናኝ የሆነው የሱስ--ለዘላለማዊ አምላክነቱ ማጣቀሻ አልፋ እና ኦሜጋ ወይም የመጀመሪያውም ሆነ የመጨረሻው እርሱ መሆኑን በማመላከት እንዳይፈራ ሲነግረው ይታይል፡፡ በመቀጠል ስለ ሞቱ፣ ስለ ትንሣኤው--ብሎም ትንሣኤው ስላስገኘው ተስፋ ይናገራል፡፡ የሱስ "የሞትና የሲኦል" መክፈቻ በእጁ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር ማርታና ማርያም ወንድማቸው አልዓዛር በሞተ ጊዜ የነገራቸውን መልሶ በዚህ ቦታ ለዮሐንስ እየነገረው ነበር፡፡ ዮሐንስ ይህንኑ ጉዳይ እንዲህ ሲል በወንጌል አስፍሮት ነበር "'ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፤ በእኔ የሚያምን ቢሞት እንኳ በሕይወት ይኖራል፤ በእኔ የሚኖር፣ የሚያምንብኝም ከቶ አይሞትም፤ ይህን ታምኛለሽ?' " (ዮሐ. 11፡25-26)፡፡

የሱስ ቀደም ሲል በማርታ አሁን ደግሞ በዮሐንስ አማካይነት የክርስትና እምነት መደምደሚያና ከፍታ ወደ ሆነው የትንሣኤው ተስፋ ያመላክተናል፡፡ ይህ ተስፋ ባይኖር ምን ይበጀን ነበር?

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 22፡7፣12-13፡፡ በተጨማሪ ጥቅሶቹ ስለ የሱስ ምን ይገልጣሉ?**

---

“የብሉይ ኪዳን ዘፍጥረት እና የአዲስ ኪዳን ራእይ የሆነው ክርስቶስ የሱስ አልፋ እና ኦሜጋ ነው፡፡ ሁለቱም በክርስቶስ በአንድነት ይገናኛሉ፡፡ ሁለተኛው አዳም የሰይጣንን ፈተና አሸንፎ ለመጀመሪያው አዳም አሳፋሪ ውድቀትና ጥፋት ቤዛ በመሆኑ፤ በሁለተኛው አዳም መታዘዝ የመጀመሪያው አዳም እና እግዚአብሔር እርቅ ፈጠሩ፡፡”— Ellen G. White Comments, *The SDA Bible Commentary*, vol. 6, pp. 1092, 1093. አዎ የሱስ የመጀመሪያው እና የመጨረሻው ነው፡፡ እርሱ በመጀመሪያ እንደ ፈጠረን፤ በመጨረሻም እንዲሁ ይፈጥረናል፡፡

ገና ከመጀመሪያው፤ ያለፈውን ታሪክ ብቻ ሳይሆን ነገር ግን የወደፊቱን የምድር ፍጻሜ የሚያስተምረን የራእይ መጽሐፍ እነሆ ዛሬም የየሱስ ክርስቶስ ራእይ ነው፡፡ ስለ መጪው ጊዜ ክስተቶች የቱንም ዓይነት ጥናት ብናካሂድ የሱስ ክርስቶስ የሁሉም ነገር ማዕከል መሆኑን አንዘንጋ፡፡

**የሱስን በየቀኑ የሕይወታችን ማዕከል አድርገን መጠበቅ የምንችልባቸው መንገዶች የትኞቹ ናቸው?**

## አርብ ሚያዝያ 12

**ተጨማሪ ሀሳብ፡** “በራእይ መጽሐፍ ጥልቀት ያላቸው አምላካዊ ነገሮች ተገልጸዋል፡፡ ‘ራእይ’ በሚል ለመጽሐፉ የተሰጠው ስያሜ መጽሐፉ የተዘጋ ነው የሚለውን አባባል ይጣረሳል፡፡ ራእይ--የተገለጠ የሚል ፍቺ አለው፡፡ የመጽሐፉን ምስጢር ለአገልጋዩ የገለጠው ጌታ ራሱ እንደመሆኑ ሁሉም እንዲያጠኗቸው ክፍት አድርጎ ነድፎአቸዋል፡፡ መጽሐፉ የያዛቸው እውነቶች የተጻፉት ዮሐንስ ለኖረበት ዘመን ብሎም በምድር ታሪክ መዝጊያ ለሚኖሩ ወገኖች ነው፡፡ በዚህ ትንቢት ከተገለጹት ትዕይንቶች መካከል አንዳንዶቹ ቀደም ባሉት ዘመናት ፍጻሜ ሲያገኙ የተወሰኑት

ደግሞ አሁን ባለንበት ዘመን በመፈጸም ላይ ይገኛሉ፡፡ አንዳንዶቹ በጨለማ ኃይላት እና በሰማይ ልዑል መካከል ሲካሄድ የኖረው ታላቁ ውዝግብ ሊቋጭ መቃረቡን ሲያሳዩ--ሌሎቹ ደግሞ በአዲሲቱ ምድር የተቤዡ አሸናፊዎችን ሐሴትና ደስታ ይገልጻሉ፡፡”—Ellen G. White, *The Acts of the Apostles*, p. 584.

በዚህ ሣምንት በመጽሐፉ መግቢያም ሆነ መጨረሻ የተመለከትናቸው ጥቅሶች ምን ያህሉ የራእይ መጽሐፍ ስለ የሱስ እንደሚናገር ያሳያሉ፡፡ የራእይ መጽሐፍ ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እስከ ታሪክ ቀመስ ክስተቶች ያሉ ማመሳከሪያዎችን በመዳሰስ ስለ ጌታችን የሱስ ክርስቶስ አብልጦ ያስተምረናል፡፡ በተጨማሪ እነዚህን ጥቅሶች ይመልከቱ፡ ራእ. 3:14፣ 5:5-6፣ 7:14፣ 19:11–16፡፡ ጥቅሶቹን በአንድነት በማኖር ለየሱስ ያላቸውን ብርቱ ውክልና ማግኘት እንችላለን፡፡

## የመወያያ ጥያቄዎች፡

1. በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ስለ ብሉይ ኪዳን የተሰጡ ጽኑና የማያቋርጡ ማመሳከሪያዎች ለእኛ ምን ማለት ናቸው? አምላካዊው ቃል የእምነታችን ማዕከልና ብርቱ አጽንኦት ልንሰጠው የተገባ ስለመሆኑ ምን ሊነግረን ይገባል? በግል ህይወታችን እና በቤተክርስቲያን ህይወት የመጽሐፍ ቅዱስን ሥልጣን ለማቃለል የሚደረጉ ማናቸውንም ዓይነት ጥረቶች መከላከል የምንችለው እንዴት ነው?
2. በራእይ መጽሐፍ በተለይ ስለ የሱስ የሚናገሩ ጥቅሶችን ለመሰብሰብ ይሞክሩ፡፡ ጥቅሶቹን በሰንበት ትምህርት ጥናት ያቅርቧቸው፡፡ ስለ ጌታ ተፈጥሮ፣ ሥራ፣ ኃይልና ባህሪ በተጨማሪ ምን ይገልጡሎታል? ጥቅሶቹ ከሚገልጡት እውነታ ምን ዓይነት መጽናናት ያገኛሉ?
3. በዚህ በሞት ዓለም--ለሙታን ከተሰጠው የትንሣዔ ተስፋ ውስጥ--ተስፋን ማግኘት መማር የምንችለው እንዴት ነው?

# አራተኛ ትምህርት

ከሚያዝያ 13 – 19

## ደኅንነት እና የመጨረሻው ጊዜ

**ሰንበት ከሰዓት**

***ለዚህ ሳምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ የሐ.*** *14:9፣ ሶፎን. 3:17፣ የሐ. 1:1–3፣ ሮሜ 8:38-39፣ መዝ. 91:15-16፣ ራእ. 14:6-7፣ ኤፌ. 1:4-5፡፡*

**የሳምንቱ ጥናት መሪ ጥቅስ፡-**

**"ፍቅር ይህ ነው፤ እኛ እግዚአብሔርን እንደ ወደድነው ሳይሆን እርሱ እንደ ወደደንና ስለ ኃጢአታችን ማስተሰሪያ ይሆን ዘንድ ልጁን መላኩ ነው።" (1ዮሐ. 4፡10)።**

በክርስትና እና ከክርስትና ውጪ በሚገኙ እምነቶች መካከል አንድ አስደናቂ--ደግሞም መሰረታዊ ልዩነት አለ፡፡ ከክርስትና ውጪ ያሉ ቤተ እምነት ተከታዮች መሥራቾቻቸው ላስተማሯቸው ትምህርቶች እንጂ ስላደረጉላቸው ነገር አጽንኦት አይሰጡም፡፡ ይህ የሆነው መሥራቾቻቸው ምንም ቢያደርጉላቸው ሊያድናቸው ስለማይችል ነው፡፡ እነዚህ መሪዎች ሊያደርጉ ይችሉ የነበረው ሕዝቡ እንዴት ራሱን ማዳን እንዳለበት ለማስተማር መሞከር ብቻ ነበር፡፡

በተቃራኒው የክርስትና እምነት አጽንኦት የሚሰጠው የሱስ ስላስተማረው ነገር ብቻ ሳይሆን ስላደረገውም ጭምር ነው፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ክርስቶስ ያደረገው ነገር ብቸኛው የመዳናችን መንስኤ በመሆኑ ነው፡፡ የክርስቶስ ሰብዓዊውን ሥጋ መልበስ (ሮሜ 8፡3)፣ የመስቀል ላይ ሞቱ (ሮሜ 5፡8)፣ ትንሣኤው (1ጴጥ. 1፡3)፣ ሰማያዊ አገልግሎቱ (ዕብ. 7፡25)--እነዚህ ብቻቸውን

የመዳናችን መንስኤ ናቸው፡፡ ከዚህ ውጪ ከእኛ ውስጥ አንዳችም የለም፡፡ “ከሰው ልጆች ወስጥ መልካም መልካሙ፣ ቅዱስ የሆነው፣ የከበረና የተወደ የተባለው ማንኛውም ነገር በአንድ ላይ ተሰብስቦ ለሰብዓዊው ፍጡር መዳን እንደ ድርሻ ይቆጠር ዘንድ ለእግዚአብሔር መላእክት ቢበረከት--እቅዱ በእግዚአብሔር መንግሥት ላይ እንደተደረገ ብርቱ ክህደት ተቆጥሮ ተቃውሞ ይገጥመዋል፡፡”—Ellen G. White, *Faith and Works,* p. 24.

ይህ አስደናቂ እውነት በተለይ በአስጊ ሁናቴዎች እና ማታለያዎች ለተከበብነው ለእኛ ለመጨረሻው ጊዜ ሕዝቦች በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

## እሑድ ሚያዝያ 14

## የአብ ፍቅር

የሱስ በመስቀል ላይ መሥዋዕት ከመሆኑ ጥቂት ቀደም ባሉት ቀናት ሰዎች እንዴት በእርሱ በኩል ወደ አብ እንደሚመጡ እጅግ ቅርቡ ከነበሩ ወገኖች ጋር ይነጋገር ነበር፡፡ ታዲያ በመሃል ፊልጶስ “ ‘ጌታ ሆይ፤ አብን አሳየንና ይበቃናል’ ” አለው (ዮሐ. 14፡8)፡፡

**የሱስ ለፊልጶስ ምን ዓይነት ምላሽ ሰጠው? እርሱ የሰጠው መልስ ስለ አብ ምን ያስተምረናል? የተዛባውን አመለካከትስ እንዴት ያጠራል?**

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

አንዳንዶች ሲናገሩ እንደሚደመጠው--የብሉይ ኪዳኑ እግዚአብሔር የፍትሕና ርትዕ አምላክ፡ የአዲስ ኪዳኑ ደግሞ የምህረት፣ የጸጋና የይቅርታ ጌታ ነው-- ይላሉ ሁለቱን በማነጻጸር፡፡ ሆኖም በሁለቱ መጽሐፎች መካከል የሚያስቀምጧቸው እነዚህ ልዩነቶች ህጋዊም ተገቢም አይደሉም፡፡

በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት የምናገኘው እግዚአብሔር አንድ ዓይነት ባህሪ የተላበሰ ያው አምላክ ነው፡፡

ክርስቶስ ወደዚህ ምድር የመጣበት አንዱ ምክንያት የእግዚአብሔር አብን እውነተኛ ማንነት ለመግለጥ ነበር፡፡ ለአያሌ መቶ ዓመታት ስለ እርሱ ብሎም ስለ ባህሪው የተሳሳቱ ጽንሰ ሀሳቦች ሲነገሩና ሲሰራጩ ኖረዋል፡፡ ይህ የሆነው እርሱን በማያውቁ አረማውያን ሳይሆን በራሳቸው በተመረጡ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ነበር፡፡ “ምድር እግዚአብሔርን በተሳሳተ መንገድ በማስተዋሏ በድቅድቅ ጨለማ ተውጣ ነበር፡፡ ድቅድቁን ጨለማ ለመግፈፍ እና ዓለምን ዳግመኛ ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ--የሰይጣን አሳች ኃይል መሰበር ነበረበት፡፡”—Ellen G. White, *The Desire of Ages,* p. 22. የሱስ ወደዚህ ምድር ከመጣባቸው ምክንያቶች አንዱ ይህ ነበር፡፡

እግዚአብሔር አይለወጥም፡፡ የብሉይ ኪዳንን ነባራዊ እውነታዎች በሚገባ ከተገነዘብን በመጻሕፍቱ ውስጥ የምናገኘውን በምህረት የተሞላ አምላክ በአዲስ ኪዳንም እናገኘዋለን፡፡ “እግዚአብሔር ፍቅር ነው” (1ዮሐ. 4፡8) እርሱ አይለወጥም፡፡ “ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንት፣ ዛሬም ለዘላምም ያው ነው” (ዕብ. 13፡8)፡፡

በቀራኒዮ መሥቀል ላይ የተቸነከረው የብሉይ ኪዳኑ እግዚአብሔር መሆኑን ጭምር ማስታወሱ ተገቢ ነው፡፡

ደግሞም ይህ አምላክ ቸር፣ ርኅሩኅ፣ ለቁጣ የዘገየ፣ ምሕረቱ የበዛ ነው (መዝ. 145፡8)፡፡ የእግዚአብሔር ፍቅር የሚተማመኑትና እርግጠኛ ነው (መዝ. 143፡8)፣ በምሕረቱ በሚታመኑ ደስ ይለዋል (መዝ. 147፡11)፣ እግዚአብሔር ፍጻሜው ያማረና ተስፋ የሚሰጥ ዕቅድ አለው (ኤር. 29፡11)፡፡ በፍቅር የተሞላው አምላክ ከሕዝቡ ጋር በዝማሬ ሐሴት ያደርጋል (ሶፎን. 3፡17)፡፡ እነዚህና አያሌ ሌሎች ጥቅሶች የእውነተኛውን አብ ማንነት ገልጠው ያሳያሉ፡፡

**የሱስ ክርስቶስ አብን ስለ መወከሉ እውነታ ያስቡ፡፡ ይህ በተለይ እግዚአብሔርን ለሚፈሩ አስደናቂና በተስፋ የሚሞላ እውነት መሆን የቻለው ለምንድን ነው?**

**ሰኞ ሚያዝያ 15**

**የክርስቶስ ፍቅር**

ኃጢአት ሰብዓዊውን ዘር ከእግዚአብሔር በመነጠሉ በሁለቱ መሀል ጥልቅ ገደል ተፈጠረ፡፡ ይህ ገደል መዘጋት ካልቻለ በቀር ሰብዓዊነት ለዘላለም ተኮንኖ የሚቀር ሆነ፡፡ ክፍተቱ ጥልቅና አደገኛ ነበር፡፡ ለኃጢአት ችግር መፍትሔ አምጥቶ ኃጢአተኛውን ሰብዓዊ ፍጡር ከጻድቁ እና ቅዱሱ አምላክ ጋር ዳግም ኅብረት እንዲፈጥር ለማድረግ እጅግ ለማመን የሚከብድ ተግባር ተጠየቀ፡፡ በመሆኑም ከራሱ እግዚአብሔር ጋር ዘላለማዊ የሆነውና መለኮታዊ ባህሪ ያለው አምላክ ሰብዓዊ ፍጡር እንዲሆን በመጠየቁ--በዚያ ሰብዓዊነት ራሱን ስለ ኃጢአታችን መሥዋዕት አድርጎ ሰጠ፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ዮሐ. 1፡1-3፣ 14፣ ፊልጵ. 2፡5-8፡፡ ስለ የሱስ ማንነት ምን ያስተምሩናል?**

---

---

---

ክርስቶስ ዘላለማዊ አምላክ እንደመሆኑ ሕልውናው በማንም ወይም በምንም ላይ ጥገኛ አይደለም፡፡ አምላክነቱ ውጪያዊና የታይታ ሳይሆን ነገር ግን እርሱ ራሱ እግዚአብሔር ነው፡፡ እርሱ በእጅጉ አስፈላጊ የሆነው መለኮታዊና ዘላለማዊ ተፈጥሮ ባለቤት ነው፡፡ የሱስ ይህን መለኮታዊ ተፈጥሮ እንደያዘ

የሚኖር አምላክ ቢሆንም እርሱ ግን አምላካዊውን ሕግ በሰብዓዊው ሥጋ ጠብቆ ሕጉን በጣሱት ምትክ ይኸውም ለእኛ ለሁላችን ለመሞት ሲል ሰብዓዊውን ሥጋ ለበሰ (ሮሜ 3፡23) ፡፡

ክርስቶስ ከማንኛውም ሰብዓዊ ፍጡር የተለየ ልዩ ጥቅም ወይም ብልጫ ሳይኖረው ሰብዓዊውን ሥጋ በእኩል ለበሰ፡፡ አምላካዊውን ሕግ መጠበቅ የቻለው በዘላለማዊ መለኮታዊ ኃይሉ ሳይሆን ለማንኛውም ሰብዓዊ ፍጡር ዝግጁ ለሆነው ውጪያዊ መለኮታዊ ኃይል በመታመን ነበር፡፡

የሱስ ፍጹም አምላክ እና ፍጹም ሰው ነበር፡፡ ይህ ማለት "በህያው ቃሉ ሁሉን ደግፎ የያዘው" (ዕብ. 1፡3) እርሱ "በግርግም ተኝቶ የነበረው ሕፃን" (ሉቃ. 2፡16) ነበር፡፡ ይህ ማለት "እርሱ ከሁሉ በፊት" የነበረውና "ሁሉም ነገር በአንድ ላይ ተያይዞ በእርሱ የጸናው" (ቆላ. 1፡17) እንዲሁም "በጥበብና በቁመት በሞገስም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት" ያድግ የነበረው ነው (ሉቃ. 2፡52)፡፡ ይህ ማለት "ከተፈጠረው ሁሉ ያለ እርሱ የተፈጠረ ምንም የሌለ" (ዮሐ. 1፡3) እና "በእንጨት ላይ ተሰቅሎ የተገደለው" ነው (ሐዋ. 5፡30)፡፡

እንግዲህ ይህ ሁሉ ክርስቶስ ለእኛ ያለውን ፍቅር የሚገልጽ ከሆነ-- ክርስቶስ ለእኛ ያለው ፍቅር አብ ለእኛ ያለው ፍቅር መገለጫ እንደመሆኑ ሐሴት የምናደርግባቸውና የምናመሰግንባቸው አያሌ ምክንያቶች መኖራቸው ብዙም ሊያስገርም አይችልም፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ሮሜ 8፡38-39፡፡ በዛሬው ጥናታችን ያነበብነው ጳውሎስ በዚህ ቦታ የጠቀሰውን **እንድናምን ብርቱ ምክንያት ሊሰጠን የሚችለው እንዴት ነው?**

## ማክሰኞ ሚያዝያ 16

## የመንፈስ ፍቅር

እግዚአብሔር አብ በስህተት የተስተዋለውን ያህል ለማለት በሚያስደፍር መልኩ መንፈስ ቅዱስም በስህተት ተስተውሎአል፡፡ አንዳንድ የነገረ መለኮት ምሑራን መንፈስን በአብ እና በወልድ መካከል እንዳለ ፍቅር አድርገው ያስባሉ፡፡ በሌላ አነጋገር መንፈስ በአብ እና በወልድ መካከል የሚገኝ ፍቅር ብቻ ነው፡፡ አባባሉ እርሱን ከሁለቱ የመለኮት ባህሪያት በማሳነስ ከሥላሴ አካልነት ያወጣዋል፡፡

ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ የራሱ መለኮታዊ ባህሪ እንዳለው መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል፡፡ ክርስቲያኖች ከአብ እና ከወልድ በተጨማሪ በመንፈስ ስም ተጠምቀዋል (ማቴ. 28፡19)፡፡ መንፈስ ክርስቶስን ያከብረዋል (ዮሐ. 16፡14)፡፡ መንፈስ ሰዎችን ይወቅሳል (ዮሐ. 16፡8)፡፡ ያዝናል (ኤፌ. 4፡30)፡፡ አጽናኝ ነው (ዮሐ. 14፡16)፣ ረዳት፣ አማካሪ ነው፡፡ አስተማሪ ነው (ሉቃ. 12፡12) ይማልድልናል (ሮሜ 8፡26)፡፡ ይቀድሰናል (1ጴጥ. 1፡2)፡፡ መንፈስ ሰውን ሁሉ ወደ እውነት እንደሚመራ ክርስቶስ ተናግሯል (ዮሐ. 16፡13)፡፡

በአጭሩ መንፈስ ቅዱስ እንደ አብ እና ወልድ እርሱም እግዚአብሔር ነው፡፡ እነዚህ ሦስቱ አንድ አምላክ ናቸው፡፡

**መንፈስ ቅዱስ የሚያደርገው ነገር ሁሉ መለኮታዊውን ፍቅር ገልጦ ያሳያል፡፡ እርሱ ከሚያደርጋቸው ነገሮች መሃል አንዳንዶቹ የትኞቹ ናቸው? ሉቃ. 12:12፣ ዮሐ. 16:8–13፣ ሐዋ. 13:2፡፡**

መንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ ባህሪ ያለው እግዚአብሔር ለመሆኑ ከፍ ያለው ማስረጃ የክርስቶስ ሥጋ መልበስ ነው፡፡ የሱስ የተወለደው በመንፈስ ቅዱስ ነበር (ማቴ. 1፡20)፡፡ እግዚአብሔር ብቻ በዚያ መልኩ "መፍጠር" ይችላል፡፡

መንፈስ ቅዱስ ሁለት ተቃራኒ ታምራቶችን ለክርስቶስ ማድረግ ችሎአል፡፡ በመጀመሪያ በአንድ ጊዜ ሁሉም ስፍራ የመገኘት ችሎታ ያለውን ክርስቶስ ወደ ማርያም ማህጸን አመጣው፡፡ ክርስቶስ በዚያ አካል ውስጥ ተወስኖ በሰብዓዊ አካል ወደ ሰማይ አረገ፡፡ በሁለተኛ ደረጃ መንፈስ በሰብዓዊቱ የተገደበውን ክርስቶስ በማምጣት በሌላ ምስጢራዊ ታምራት በአለም ዙሪያ በሚገኙ ክርስቲያኖች ፊት እንዲገኝ ያደርገዋል፡፡

መንፈስ ቅዱስ በዚህ መልኩ ከአብ እና ከወልድ ጋር ስለ እኛ በመሥራት ላይ ይገኛል፡፡ "እግዚአብሔር ስለ ሰብዓዊው ዘር ከፉኛ በማዘኑ አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ ዘላለማዊውን የደኅንነት ዕቅድ አወጡ፡፡""—Ellen G. White, *Counsels on Health,* p. 222

እኛን በእኩል የሚወዱን--አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ የደኅንነት ባለቤትና የእግዚአብሔር ዘላለማዊ መንግሥት ወራሾች እንድንሆን በመሥራት ላይ ይገኛሉ፡፡ እንግዲያውስ ይህን ታላቅ መዳን እንዴት ችላ ማለት እንችላለን?

**አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ ስለ እኛ ዘላለማዊ በጎነት በሥራ ላይ የመጠመዳቸው እውነታ ምን ያህል መጽናናት ሊሰጠን ይገባል?**

## ረቡዕ ሚያዝያ 17

## ስለ መዳናችን እርግጠኞች መሆን

አንዳንድ አድቬንቲስቶች ስለ መዳናቸው ገና እርግጠኞች አይደሉም፡፡ መዳናቸውን ማረጋገጥ ስለሚቸገሩ በዘላለማዊው ህይወት ዙሪያ መጨረሻቸውን ለማወቅ ይመኛሉ፡፡ መልካም ለመሆን አብልጠው ቢደክሙም ይህ የትም እንደማያደርስ ያውቃሉ፡፡ ወደ ውስጣቸው ይመለከቱና ለሕይወት ጉዞአቸው ጥቂት የሚያበረታታቸው ነገር ያገኛሉ፡፡

በየሱስ ጸባይና በራሳችን መሃል ያለውን ግዙፍ ክፍተት ስንመለከት ወይም "ወደ ሕይወት የሚያደርሰው ግን መንገዱ ቀጭን፣ በሩም ጠባብ ነው፤ የሚገቡበትም ጥቂቶች ብቻ ናቸው" (ማቴ. 7፡14) የሚለውን ስናነብ--*እንዴት ነው ነገሩ ጎበዝ* የሚል አግራሞት ያልያዘው ማነው?

ሰዎች ለመጨረሻው ጊዜ መዘጋጀት እንዲችሉ ዛሬ ለመዳናቸው ዋስትና ሊኖራቸው ይገባል፡፡ የወደፊቱን ሳይፈሩ በልበ ሙሉነት መጋፈጥ ይችሉ ዘንድ ተጨባጭ በሆነው ደኅንነት ሐሴት ማድረጋቸው የግድ ይሆናል፡፡ ቀደም ብለን እንደተመለከትነው እግዚአብሔር አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ እኛን ለማዳን በሥራ ላይ ናቸው፡፡ በዚህ የተነሳ በመዳናችን እርግጠኞች ሆነን መመላለስ እንችላን፡፡

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥቅሶች ያንብቡ፡፡ ከደኅንነትና እግዚአብሔር ከሰጠን ተስፋ አኳያ ከጥቅሶቹ ምን ዓይነት ተስፋና ዋስትና እናገኛለን?

መዝ. 91፡15-16________________________________________

ኢዮኤ. 2:31-32________________________________________

ዮሐ. 10:28__________________________________________

ሮሜ 10:9–13________________________________________

1ዮሐ. 5:11–13________________________________________

የተቀደሰ ህይወት እንድንኖር ተጠርተናል--ታዘንማል፡፡ ሆኖም ይህ የተቀደሰ ህይወት በክርስቶስ የመዳናችን ውጤት እንጂ የዚያ ደኅንነት ባለቤት የመሆን ምክንያት አይደለም፡፡ እስከ ሞት መታመን ቢኖርብንም፤ ሁሌም ቢሆን የደኅንነትን ስጦታ እንደ ብቸኛው ተስፋችን ልንደገፍ የግድ ይሆናል፡፡ የእግዚአብሔር ሕዝቦች በመጨረሻው ዘመን ታማኞችና ጌታን የሚታዘዙ ሆነው ይገኛሉ፡፡ የዚህ ታማኝነታቸውና ታዛዥነታቸው መንስኤ ክርስቶስ ለእነርሱ ያደረገው ነገር ነው፡፡

## ሐሙስ ሚያዝያ 18

## ዘላለማዊው ወንጌል

**በራእ. 14፡6-7 የቀረበው "የዘላለም ወንጌል" ምንድን ነው?**

__________________________________________________________

__________________________________________________________

በዚህ ቦታ ወንጌል "የዘላለም" በሚል ተጠቅሶአል፡፡ አባባሉ እግዚአብሔር የማይለወጥ አምላክ የመሆኑ ተጨማሪ መስረጃ ነው፡፡ የማይለወጠው አምላክ የማይለወጥ ወንጌል ባለቤት ነው፡፡ ይህ የዘላለም ወንጌል ሊቀበሉት ፈቃደኞች ለሆኑ ሁሉ ዋስትና ይሰጣል፡፡ ወንጌል የማይለወጠውን የእግዚአብሔር ፍቅር ገልጦ የሚያሳየን እንደመሆኑ፤ ይኸው መልእክት ወደ ዓለም ሊሄድ የተገባ ነው፡፡ እያንዳንዱ ሰው ይህን ወንጌል የመስማት ዕድል ሊያገኝ ስለሚገባ የእግዚአብሔር ሕዝብ ይህን ለዓለም እንዲያደርስ ተጠርቶአል፡፡

**"በፊቱ ቅዱሳንና ነውር አልባ እንድንሆን ዓለም ከመፈጠሩ አስቀድሞ**

**በእርሱ መርጦናልና፡፡ በፍቅር፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ልጆቹ እንሆን ዘንድ፣ እንደ በጎ ፈቃዱ አስቀድሞ ወሰነን" (ኤፌ. 1፡4-5)፡፡ ወንጌል በእርግጥ እንዴት "ዘላለማዊ" እንደሆነ አስመልክቶ ጥቅሶቹ ምን ይነግሩናል?**

____________________________________________________________

____________________________________________________________

"ዓለም ከመፈጠሩ አስቀድሞ በእርሱ መርጦናል" የሚለው ሃረግ ስለ "ዘላለማዊ" ወንጌል ይናገራል! ገና ይህ ምድር ከመፈጠሩ አስቀድሞ፤ በእርሱ የደኅንነት ባለቤቶች እንሆን ዘንድ የእግዚአብሔር እቅድ ነው፡፡

በጥቅሶቹ የቀረቡትን አንዳንድ ቃላት እንመልከት፡ "መርጦናል" ፣ "እንደ በጎ ፈቃዱ"፣ "ልጆቹ እንሆን ዘንድ"...፡፡ እግዚአብሔር ይህን ሁሉ ያደረገው ለዘላለም የመሆኑ (2ተሰ. 2፡13፣ 2ጢሞቴ. 1፡9) እውነታ በግልጽ ወደ ጸጋው ያመላክተናል፡፡ ይኸውም የደኅንነት ባለቤቶች የሆንነው ከበጎ ተግባራችን ወይም ከመልካም ፍጥረትነታችን ሳይሆን ከእግዚአብሔር በመነጨና የእርሱ ብቻ ከሆነ የፍቅር ባህሪ ነው፡፡ ገና ከመፈጠራችን አስቀድሞ በእርሱ የዚያ ደኅንነት ባለቤቶች እንድንሆን ከተመረጥን--ማንኛውም ልናደርግ የምንችለው ነገር ለመዳናችን እንዴት መንስዔ መሆን ይችላል? መዳንን ለመቀበል ወይም ለመቃወም ምርጫው የገዛ ራሳችን ነው!

ለመሆኑ ይህ መመረጥ በተመራጩ ግለሰብ ህይወት የሚታየው እንዴት ነው? "በፊቱ ቅዱሳንና ነውር አልባ እንድንሆን" (ኤፌ. 1፡4)፡፡ እንግዲህ የተመረጥነው ለዚህም ነው...፡፡

## አርብ ሚያዝያ 19

**ተጨማሪ ሀሳብ፡** ስለ መዳናችን እርግጠኞች መሆን እንችላለን፡፡ ሆኖም ከልክ ያለፈ መመጻደቅ ውስጥ መግባት ግን የለብንም፡፡ ለመሆኑ የተሳሳተ የደኅንነት ማረጋገጫ የሚባል ነገር አለ? በእርግጥ አለ፡፡ የሱስም ቢሆን በዚህ ዙሪያ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶአል "በሰማይ ያለውን የአባቴን ፈቃድ ሳይፈጽም 'ጌታ ሆይ፤ ጌታ ሆይ' የሚለኝ ሁሉ ወደ መንግሥተ ሰማይ አይገባም፡፡ በዚያ ቀን ብዙዎች 'ጌታ ሆይ፤ ጌታ ሆይ፤ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን? በስምህ አጋንንት አላወጣንምን? በስምህስ ብዙ ታምራት አላደረግንምን?' ይሉኛል፡፡ በዚያ ጊዜ፤ 'ከቶ አላውቃችሁም፤ እናንተ ክፉዎች፤ ከእኔ ራቁ' ብዬ በግልጽ እነግራቸዋለሁ!" (ማቴ. 7፡21-23)፡፡

እነዚህ ሕዝቦች ሁለት ብርቱ ስህተቶች ሠርተዋል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ--የቱንም ዓይነት ታላቅ ሥራ በጌታ ስም ቢሠሩም የጌታን ፈቃድ ይኸውም ሕጉን እየታዘዙ አልነበረም፡፡ የሱስ "ከእኔ ራቁ" እናንተ "ኃጢአት ያልሠራችሁ" አላለም ወይም "ያለ ነቀፋ" የተመላለሳችሁ ወይም ደግሞ "ፍጹም ያልሆናችሁ" አላለም፡፡ ይልቁንም እነዚህን ሕዝቦች የገለጻቸው "ክፉዎች" ወይም "ሕገ ጠሎች" በሚል ቃል ነው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ--ስለ ራሳቸውና ስለሠሯቸው ነገሮች የሚሰጡትን አጽንኦት ልብ ይበሉ፡ *ይህን በስምህ አላደረግንም? ወይም ያንን በስምህ አላደረግንም?* ራሳቸውን በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ አድርገው ለማቅረብ ምን ያህል ከክርስቶስ ርቀው ሄደዋል? እኛን የሚያድኑ ብቸኛ ሥራዎች የክርስቶስ ሲሆኑ፤ እነርሱም በእምነት ለእኛ ተቆጥረዋል፡፡ ዋስትናችን የራሳችን ማንነት ወይም ሥራችን ሳይሆን ክርስቶስ ለእኛ ያደረገው ነገር ብቻ ነው፡፡ ለመዳንዎ ዋስትና ይፈልጋሉ? እንግዲያውስ የእግዚአብሔርን ሕግ ይጠብቁና በክርስቶስ የጽድቅ ሥራ ብቻ ይረፉ፡፡ ያን ጊዜ የሚያስፈልጎትን

ማረጋገጫ ያገኛሉ፡፡

## የመወያያ ጥያቄዎች፡

1.ታዋቂው የክርስትና ተሐድሶ አራማጅ ማርቲን ሉተር እንዲህ ብሎ ነበር፡ “ወደ ራሴ ስመለከት እንዴት መዳን እንደምችል አላውቅም፡፡ ወደ የሱስ ስመለከት ደግሞ እንዴት መጥፋት እንደምችል አላውቅም፡፡” በእነዚህ ቃላት ውስጥ እንዴት ዓይነት ታላቅ ጥበብ አለ? ይህን ስሜት ሁሌም ከፊታችን ማኖር መልካም ሀሳብ የሚሆነው ለምንድን ነው?

2.ዓለም ከመፈጠሩ አስቀድሞ በመመረጣችን ጽንሰ ሀሳብ ዙሪያ ተወያዩ፡፡ አባባሉ እያንዳንዱ ሰው ይድናል የሚል አንደምታ ያልኖረው ለምንድን ነው? ሰዎች ሳይድኑ የሚቀሩት እግዚአብሔር ስላልመረጣቸው ነው ወይስ እነሱ ስላልመረጡት? ጥያቄዎቹን በክፍል ተወያዩ፡፡

3.የታላቁ ተቃርኖ ትዕይንት አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ በሚወዱት ዓለም የክፉውን በተጨባጭ መከሰት በተሻለ ማስተዋል እንድንችል የሚረዳን እንዴት ነው?

# አምስተኛ ትምህርት

ከሚያዝያ 20 – 26

## ክርስቶስ በሰማያዊው መቅደስ

### ሰንበት ከሰዓት

***ለዚህ ሳምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ሮሜ.*** *8:3፣ ዮሐ. 1:29፣ ራእ. 5:12፣ ዕብ. 7:1–28፣ 9:11–15፣ ዘሌዋ. 16:13፣ ዕብ. 9:20–23፡፡*

**የሳምንቱ መታሰቢያ ጥቅስ:**

**“ስለዚህ እግዚአብሔር እጅግ ከፍ አደረገው፤ ከስምም ሁሉ በላይ የሆነውን ስም ሰጠው፤ ይኸውም በሰማይና በምድር፣ ከምድርም በታች፣ ጉልበት ሁሉ ለኢየሱስ ስም ይንበረከክ ዘንድ” (ፊልጵ. 2፡9-10)፡፡**

የዕብራውያን መጽሐፍ በሰማያዊው መቅደስ ስላለው የሱስ ሲናገር እንዲህ ይላል፡ “ይህም ስፍራ ኢየሱስ ስለ እኛ ቀድሞ የገባበት ነው፡፡ እርሱም እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ለዘላለም ሊቀ ካህናት ሆኖአል፡፡” (ዕብ. 6፡20)፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ፤ በተለይም አዲስ ኪዳን ክርስቶስ በዚህ ምድር ስለ እኛ መሥዋዕት ሆኖ ሥራውን ካጠናቀቀ በኋላ በሰማያዊው መቅደስ እንደ ሊቀ ካህናችን ሆኖ የሚጫወተውን ሚና በግልጽ ያስቀምጥልናል (ዕብ. 10፡12)፡፡

በዚህ ሣምንት ክርስቶስ በሰማያዊው መቅደስ እየሰጠ በሚገኘው አገልግሎት ዙሪያ ፍተሻ እናደርጋለን፡፡ የእርሱ የማማለድ ሥራ ሕዝቡን ለመጨረሻው ጊዜ በማዘጋጀቱ ረገድ ወሳኝ ድርሻ አለው፡፡ ስለዚህ ይህ እጅግ ጠቃሚ የሆነ ምክር ተሰጥቶናል፡ “የቤተ መቅደሱና የፍርድ ምርመራው ርዕሰ ጉዳይ በእግዚአብሔር ሕዝቦች ዘንድ በግልጽ ሊስተዋል ይገባል፡፡

ሁሉም--ታላቁ ሊቀ ካህን ስለሚገኝበት ሁናቴ ለየራሳቸው ዕውቀት ሊኖራቸው ያስፈልጋል፡፡ ያለበለዚያ በዚህ ጊዜ አንገብጋቢ የሆነውን እምነት ለመለማመድ ወይም በእግዚአብሔር የታቀደላቸውን ስፍራ ለመሙላት የማይቻል ይሆንባቸዋል፡፡”—Ellen G. White, *The Great Controversy,* p. 488. ክርስቶስ በሰማያዊው ቤተ መቅደስ ለእኛ ምን እያደረገ ይገኛል? ይህን ጉዳይ በተለይ በመጨረሻዎቹ ጊዜያቶች ማስተዋላችን በጣም አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?

## እሑድ ሚያዝያ 21

## *ታላቁ መሥዋዕትነት*

ታላቁን የክርስቶስ መሥዋዕትነት ማጥናታችን አማኞችን ለመጨረሻው ጊዜ በማዘጋጀቱ ረገድ ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡ ብዙውን ጊዜ ሰዎች ከፊታቸው ወዳስቀመጡት ግብ የሚመለከቱ ሲሆን ይህ ደግሞ ትክክል ነው፡፡ ሆኖም ከዚህ በተጨማሪ ከኋላቸውም ዕቅድ መኖሩን መገንዘባቸው መልካም ነው፡፡ ስለ ቀራኒዮ እንናገራለን፡፡ በዚህ ቦታ የሱስ ስለ እኛ ያደረገው ነገር የማይቀለበስና የመጨረሻ ከመሆኑ በተጨማሪ ከፊት ለፊት ላለው ግብ እርግጠኞች የሚያደርገን ነው፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ሮሜ 8:3፣ 1ጢሞቴ. 1:17፣ 6:16፣ 1ቆሮ. 15:53፡፡ እግዚአብሔር ልጁን ወደ ዓለም የላከው ለምንድን ነው?**

---

---

እግዚአብሔር ኃጢአትን በሥጋ ለመኮነን ክርስቶስን የኃጢአት መሥዋዕት አድርጎ ላከው፡፡ ይህ ምን ማለት ነው? ክርስቶስ በባህሪው መለኮት እንደመሆኑ ሊሞት አይችልም፡፡ ስለዚህ ጌታ በትክክል በእኛ ምትክ መሞት ይችል ዘንድ እንደ እኛ ሰው ሆኖ ሟች የሆነውን ማንነት ለራሱ ወሰደ፡፡

ምንም እንኳ እርሱ መለኮት፣ በባህሪውም አምላክ ቢሆንም "በሰው አምሳል ተገኝቶ... እስከ ሞት፣ ያውም በመስቀል ላይ እስከ መሞት ድረስ ታዛዥ ሆነ" (ፊልጵ. 2፡6-8)፡፡ የሱስ በመስቀል ላይ በሞተ ጊዜ መለኮትነቱ ግን በእግዚአብሔር ዘንድ ብቻ በሚታወቅ መልኩ ሕያው ነበር፡፡ የሱስ ለዘጠኝ ወራት በማኅጸን ውስጥ በነበረባቸው ጊዜያቶችና በመቃብር በቆየባቸው ቀናት መለኮትነቱ ሰው ሊያስተውል ከሚችለው በላይ በጸጥታና በተረጋጋ ሁናቴ ውስጥ የነበረ ሲሆን፣ ይህን መለኮትነቱን በምድራዊ ሕይወቱና አገልግሎቱ ፈጽሞ አልተጠቀመም ነበር፡፡

**ጥቅሱን ያንብቡ፡ ሉቃ. 9፡22፡፡ ጥቅሱ በዕቅድና ሆን ተብሎ ገቢራዊ ስለሆነው የክርስቶስ ሞት ምን ይነግረናል?**

---

---

ክርስቶስ የተወለደው ለኃጢአት መሥዋዕት ሆኖ ለመሞት ነበር፡፡ ክርስቶስ ስለ ሚደርስበት--ፌዝ፣ እንግልት፣ ግርፋት፣ ድብደባና ልብ የሚሠብር ሥቅላት ሳያስብ የኖረበት ዘመን ሊኖር እንደማይችል መገመት አያዳግትም፡፡ ይህ ፈጽሞ ያልታየና ሙሉ ለሙሉ ያልተስተዋለ አቻ የሌለው ፍቅር ነው፡፡

**እኛ ሰብዓዊ ፍጡራን በእንዲህ ዓይነቱ ፍቅር እግሮች ስር ወድቀን በእምነትና በመታዘዝ አምልኮ ከማቅረብ ውጪ ምን ማድረግ እንችላለን? የመስቀሉ እውነታ ስለ ሰው መልካም ሥራ ከንቱነት ምን ይነግረናል?**

## ሰኞ ሚያዝያ 22

## የእግዚአብሔር በግ

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ዮሐ. 1፡29፣ ራእ. 5፡12፣ 13፡18፡፡ ጥቅሶቹ በጋራ የያዙት አንድ ምስል ምንድን ነው? የደኅንነትን እቅድ እንድናስተውል በመርዳቱ ረገድ የምስሉ አስፈላጊነት ምን ይመስላል?

__________________________________________________

__________________________________________________

__________________________________________________

መጥምቁ ዮሐንስ የሱስን "የእግዚአብሔር በግ" ብሎ ሲጠራው ስለ ቤተ መቅደሱ የማያሻማ ማስረጃ እያቀረበ ነበር፡፡ እንዲያውም ይበልጥ ቀጥተኛ በሆነ መንገድ የክርስቶስን ለኃጢአት መሞት እንደ ብቸኛው ለኃጢአት መሥዋዕት የታረዱ የሁሉም በጎች (እና በዕብራውያን ሜዳዊ ሥርዓት የማንኛውም እንስሳ) መሥዋዕት ፍጻሜ አድርጎ ሲያቀርብ ይስተዋላል፡፡ በእርግጥ አራቱ ወንጌሎች የቱንም ዓይነት ተጨማሪ ትምህርት ቢኖራቸውም የመልእክታቸው አንኳር ታሪክ የሱስ እንደ እግዚአብሔር በግ የዓለምን ኃጢአት በማስወገድ ስለነበረው ሚና ነው፡፡

ሆኖም የየሱስ ታሪክ እና እርሱ ለደኅንነታችን የሠራው ሥራ ከሞቱና ከትንሣኤውም በኋላ እንኳ በወንጌል መልእክቶች ብቻ አይጠናቀቅም፡፡

ክርስቶስ የመሥዋዕት በግ ሆኖ ሥራውን ካከናወነ በኋላ በሰማያዊው መቅደስ ሊቀ ካህን ሆኖ የሚሰጠውን አገልግሎት የዕብራውያን መጽሐፍ ገና ከመጀመሪያው የሚዳስሰው ርዕሰ ጉዳይ ነው፡፡ ከመስቀሉ በኋላ በሚኖረው ሚና ዙሪያ ለመጀመሪያ ጊዜ በዚህ ስፍራ ከተጠቀሰበት አንስቶ (ዕብ. 1፡3) ባሉት ቀጣይ የመጽሐፉ ምዕራፎች የሱስ የሚወሳው እንደ ሊቀ ካህን ነው፡፡ በሰማያዊው መቅደስ የሚሠራው ሥራ ሙሉ ዝርዝር በዕብ. 7፡1-28

ተብራርቶአል፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ዕብ. 7፡1-28፡፡ ሐዋርያው ስለ የሱስ ምን እያለ ነው?**

___

___

___

ምንም እንኳ እነዚህ ቁጥሮች በጣም ጥልቀት ያላቸውና እጅግ የበለጸጉ ቢሆኑም፤ ከአሮን መስመር ምድራዊ የቤተ መቅደስ አገልግሎት ካህናት ይልቅ የሱስ ክርስቶስ የተሻለ ክህነት አለው የሚል ፍሬ ነገር ይዘዋል፡፡ አሁን ግን በምድራዊው ካህንና ቤተ መቅደስ ፋንታ በሰማያዊው መቅደስ የሚያገለግል ሰማያዊ ሊቀ ካህን አለን፡፡ ስለዚህ ዐይኖቻችንን በየሱስ ላይ ስናሳርፍ እርሱን እንደ ሰማያዊ መቅደስ ሊቀ ካህናችን መመልከት እንችላለን፡፡

## ማክሰኞ ሚያዝያ 23

## ሊቀ ካህናችን

**የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ዕብ. 7፡24-27፣ 8፡6፡፡ በጥቅሶቹ የተሰጠን ታላቅ ተስፋ ምንድን ነው?**

___

___

___

ሌላ ካህን ፈጽሞ ሊኖረው የማይችለውን ብቃት የተላበሰው ክርስቶስ ሙሉ ለሙሉ የማዳን ኃይል አለው፡፡ እርሱ ኃጢአትን ይቅር የማለት ሥልጣን ያለው አምላክ ነው፡፡ ቋሚ የክህነት ሥልጣን በእጁ ነው፡፡ ክርስቶስ በሽተኛውን ሲፈውስና ብቸኝነት ያጠቃውን ሲያጽናና ይስተዋልበት በነበረው ተመሳሳይ ፍቅር ለዘመናት ለሕዝበ ክርስቲያኑ ሲማልድ ኖሮአል፡፡ ክርስቶስ እንደ

ማናችንም ሰው ቢሆንም ነገር ግን ያለ ኃጢአት ተወለደ--ያለ ኃጢአትም ኖረ፡፡ ኃጢአት የሌለበት እርሱ የመላውን የሰው ዘር ኃጢአት ድምር ተሸክሞ ሞተ፡፡ ስለዚህ ሰው እና አምላክ የሆነው ክርስቶስ ብቻ በሰማያዊው መቅደስ ለኃጢአተኞች የመማለድ ሥራ መሥራት ይችላል፡፡

የክርስቶስ መሥዋዕትነት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ገቢራዊ መሆኑን እነዚህ ጥቅሶች ያሳዩናል፡፡ ለአንድ ጊዜ ብቻ መሆን የነበረበት የእርሱ መሥዋዕትነት ለእያንዳንዱ ሰብዓዊ ፍጡር ደኅንነት ለማምጣት በቂ ነበር፡፡

በመስቀል ላይ መሥዋዕት የሆነው ማን እንደሆነ ማስተዋል እስከ ቻልን ድረስ እንደዚያ ዓይነቱ መሥዋዕትነት ለመላው ሰብዓዊ ፍጡር በቂ መሆን አይችልም?

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ዕብ. 9፡11-15፡፡ ክርስቶስ ቀደም ሲል በሞቱ እሁን ደግሞ በሰማያዊ አገልግሎቱ ምን አስገኘልን**?

______________________________________________________

______________________________________________________

ክርስቶስ "የዘላለም ቤዛነት" አስገኘልን ሲል ዕብ. 9፡12 ይነግረናል፡፡ ቤዛነት በማለት የተተረጎመው የግሪክ ቃል በተጨማሪ "መዋጀት"፣ "ዋጋ ከፍሎ ማስለቀቅ"፣ "ንብረትንና ሙብትን ማውረስ"፣ "ማዳን" የሚል ፍቺ አለው፡፡ ተመሳሳይ ቃል በሉቃ. 1፡68 ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን ይኸውም ጌታ "መጥቶ ሕዝቡን ተቤዥቶአልና" በማለት ዘካርያስ በተናገረ ጊዜ ነበር፡፡ ዋጋ ከፍሎ ያስለቀቀንና ቤዛ የሆነን፣ የዓለምን ኃጢአት ለማስተሰረይ ብቁ የሆነው ብቸኛው የመሥዋዕት በግ ክርስቶስ ነው--የሚለው አገላለጽ የክርስቶስን ደም ይወክላል፡፡ ክርስቶስ ይህን ያስገኘው ለራሱ ሳይሆን ነገር ግን ለእኛ መሆኑ የወንጌልን የምስራች ታላቅ ያደርገዋል፡፡ የክርስቶስን መሥዋዕትነት ለግላቸው

ለሚቀበሉ ሁሉ ይህ ፍቱን ነው፡፡

**ክርስቶስ "የዘላለም ቤዛነት" አስገኘልን በሚለው ጽንሰ ሃሳብ ዙሪያ ተወያዩ፡፡ እርሱ ይህን ዘላማዊ ቤዛነት ካስገኘልን በኋላ ነበር ስለ እኛ ወደ ሚያከናውነው ሰማያዊ የመቅደስ ሥራው የገባው፡፡ ክርስቶስ በሰማያዊው መቅደስ ለእኛ እያደረገ ስላለው ነገር ይህ ምን ዓይነት ተስፋ ይሰጠናል?**

## ረቡዕ ሚያዝያ 24

## አማላጃችን

ምንም እንኳ ኃጢአት በእግዚአብሔርና በሰብዓዊው ዘር መሃል አስፈሪ መለያየት ቢፈጥርም፤ በክርስቶስ የመሥዋዕትነት ሞት አማካይነት እኛ እንደ ሰብዓዊነታችን ወደ እግዚአብሔር መቅረብና ከእርሱ ጋር የነበረንን ግንኙነት መቀጠል ቻልን--ኤፌ. 2፡18፣ 1ጴጥ. 3፡18፡፡

**"እኛም የነፍስ መልሕቅ የሆነ ጽኑና አስተማማኝ ተስፋ አለን፤ ይህም ተስፋ ከመጋረጃው በስተ ጀርባ ወዳለው ውስጠኛ መቅደስ ይገባል፡፡ ይህም ስፍራ ኢየሱስ ስለ እኛ ቀድሞ የገባበት ነው፡፡ እርሱም እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ለዘላለም ሊቀ ካህናት ሆኖአል" (ዕብ. 6፡19-20)፡፡ በጥቅሶቹ መሰረት የሱስ ለእኛ ያደረገው ምንድን ነው?**

---

**የክርስቶስ ሥራ ስለሚያካትተው ነገር ዕብ፣ 9፡24 ምን ይላል?**

---

---

የሱስ ስለ እኛ በአብ ፊት ሊታይ ወደ ሰማያዊው መቅደስ ገባ፡፡ ይህ ማለት የሱስ በሥርየት አገልግሎቱ "የዘላለም ቤዛነት ሊያስገኝ" ስለ እኛ በአብ ፊት ቆሞአል፡፡

አዎ--የሱስን የግል አዳኛችን አድርገን ስንቀበል ኃጢአታችን ተሰርዞ፣ ይቅር ተብለንና ነጽተን በእግዚአብሔር ፊት እንቆማለን፡፡ ነገር ግን ክርስቲያን ከሆንና እነዚያ ሁሉ የአሸናፊነት ድንቅ ተስፋዎች ከተሰጡን በኋላም እንኳ አሁንም አልፎ አልፎ ራሳችንን በኃጢአት ወድቆ እናገኘዋለን፡፡ እንዲህ ያለው ሁናቴ ሲከሰት በሰማይ ያለው የሱስ ሊቀ ካህናችን ይማልድልናል፡፡ ተነሳሂውን ኃጢአተኛ የሚወክለው እርሱ የእኛን መልካም ሥራ ሳይሆን (ምንም መልካም ሥራ ስለሌለን) ይልቁንም የራሱን የጽድቅ ሥራ ይዞ ስለ እኛ በአብ ፊት ይማልዳል፡፡ "ስለዚህ ስለ እነርሱ እየማለደ ሁል ጊዜ በሕይወት ስለሚኖር፣ በእርሱ በኩል ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል፡፡" (ዕብ. 7፡25)፡፡

**ምንም እንኳ በየሱስ የአዲስ ሕይወት ባለቤቶች ብንሆንም፣ በራሳችን ውስጥ አስደናቂ ለውጦች መመልከት ብንችልም፤ ቋሚና ጽናት ያለው ምኅረትና ይቅርታ እንደሚያስፈልገው የማይገነዘብ ማን ነው? ክርስቶስን እንደ ሊቀ ካህናታችን ማወቃችንና መገንዘባችን ለእኛ የከበረ የሆነው ለምንድን ነው?**

## ሐሙስ ሚያዝያ 25

## የስርየት ቀን

ምድራዊው የዕብራውያኑ የቤተ መቅደስ አገልግሎት ክርስቶስ ሊቀ ካህናችን ሆኖ የከፈተውና የገባበት የሰማያዊው ምሳሌ መሆኑን የዕብራውያን መጽሐፍ ያስተምራል፡፡ ሁለቱን ክፍሎች እንዲሁም የመሥዋዕት እና ከኃጢአት የሚነጻበትን ሥርዓት የያዘው ምድራዊው አገልግሎት ይካሄድ የነበረው "ምሳሌና ጥላ በሆነችው ውስጥ ነው፤ ሙሴ ድንኳኒቱን ለመሥራት በተነሣ ጊዜ፣ 'በተራራው ላይ በተገለጠልህ ምሳሌ መሠረት ሁሉን ነገር እንድታደርግ ተጠንቀቅ' የሚል ትእዛዝ የተሰጠው በዚህ ምክንያት ነበር" (ዕብ. 8፡5)፡፡ ምድራዊው የቤተ መቅደስ አገልግሎት ሁለቱን ክፍሎች ማለትም ቅዱሱንና

ቅድስተ ቅዱሳኑን እንዳካተተ ሁሉ፤ የክርስቶስም ሰማያዊ መቅደስ አገልግሎት በተመሳሳይ ሁለቱንም ክፍሎች ያካትታል፡፡ በዘሌዋ. ምዕ. 16 የቤተ መቅደሱን መንጻት ያስከተለው የምድራዊው ቤተ መቅደስ የፍርድ ጽንሰ ሃሳብ ከሥርየት ቀን ጋር የተመላከተ ነበር፡፡ ይህ ሊቀ ክህኑ ስለ ሕዝቡ የማንጻትና የስርየት ሥራ ለመሥራት በዓመት አንድ ጊዜ ወደ ሁለተኛው ክፍል ማለትም ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ (ዘሌዋ. 16፡12-14) የሚገባበት ነው፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ዕብ. 9፡20-23፡፡ ሊነጻና ሊታጠብ የሚያስፈልገው ነገር ምንድን ነው? ይህ ለክርስቶስ አገልግሎት የስርየት ቀን ግልጽ ማጣቀሻ የሆነው ለምንድን ነው?**

---

ራሱ ሰማያዊው መቅደስ ሳይቀር “መንጻት” ይኖርበታል ወይስ አይኖርበትም የሚለው አስተሳሰብ በነገረ መለኮት ምሑራን ዘንድ ግርምትን የፈጠረ ነበር፡፡ ሆኖም ጉዳዩ ከስርየት ቀን ማጣቀሻ አኳያ ከተስተዋለ በኋላ ግን ችግሩ መወገድ ችሎአል፡፡ ክርስቶስ በሰማያዊው መቅደስ የሚሠራው ሥራ ምድራዊው ሊቀ ካህን በእስራኤላውያኑ መቅደስ በዓመት አንድ ጊዜ ያከናውን ለነበረው የስርየት አገልግሎት እውነተኛ ማሳያ እንደ ነበር በዕብ. 9፡23 እንመለከታለን፡፡ ምድራዊው ሊቀ ካህናት ይሠራ የነበረው ቤተ መቅደሱን የማንጻት ሥራ ክርስቶስ አንድ ቀን በሰማያዊው መቅደስ ለሚሠራው ሥራ አመላካች ነበር፡፡ ይህ የሰማያዊው ነገር የማንጻት ተግባር ክርስቶስ እንዳረገ ገቢራዊ ይሆናል ብሎ ጥቅሱ አይነግረንም፡፡ ይልቁንም በ1844 ይኼኛው የአገልግሎት ምዕራፍ እንደ ጀመረ ከዳንኤል መጽሐፍ ጥናት መመልከት እንችላለን፡፡ ስለዚህ የመጨረሻዎቹን ቀናት እንደሚጋፈጡ ክርስቲያኖች የምንገኝባቸውን ብርቱ ቀናት እያስተዋልን ቀደም ባሉት ጊዜያቶች ክርስቶስ በሰጠን ዋስትናዎች እና አሁን በቅድስተ ቅዱሳን እያደረገልን ባለው ነገር ላይ ማረፍ ይኖርብናል፡፡

**የመጀመሪያው መልአክ እንዲህ ሲል በታላቅ ድምፅ ዐወጀ፡ “እግዚአብሔርን ፍሩ፤ ክብርንም ስጡት፤ ምክንያቱም የፍርዱ ሰዓት ደርሶአል” (ራእ. 14፡7)፡፡ የአምላካዊው ፍርድ በተጨባጭ መኖር መጨረሻው የተቃረበ መሆኑን ያመላክታል፡፡ እውነታው በዕለት ከዕለት አኗኗራችን ላይ ተጽእኖ ሊኖረው የሚችለው እንዴት ነው?**

## አርብ ሚያዝያ 26

**ተጨማሪ ሀሳብ፡** ክርስቶስ በምድር *መሥዋዕት* በመሆን በሰማይ ደግሞ በሊቀ ካህናትነት የሚሰጠውን አገልግሎት ለመግለጥ የዕብራውያን መጽሐፍ በምሳሌነት ወደ ምድራዊው መቅደስ ያመላክተናል፡፡ የእስራኤላውያን ቤተ መቅደስ ሁሌም ቢሆን የወንጌል ተጨባጭ ማስተማሪያ መሣሪያ ነው፡፡ ሥርዓቱ መሥዋዕትን፣ ፍርድንና የኃጢአትን መጨረሻ የሚያካትተውን የደኅንነት እቅድ ለአይሁዳውያን ለማስተማር ታልሞ የተዘጋጀ ነበር፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ክርስቶስ በፍጻሜው ጊዜ በሰማያዊው መቅደስ የሚሠራውን የመጨረሻ ሥራ ገጽታ አንባቢው ማስተዋል እንዲችል የሚረዱ ተጨማሪ ብርሃኖችን የዳንኤል መጽሐፍ ያክልልናል፡፡ “ለመንጻት፣ ለፍርድ እና ለጽድቅ አጽንኦት የሚሰጡት የዳንኤል የመጨረሻው ጊዜ ራእዮች በምድር ታሪክ መዝጊያ ላይ ገቢራዊ ወደሚሆነው የስርየት ቀን ገጽታ ያመላክታሉ፡፡ የማንጻት ሥራው ከሰማያዊው መቅደስ እና ከንጉሡ መሲህ ሊቀካህን ጋር በቀጥታ የተቆራኘ ነው፡፡ ራእዮቹ አንባቢውን ከጊዜ አላባ ጋር በማስተዋወቅ መሲሁ በእግዚአብሔር ማደሪያ ሆኖ የመጨረሻውን የማንጻት፣ የፍርድ እና የጽድቅ ሥራውን በሚጀምርበት ጊዜ በደህንነት ታሪክ ውስጥ ያሉትን ተወስነው የተቀመጡ ጊዜያቶች ለይቶ እንዲገነዘብ ያስችላሉ፡፡”—*Handbook of Seventh-day Adventist Theology (Hagerstown, Md.: Review and Herald® Publishing Association, 2000), p. 394.*

***የመወያያ ጥያቄዎች፡***

ይህን ከኤለን ኋይት መልእክት የተወሰደ ጽሑፍ ይመልከቱ፡ "በጥንት ዘመን መሥዋዕት በሚሆነው እንስሳ ላይ በእምነት ይተላለፍ የነበረው የሕዝቡ ኃጢአት በታረደው የእንስሳ ደም ምሳሌ ወደ ምድራዊው መቅደስ ይተላለፍ ነበር፡፡ በተመሳሳይ በአዲሱ ኪዳን የተነሳሂው (ንስሐ የገባው ሰው) ኃጢአት በእምነት በክርስቶስ ላይ ያርፍና ወደ ሰማያዊው መቅደስ ይተላለፋል፡፡ የተለመደው ምድራዊው የማንጻት ሥራ የሚከወነው በኃጢአት የተበከለውን በማስወገድ አንደ ነበር ሁሉ፤ ሰማያዊው የማንጻት ሥራ ተግባራዊ የሚሆነው ደግሞ በዚያ የተጻፈውን በማስወገድ ወይም በመደምሰስ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ይህ መተግበር ከመቻሉ አስቀድሞ የእርሱ ስርየት ተጠቃሚ ለመሆን ማን ለኃጢአቱ ንስሐ እንደገባና በክርስቶስ ላይ እምነት እንዳለው ለማየት መጻሕፍት መመርመራቸው የግድ ይሆናል፡፡ "—***The Great Controversy,* pp. 421, 422. ኤለን ኋይት "የእርሱ ስርየት ተጠቃሚ" ስለሆኑት የምትናገራቸው ሁለት ነገሮች ምንድን ናቸው**? በተለይ ከመጨረሻው ጊዜ ፈተናዎች አኳያ የእነዚህን ነገሮች ምንነት በእጅጉ ማስተዋል አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ዘሌዋ. 16፡15-16፡፡ የደም ትርጉም ምንድን ነው? ደም ምን ይወክል ነበር? በጥንት ዘመን ደም ለስርየት ቀን ሥርዓታዊ አገልግሎት በእጅጉ አንገብጋቢ የነበረው ለምንድን ነው? ዛሬስ ለእኛ ያለው አንደምታ ምን ይመስላል?**

# ስድስተኛ ትምህርት

ከሚያዝያ 27- ግንቦት 3

## የሕግ "መለወጥ"

### ሰንበት ከሰዓት

***ለዚህ ሳምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡*** *ሮሜ 8:1፣ 7:15–25፣ ሮሜ 7:1–14፣ የሐ. 20:19–23፣ ሐዋ. 20:6-7፣ ዳን. 7:23–25፣ ራእ. 13:1–17፡፡*

**የሳምንቱ ጥናት መሪ ጥቅስ፡-**

**"በልዑል ላይ የዐመፅ ቃል ይናገራል፤ የልዑልንም ቅዱሳን ያስጨንቃል፤ ለበዓላት የተመደበውን ጊዜና ሕግን ለመለወጥ ይሞክራል፤ ቅዱሳንም ለዘመን፣ ለዘመናት፣ ለዘመን እኩሌታም ለእርሱ ዐልፈው ይሰጣሉ"** (ዳን. 7፡25)፡፡

የመጨረሻውን ጊዜ ክስተቶች ለመረዳት ዋናውና ማዕከላዊው ክፍል በእግዚአብሔር ሕግ ዙሪያ የሚነሳው ጥያቄ ነው፡፡ ጉዳዩን ይበልጥ ጠለቅ ብለን ስንመለከተው በአራተኛው ትእዛዝ ማለትም በሰባተኛው ቀን ሰንበት ላይ የሚነሳ ጥያቄ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ምንም እንኳ መዳን የሚገኘው በእምነት ብቻ መሆኑን ብናስተውልም፤ ሰንበትን ጨምሮ ሕጉን መጠበቅ ደኅንነት ሊያስገኝ እንደማይችል ብንረዳም፤ ነገር ግን በመጨረሻው ጊዜ ሰባተኛውን ቀን ሰንበት ጨምሮ የእግዚአብሔርን ሕግ መታዘዛችን የእውነተኛ ታማኝነታችን ውጫያዊ ምልክት መሆኑን እናውቃለን፡፡

ይህ ልዩነት ይበልጥ ግልጽ እየሆነ የሚመጣው በተለይ በራእ 13 እና 14 በተገለጹት የመጨረሻው ጊዜ ክስተቶች መሀል ሲሆን ይኸውም የፖለቲካና የኃይማኖት ኃያላን፤ በምድር ሕዝቦች ላይ ሐሰተኛ አምልኮ እንዲተገበር

የሚያስገድድ ኅብረት በሚፈጥሩበት ወቅት ነው፡፡ እነዚህ አካሄዶች "ሰማይንና ምድርን፣ ባሕርንና የውሃ ምንጮችን ለፈጠረው ስገዱ" (ራእ. 14፡7) ከሚለው የእግዚአብሔር ሕዝቦች ከተጠሩበት ፈጣሪን ከማምለክ ጋር የሚቃረኑ ናቸው፡፡

በዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችን በእግዚአብሔር ሕግ፤ በተለይ ሰንበት ላይ ትኩረት በማድረግ ይህ ሕግ የከበበውን ሁኔታና ለመለወጥ የተደረጉ ሙከራዎችን እንዳስሳለን፡፡ መጨረሻው እየተቃረበ በመጣ ቁጥር ሰንበት ለእኛ የሚኖረውን አንደምታም እንዲሁ እንፈትሻለን፡፡

## እሑድ ሚያዝያ 28

## አምላካዊው ተስፋ

በመጽሐፍ ቅዱስ ከምናገኛቸው ታላላቅ ተስፋዎች አንዱ ሮሜ 8፡1-2 ነው፡ "ስለዚህ በክርስቶስ ኢየሱስ ያሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም፤ ምክንያቱም የሕይወት መንፈስ ሕግ በክርስቶስ ኢየሱስ ከኃጢአትና ከሞት ሕግ ነጻ አውጥቶአችኋል፡፡" እነዚህ ቃላት እንደ ባቡር ፉርጎ ተቀጣጥለው ለመጡ ሀሳቦች እንደ አክሊል ወይም መደምደሚያ ናቸው፡፡ ጳውሎስ ቀደም ሲል ያነሳቸውን ከእነዚህ ቁጥሮች ኋላ ያሉትን ሀሳቦች በማጥናት በውስጣቸው የያዙትን ተስፋዎች በተሻለ መጨበጥ እንችላለን፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ሮሜ 7፡15-25፡፡ ሐዋርያው በሮሜ 8፡1-2 የተናገረውን የሚያረጋግጥልን የዚህ መልእክቱ መሰረታዊ ነጥብ ምንድን ነው?

________________________________________________

________________________________________________

________________________________________________

ምንም እንኳ በጳውሎስ መልእክቶች ዙሪያ በተለይም እንደ አንድ አማኝ ስለ ራሱ በጻፋቸው መልእክቶች በክርስትናው ዓለም ከፍ ያሉ ሙግቶች ቢነሱም አንድ ነገር ግን ግልጽ ነው፡ በእርግጥ ጳውሎስ እየተናገረ የነበረው ስለ ኃጢአት ተጨባጭ ሁኔታ ነው፡፡ እያንዳንዱ ሰው፣ ክርስቲያኖችም ቢሆኑ ጳውሎስ ከጠቀሰው ትግል ጋር በተመሳሳይ ራሳቸውን ሊያገኙ ይችላሉ፡፡ የሥጋ ፈቃድ ዝንባሌ እና በውስጥ "የሚኖረው ኃጢአት" ማድረግ የሌለበትን እንዲያደርግ ያልገፋፋው ወይም ማድረግ እንደሌለበት እያወቀ ያላደረገ ማን ነው? ለጳውሎስ ችግሩ ያለው ሕጉ ላይ ሳይሆን የሥጋው ፈቃድ ላይ ነው፡፡

ትክክለኛውን ነገር ለማድረግ እየፈለገ ነገር ግን የተሳሳተውን እያደረገ ራሱን ያላገኘ ማን አለ? ጳውሎስ ዳግም በተወለደው ክርስቲያን ሕይወት የኃጢአትን አይቀሬነት ባያወራ እንኳ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ብርቱ ምኞት ያለው ሁሉ ሰርክ ስለሚጋፈጠው ትግል ብርቱ ማሳያ አቅርቦአል፡፡

ጳውሎስ እንዲህ ሲል ዝነኛውን መልእክት ያቀርባል "እኔ ምን ዓይነት ጎስቋላ ሰው ነኝ! ከዚህ ለሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ሊያድነኝ ይችላል?" (ሮሜ. 7:24)፡፡ ለጥያቄው መልስ ያገኘው በየሱስ ሲሆን ይኸውም በየሱስ የሚያምኑና እንደ መንፈስ ፈቃድ በጸጋው የሚመላለሱ "ኩነኔ የለባቸውም" የሚል ነው፡፡ አዎ--አማኞች ሁሌም ትግል ውስጥ እንደመሆናቸው ይፈተናሉ፣ ኃጢአትም ይሠራሉ፡፡ ነገር ግን አማኞች በየሱስ ላይ በሚኖራቸው እምነት በሕጉ ኩነኔ የለባቸውም፡፡ በእርግጥ የመታዘዝ ሕይወት ግን ይኖራሉ፡፡ በዚህ የተነሳ "በሥጋ ፈቃድ" ሳይሆን በመንፈስ መመላለስ ይማራሉ፡፡

**በዛሬ ጥናታችን የተመለከትናቸውን ጥቅሶች መልሰው ያንብቡ፡፡ ጳውሎስ እየተናገረ ካለው ነገር ጋር ራስዎን እንዴት ያዛምዱታል? ሮሜ 8፡1-2 አስደናቂ ተስፋ የሆነው ለምንድን ነው?**

## ሰኞ ሚያዝያ 29

## አምላካዊው ሕግ እና ኃጢአት

በትናንቱ ጥናታችን ክርስቲያኖችን ጨምሮ ሁሉም ሰው ኃጢአት የመሥራቱን እውነታ በሮሜ 7፡15-25 ተመልክተን ነበር፡፡ ሆኖም ጳውሎስ ከእነዚህ ቁጥሮች ቀደም ባሉት መልእክቱ ኃጢአት ምን ያህል ተስፋፊና ገዳይ መሆኑን ወደ ሕጉ በማመላከት ያሳየናል፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ሮሜ 7፡1-14፡፡ በሕጉ እና በኃጢአት መካከል ያለው ግንኙነት ምንድን ነው? በሕጉ አማካይነት መዳን የማይቻል ስለ መሆኑ በተጨማሪ ጥቅሶቹ ምን ይነግሩናል?**

________________________________________________

________________________________________________

ጳውሎስ በዚህ ስፍራ ከሚያስተምረው ትምህርት ሁለት ወሳኝ ነጥቦች ነጥረው ይወጣሉ፡፡ በመጀመሪያ ሕጉ ችግር አለመሆኑን ያሳየናል፡፡ ሕጉ "ቅዱስ፣ ጻድቅና መልካም ነው"፡፡ ስለዚህ ችግሩ ያለው ወደ ሞት የሚመራው ኃጢአት ላይ ነው፡፡ ሌላው ነጥብ ሕጉ እኛን ከኃጢአትና ከሞት ለማዳን ኃይል የሌለው መሆኑ ነው፡፡ ሕጉ የኃጢአትንና የሞትን ችግር ነቅሶ በማውጣት ይበልጥ ግልጽ አድርጎ ከማቅረብ ውጪ ለችግሩ መወገጃ የሚያቀርበው አንዳችም መፍትሔ የለም፡፡

ይህን መልእክት በጥልቀት ሳይሆን ላይ ላዩን የሚያነብ ብቻ ከእነዚህ ጥቅሶች ተነስቶ ሕጉ ማለትም አስሩ ትእዛዛት ተሽረዋል የሚል ሙግት ሊያነሳ ይችላል፡፡ ሕጉ ዛሬም ጸንቶ መኖሩን የሚያመላከቱ ኢያሌ ጥቅሶችን ችላ በማለት ይህ ሲፈጸም ይስተዋላል፡፡ እንዲህ ያለው አስተሳሰብ ጳውሎስ ካነሳው ነጥብ ፍጹም ተቃራኒ ነው፡፡ ሕጉ ተሽሮ ቢሆን ኖሩ ጳውሎስ በዚህ ስፍራ ትርጉም ያለው ነገር ባልጻፈ ነበር፡፡ የእርሱ መሚገቻ ነጥብ ሕጉ ዛሬ ድረስ

እንደ ጾና በመኖሩ ምክንያት ኃጢአትን በተጨባጭ እያሳየን ነው፤ በውጤቱም የወንጌልን አስፈላጊነት እንገነዘባለን "እንግዲህ ምን እንላለን? ሕግ በራሱ ኃጢአት ነውን? በፍጹም አይደለም፤ ነገር ግን በሕግ በኩል ባይሆን ኖሮ፣ ኃጢአት ምን እንደ ሆነ ባላወቅሁም ነበር፤ ሕጉ 'አትመኝ' ባይል ኖሮ፣ ምኞት ምን እንደ ሆነ በእርግጥ አላውቅም ነበር" (ሮሜ 7፡7)፡፡

**ጥቅሱን በጥንቃቄ ያንብቡ፡ ሮሜ 7፡13፡፡ ጳውሎስ ስለ ሕጉ ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ዛሬም አስፈላጊ ስለመሆኑ ምን እያለ ነው?**

ሞት የሚያስከትለው ሕጉ ሳይሆን ኃጢአት ነው፡፡ ኃጢአት ምን ያህል ገዳይ እንደሆነ የሚያሳየን ሕጉ ነው፡፡ ሕጉ መልካም በመሆኑ ወደ ኃጢአት ያመላክታል፡፡ ከዚህ ውጪ ከወንጌል በቀር ሕጉ ለኃጢአት መልስ የለውም፡፡ የጳውሎስ መልእክት--እንደ ክርስቲያን፣ በክርስቶስ እንደ ዳኑ ሕዝቦች "አዲስ በሆነው በመንፈስ መንገድ" (ሮሜ 7፡6) ልናገለግል ይገባል--የሚል ነው፡፡ አባባሉ ከየሱስ ጋር በእምነት ግንኙነት እየተመላለስን እርሱ ለእኛ በሠራው የጽድቅ ሥራና ባስገኘልን ደኅንነት እንታመን የሚል አንደምታ አለው፡፡

**ሕጉን የመጠበቅ የግል ተሞክሮዎ አምላካዊው ጸጋ እንደሚያስፈልግዎ ያሳዮት እንዴት ነው?**

## ማክሰኞ ሚያዝያ 30

## ከቅዳሜ ሰንበት ወደ እሑድ?

እንደ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስትነታችን በሌሎች የክርስትና ተቋም የሚገኑ ወንድምና እህቶች የሕጉ ጉዳይ እንዳበቃለት ሲናገሩ ወይም ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች አይደለንም የሚል የክርክር ሃሳብ ሲያነሱ እንሰማለን፡፡ በእርግጥ በትክክል እያሉ ያሉት--አራተኛው ትእዛዝ ብቻ ተወግዶአል ነው፡፡ እንዲያውም ብዙዎች የሚሉት እንዲህ ሳይሆን--ለየሱስ ትንሳኤ ክብር ለመስጠት ሲባል ሰባተኛው ቀን ሰንበት የሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን በሆነው እሁድ ተተክቶአል ነው፡፡

ይህን አባባላቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች እንደሚደግፉም ያስባሉ፡፡ ብዙ ክርስቲያኖች ሰንበት ከብሉይ ኪዳኑ ሰባተኛ ቀን ወደ አዲስ ኪዳን የመጀመሪያው ቀን ለመለወጡ አመለካች ናቸው ብለው የሚያምኑባቸው ጥቂት የአዲስ ኪዳን ጥቅሶች ከዚህ በታች ቀርበዋል፡፡ ጥቅሶቹን ስናነብ በእውነት ስለ ቀን መለወጥ የሚናገሩ መሆናቸውን ወይም የቀን ለውጥ ደረጃ ላይ ሳይደርሱ በዚያ ቀን ገቢራዊ የሆኑ ክስተቶችን ብቻ እየገለጡ እንደሆነ ራሳችንን መጠየቅ ያስፈልገናል፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ዮሐ. 20፡19-23፡፡ ደቀ መዛሙርቱ በዚያ ክፍል ውስጥ ለተሰባሰቡበት የቀረበው ምክንያት ምን ነበር? አንዳንዶች እንደሚሉት የየሱስን ዕርገት ለመዘከር የተደረገ የአምልኮ አገልግሎት ስለመሆኑ እነዚህ ጥቅሶች ምን ይነግሩናል?

---

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ሐዋ. 20፡ 6-7፡፡ ሰንበት ከቅዳሜ ወደ ሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን እሁድ ስለ መለወጡ የሚያሳይ አንዳች ነገር አለ? ሐዋ. 2፡46፡፡**

---

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ነቆሮ. 16፡1-4፡፡ በሣምንቱ መጀመሪያ ላይ በየቤቱ ይደረግ የነበረው የገንዘብ ማሰባሰብ መርኀ ግብር ሰንበት ወደ እሁድ ቀን ለመቀየሩ ምን የሚያስተምረው ነገር አለ?

---

የሣምንቱ የመጀመሪያው ቀን ሰባተኛውን ቀን ሰንበት የመተካቱን ኃይማኖታዊ አስተምህሮ ለማበረታታትና ለማዳበር ጥቅም ላይ የዋለው ዋንኛው የጥቅስ “ማስረጃ” ይዘት ይኸው ነው፡፡ አማኞች ለጥቂት ጊዜያት በተለያዩ ምክንያቶች መገናኘታቸው ከመገለጹ ውጪ ይህ መሰባሰባቸው ሰባተኛውን ቀን ሰንበት በመተካት በሣምንቱ መጀመሪያ ቀን የተደረገ የአምልኮ አገልግሎት መሆኑን አንድ እንኳ ጥቅስ አያመለክትም፡፡ እነዚህን ጥቅሶች በመከራከሪያ ነጥብነት የሚያቀርበውና ገና ከመጀመሪያው ፈጽሞ ያልነበረውን ሀሳብ በጥቅሶቹ ውስጥ ያኖረው የእሁድ አምልኮ ልማድና ወግ፤ በክርስትናው ዓለም አያሌ መቶ ዓመታት አስቆጥሮአል፡፡

## ረቡዕ ግንቦት 1

## ሰባተኛው ቀን በአዲስ ኪዳን

በትናንቱ ጥናታችን እንደ ተመለከትነው እሁድ በቅዳሜ ሰንበት የመተካቱን ጽንሰ ሃሳብ ለማራመድ በተለምዶ ጥቅም ላይ እየዋሉ የሚገኙ ጥቅሶች እንደሚባለው አይናገሩም፡፡ ይልቁንም በአዲስ ኪዳን ስለ ሰባተኛው ቀን ሰንበት የሚቀርቡ ማስረጃዎች ከእግዚአብሔር አስርቱ ትእዛዛት እንደ አንዱ ይጠበቅ እንደ ነበር ይፋ ያደርጉልናል፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ሉቃ. 4፡14–16፣ 23፡55-56፡፡ ከክርስቶስ ሞት በፊትም ሆነ በኋላ ስለ ሰባተኛው ቀን ሰንበት ምን ይነግሩናል?**

---

ከገሊላ ጀምሮ የመጡት ሴቶች “ሕጉ በሚያዘው መሰረት በሰንበት ቀን ዐረፉ” (ሉቃ. 23፡56) የሚለውን ጥቅስ ልብ ይበሉ፡፡ በእርግጥ ይህ ሕግ በሲና ተራራ ተጽፎ የተሰጠው አራተኛው ትእዛዝ ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ ደቀ መዛሙርቱ ከየሱስ ጋር በነበሩባቸው ጊዜያቶች የቱንም ዓይነት ትምህርት ቢማሩ ሰንበትን ጨምሮ የእግዚአብሔርን ሕግ ከመጠበቅ ውጪ የቀሰሙትን የሚጠቁም ነገር የለም፡፡ እንደውም ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን ያላቸው “‘ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ’ ” (ዮሐ. 14፡15) ነበር፡፡ እርሱ ራሱ የጠበቃቸው የራሱ ትእዛዛት ሰባተኛውን ቀን ሰንበት ያካተቱ ነበሩ፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ሐዋ. 13፡14፣ 42–44፣ ሐዋ. 16፡12- 13፡፡ ሰባተኛውን ቀን ሰንበት ስለ መጠበቅ ምን ዓይነት ማስረጃ ይሰጣሉ? የሣምንቱን የመጀመሪያ ቀን ስለ መጠበቅ የሚሰጡት ማስረጃስ ምንድን ነው?

---

የሰንበት ቀን ወደ እሁድ ስለ መቀየሩ ምንም ዓይነት ማስረጃ በጥቅሶቹ ተሰጥቶ አናገኝም፡፡ ይልቁንም ሰባተኛውን ቀን ሰንበት መጠበቅ በመጀመሪያዎቹ የየሱስ አማኞች መሃል ይተገበር እንደ ነበር በግልጽ ያመለክተናል፡፡

በተለይ ሐዋ. 16፡ 13 የቀረበው መልእክት ከተለመደው የቤተ ክርስቲያን ጉባዔ ዐውድ ወጣ ያለ በመሆኑ መሳጭ ነው፡፡ አማኞች በአንድ ወንዝ ዳር ተሰባስበው እንደ ልማዳቸው አምልኮ ያደርጉ ነበር፡፡ ከየሱስ ሞት እና ትንሣዔ አያሌ ዓመታት በኋላም እንኳ በሰባተኛው ቀን ሰንበት ለአምልኮ ይሰባሰቡ ነበር፡፡ በአምልኮ ቀን ላይ ለውጥ ለመደረጉ በእነዚህ ጥቅሶች የሚያመላክት አንዳችም ነገር የለም፡፡

**እሁድን እንደ ሰንበት በመቁጠር በዕለቱ አምልኮ የሚያደርጉትን በማይኮንን መንገድ ስለ ሰባተኛው ቀን ሰንበት መመስከር የሚችሉባቸው መንገዶች የትኞቹ ናቸው?**

## ሐሙስ ግንቦት 2

## ሰንበትን ለመለወጥ የተደረገ ሙከራ

የእግዚአብሔር ሕግ የሆኑት አስርቱ ትእዛዛት ዛሬ ድረስ ጸንተው ያሉ ሲሆን (ያዕ. 2፡10-12) ሰባተኛው ቀን ሰንበት ደግሞ የዚህ ሕግ አካል ነው፡፡ ታዲያ ብዙ ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ የሌለውን እሁድ ቀን የሚጠብቁት ለምንድን ነው?

ዳን. ምዕ. 7 ስለ አራቱ የዓለም ልዕለ ኃያላን መንግሥታት መነሳት ይናገራል፡፡ ባቢሎን፣ ሜዶንና ፋርስ፣ ግሪክ እንዲሁም በመጨረሻ ሮም፡፡ በሮም መንግሥት መጨረሻ አካባቢ አንድ ትንሽ ቀንድ (ኃይል) ከዚህ ልዕለ ኃያል መንግሥት ውስጥ ሲወጣ ተገልጾአል (ዳን. 7፡8)፡፡ ይህ ቀንድ የሮም መንግሥት ቀጣይ ምዕራፍ አካል በመሆን ዛሬ ድረስ አለ፡፡ በቀጥታ ከሮም የሚወጣው ኃይል ጳጳሳዊው ሥርዓት ከመሆን ውጪ ሌላ ምን ሊሆን ይችላል? ቶማስ ሆብስ ከአራት መቶ ዓመታት በፊት ማለትም በሺ ስድስት መቶዎቹ አካባቢ የሚከተለውን ጽፎ ነበር፡ "አንድ ሰው የዚህን ታላቅ የቤተ ክርስቲያን ተቋም አመጣጥ ለመመርመር ቢሞክር፤ ጳጳሳዊው ሥርዓት የዓለም ልዕለ ኃያል የነበረውና ግብአተ መሬቱ የተፈጸመው፣ የሮም መንግሥት መቃብር ላይ አክሊል የጫነ ቅሪተ አካል መሆኑን በቀላሉ መገንዘብ ይችላል፡፡"—*Thomas Hobbes, Leviathan, (Oxford: Oxford University Press, 1996), p. 463.*

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ዳን. 7፡23-25፡፡ የእሁድን ቀን አምልኮ መሰረታዊ አመጣጥ ማስተዋል እንችል ዘንድ ምን ያስተምሩናል?**

**የቀደመው አረማይክ ቋንቋ የትንሹ ቀንድ ኃይል ጊዜና ሕግን ለመለወጥ “ያቅዳል” ቁ. 25 ሲል ይጠቁማል፡፡ ለመሆኑ የእግዚአብሔርን ሕግ መለወጥ የሚችለው እንዴት ያለ ምድራዊ ኃይል ነው?**

ምንም እንኳ ከረጅሙ የታሪክ ሂደት አኳያ እያንዳንዱ ነጥብ በጉልህ መታየት ባይችልም ነገር ግን በሮም ጳጳሳዊው ሥርዓት ትእዛዝ ሰባተኛው ቀን ሰንበት በባህላዊው የእሁድ አምልኮ መተካቱን እናውቃለን፡፡ ይህ ባህላዊ ወግና ልማድ ሥር የሰደደ ከመሆኑ የተነሳ የፕሮቴስታንት ተሐድሶም እስከ ሃያ አንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጠብቆ አኑሮታል፡፡ ዛሬ አብዛኛው ሕዝበ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሰባተኛው ቀን የሚያዘውን በመከተል ፋንታ ዛሬም እሁድን እየጠበቀ ይገኛል፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 13፡1-17 እና ከሚከተሉት ጋር ያስተያዩ፡ ዳን.7፡1-8፣ 21፣ 24-25፡፡ የመጨረሻውን ጊዜ ክስተቶች ለማስተዋል የሚረዱን ምን ዓይነት ተመሳሳይነት ያላቸው ምስላዊ አቀራረቦች ጥቅም ላይ ውለዋል?**

---

የራእይ መጽሐፍ የሮምን ቀጣይ ምዕራፍ (ጳጳሳዊውን ሥርዓት) ያካተተውን የዳንኤልን ምስላዊ አቀራረብ በቀጥታ ጥቅም ላይ በማዋል በመጨረሻው ጊዜ የአስገዳጁን ኃይል “አምልኮ” በሚቃወሙ ላይ የሚደርሰውን ስደት ያመላክታል፡፡

**በራእ. 14፡ 6-7 በተለይ ከአራተኛው ትእዛዝ (ዘፀ. 20፡10) የተወሰደውን ቋንቋ የሚያንጸባርቀው ቁ. 7--ሰንበት በመጨረሻው ጊዜ ከአምልኮ ጋር በተያያዘ ለሚነሳው ብርቱ ቀውስ እጅግ ወሳኝ መሆኑን መመልከት እንድንችል አይረዳንም?**

## አርብ ግንቦት 3

**ተጨማሪ ሀሳብ፡** በምድር “የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የሚጠብቁ” (ራእ. 12፡17፣ 13፡2፣ 4) ሕዝቦች ላይ ጦርነት የከፈተው፤ በሰማይ አምላክ **እ**ግዚአብሔር ላይ ጦርነት አውጆ የነበረው ያው ዘንዶ ወይም ሰይጣን ነው (ራእ. 12፡7)፡፡ በእርግጥ ሰይጣን ራሱ ስግደት ይቀበላል (ራእ. 13፡4)፡፡ ስለዚህ ሰይጣን በእግዚአብሔር ላይ በሰማይ የጀመረውን ውጊያ በምድርም ለመቀጠል ብርቱ ምኞቱ ነው፡፡ በእግዚአብሔር ላይ ለከፈተው ጦርነት ዋንኛ ኢላማው ደግሞ ሕጉ ነው፡፡

“እግዚአብሔር ከሁሉም ሐሰተኛ አማልክት ተለይቶ የሰማይና የምድር ፈጣሪ ሆኖ በአራተኛው ሕግ ላይ ተገልጾአል፡፡ የፍጥረት ሥራ መታሰቢያ የሆነው ሰባተኛው ቀን ለሰው የዕረፍት ቀን ሆኖ ተቀደሰ፡፡ ዕለቱ ሕያው አምላክ ሁሌም በሰብዓዊው አእምሮ--የፍጥረት ባለቤት፣ የቅድስናና የአምልኮ ምልክት ሆኖ እንዲታሰብ ተነደፈ፡፡ ሰዎች ለእግዚአብሔር ያላቸውን ታማኝነት ለማስቀየስና ሕጉን በመታዘዝ ምላሽ እንዳይሰጡ ሰይጣን በመዋጋት ላይ ይገኛል፡፡ ስለዚህ በተለይ የእግዚአብሔርን ፈጣሪነት ከሚያመለክተው ትእዛዝ በተቃራኒ በመሥራት የተቻለውን ሁሉ ያደርጋል፡፡”—*Ellen G. White, The Great Controversy, pp. 53, 54.*

ጌታ “የሰማይና ምድር” ፈጣሪ በመሆኑ እናመልከዋለን፡፡ ሰባተኛው ቀን ሰንበት ደግሞ ወደ ኋላ እስከ ፍጥረት ሣምንት በመሄድ የፈጣሪነቱ ምልክት መሰረት መሆኑን ያሳያል (ዘፍ. 2፡1-3)፡፡ ሰይጣን በእግዚአብሔር ላይ የሚሰነዝረው ጥቃት አበይትና መሰረታዊ የሥልጣኑ ምልክት በሆነው፡ ሰባተኛ ቀን ሰንበት ላይ መሆኑ እምብዛም ላይደንቅ ይችላል፡፡

እግዚአብሔር በመጨረሻዎቹ ጊዜያቶች--ለአምልኮአችን ብቸኛ ዋጋ ያለውንና ጌታን እንደ ፈጣሪ የሚጠቅሰውን ትእዛዝ ጨምሮ ሁሉንም ትእዛዞች በመጠበቁ ረገድ ጽኑና የማያወላውል አቋም ያላቸው ሕዝቦች ይኖሩታል፡፡

## የመወያያ ጥያቄዎች፡

1.በአንድ በኩል ስለ ኃጢአት መኖር እያወሩ በሌላው የእግዚአብሔር ሕግ ተወግዷል የሚሉ ሰዎች ችግር ምንድን ነው? በእንዲህ ዓይነቱ ነገረ አስተሳሰብ ውስጥ ምን ዓይነት እርስ በርስ የሚጻረሩ ነጥቦችን ማውጣት ይችላሉ?

2.በቅዳሜ ሰንበት ፋንታ እሁድን ከሚጠብቁ ሰዎች ጋር ያደረጓቸው ሙግቶች ተሞክሮ ምን ይመስላል? ለመሟገቻ የተጠቀሟቸው ነጥቦች ምን ይመስላሉ? ምን ያህልስ ውጤታማ ነበሩ? ሰባተኛውን ቀን ሰንበት መጠበቅ በጸጋ ሳይሆን በሥራ ለመዳን መሞከር ነው በሚል የሚነሳውን የተለመደ ሙግት የሚጋፈጡበት መንገድ ምን ይመስላል?

3.ለመጨረሻው ጊዜ በምናደርገው ዝግጅትና ሰንበትን አስመልክቶ ከሌሎች ጋር በምናደርገው የሃሳብ መለዋወጥ በ “አውሬው ምልክት” ዙሪያ የሚነሱ ፈታኝ ነጥቦች ገና ገቢራዊ አለመሆናቸውን ግልጽ ማድረግ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?

# ሰባተኛ ትምህርት

ከግንቦት 4- 10

## የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 24-25

**ሰንበት ከሰዓት**

***ለዚህ ሳምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ማቴ.*** *24:1–25፣ ራእ. 13:11–17፣ ማቴ. 7:24–27፣ ሉቃ. 21:20፣ ማቴ. 25:1–30፡፡*

**የሳምንቱ ጥናት መሪ ጥቅስ:**

**" 'ሐሰተኛ ክርስቶሶችና ሐሰተኛ ነቢያት ይነሣሉና፤ ቢቻል የተመረጡትን ለማሳት ሲሉ ታላላቅ ምልክቶችንና ታምራትን ያደርጋሉ' " (ማቴ. 24፡24)**

የሱስ ስለ መጨረሻዎቹ ጊዜያቶችና እንዴት ለወደፊቱ መዘጋጀት እንዳለብን አስመልክቶ በማቴ. ምዕ. 24 እና 25 አስፈላጊ እውነቶችን ይገልጽልናል፡፡ እነዚህ ምዕራፎች ክርስቶስ ስለ መጨረሻዎቹ ጊዜያቶች የተወልን ትምህርቶች ናቸው ቢባል ያስኬዳል፡፡ የሱስ ስለ እነዚያ የምድር መጨረሻ ክስተቶች እየተናገረ ወዲያው ደግሞ እርሱ ከነበረበት ዘመን ብዙም ሳይርቅ ሊሆን ያለውን የየሩሳሌምን ጥፋት እና በሕዝቡ ላይ የሚደርሰውን እልቂት እንዲሁ ተመልክቶ ነበር፡፡

ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ የሰጣቸው መልእክት ከእነርሱ በኋላ ለሚመጡ ትውልዶችም ሆነ በተለይ ደግሞ ከዳግም ምጽአቱ አስቀድሞ ባሉ የመጨረሻዎቹ ዘመናትና በምጽአቱ ወቅት ለሚኖሩ ሕዝቦች ገጣሚ ናቸው፡፡ የሱስ መጪውን ጊዜ ሲስል ሁሉም ነገር አልጋ በአልጋ እና ምቹ ይሆናል አላለም፡፡ ይልቁንም የጦርነት ወሬ፣ መቅሰፍት፣ ሐሰተኛ ክርስቲያኖች እና ስደት የዓለም ብሎም የቤተ

ክርስቲያኑ ዕጣ ፈንታ ይሆናል ሲል ነው ያስጠነቀቀው፡፡ ወደ ኋላ መለስ ብለን በዘመናት የሆኑትን በመቃኘት የየሱስ ትንቢቶች ምን ያህል ትክክል እንደ ነበሩ በአግራሞት መመልከት እንችላለን፡፡ በዚህ የተነሳ በእኛ ዘመንም ሆነ ከእኛ በኋላ ፍጻሜ ለሚያገኙት ትንቢቶች ልናምነው እንችላለን፡፡

ይሁን እንጂ የሱስ ወደ ፊት ስለሚመጣው ነገር እንደው ማስጠንቀቂያ ብቻ አልተወም፡፡ በማቴ. 25 ከቀረቡት የየሱስ ምሳሌያዊ አባባሎች መመልከት እንደምንችለው--ምክሩን የሚሰሙና የሚያከብሩ "'የሰው ልጅ'" በሚመጣ ጊዜ ዝግጁ ሆነው መጠበቅ ይችላሉ፡፡ አዎ--አስቸጋሪ ጊዜያቶች ይመጣሉ፤ ነገር ግን እርሱ ዳግም በሚገለጥበት ጊዜ የሚገናኙትን ሕዝቦች ያዘጋጃል፡፡

## እሑድ ግንቦት 5

## ትንቢት ማረጋገጫ ብርቱ መንገድ

ከመስቀሉ አስቀድሞ በነበሩት የመጨረሻዎቹ ቀናት ደቀ መዛሙርቱ በደብረ ዘይት ተራራ ከየሱስ ጋር ተነጋግረው ነበር፡፡ የሱስ ቤተ መቅደሱ እንደሚወድም ሲናገር እርስዎ በዚያ ቦታ ቢኖሩ ሊሰማዎ የሚችለውን ስሜት በዓይነ ኅሊናዎ ለመሳል ይሞክሩ፡፡ ደቀ መዛሙርቱ ይህን ሲሰሙ በትክክል በአእምሮአቸው የነበረውን ነገር ለማወቅ ባይቻልም ነገር ግን ይህን ተከትሎ የጠየቋቸው ጥያቄዎች የቤተ መቅደሱን መውደም ከ" 'ዓለም መጨረሻ' " (ማቴ. 24፡3) ጋር እንዳያያዙት የሚያሳዩ ነበሩ፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ ማቴ. 24፡ 1-25፡፡ የሱስ ስለ መጨረሻዎቹ ቀናት አስመልክቶ ለተከታዮቹ የሰጣቸው ጠቅለል ያሉ መልእክቶች ምንድን ናቸው?**

ክርስቶስ ወደ ኋላ ከረጅም ዘመናት አንስቶ እስከ መጨረሻው ጊዜ ድረስ ሕዝቡን ግራ የሚያጋቡ ማታለያዎች እንዳሳሰቡት ማቴ. 24፡1-25 በግልጽ ያስቀምጥልናል፡፡ ከእነዚህ ማታለያዎች መካከል ሐሰተኛ ነቢያትና ክርስቶሶች ይገኙበታል፡፡ አንዳንዶች ክርስቶስን እንወክላለን እስከ ማለት ሲደርሱ (ሐሰተኛ ነቢያት) ሌሎች ደግሞ ጭራሽ ክርስቶስ ነኝ ብለው ይመጣሉ፡፡ ታዲያ በእጅጉ የሚያሳዝነው ሰዎች እነርሱን ማመናቸውና መከተላቸው ነው፡፡

በእርግጥ አንዳንድ አሳዛኝ ክስተቶችን ብንመለከትም ነገር ግን ክስተቶቹ የእግዚአብሔርን ቃል በብርቱ የሚያረጋግጡልን ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ በቀድሞዎቹ ዘመናት እንዲሁም ዛሬ በእኛ ዘመን አሳቾች "እኔ ክርስቶስ ነኝ" ብለው ተነስተዋል፡፡ እንዴት አስገራሚ ትንቢት ነው! እኛ በዚህ ዘመን መፈጠራችን ከብዙ ምዕተ ዓመታት አስቀድሞ የነበሩትን ታሪኮች በመቃኘት (በክርስቶስ ዘመን የነበሩት ያልታደሉትን) ትንቢቱ ምን ያህል ትክክል እንደ ሆነ መመልከት እንችላለን፡፡ ወደ መጨረሻው ቀውስ ስንቃረብ እንደነዚያ ዓይነቶቹ ማታለያዎች እየጨመሩ ይሄዳሉ፡፡ ስለዚህ በዚህ ጉዳይ ፈጽሞ መደነቅ የለብንም፡፡

እንዲሁም የሱስ ከአዎንታዊው የእምነት ዐውድ አኳያ የዓለምን ሁናቴ የገለጸበትን መንገድ ይመልከቱ፡፡  ከክርስቶስ አንስቶ ባለው የምድር የተለያዩ ዘመናት ታሪክ ሰዎች የሰብዓዊው ዘር ሥቃይና እንግልት እንዲጠፋ ወይም ቢያንስ በከፍተኛ ደረጃ እንዲቀንስ ያደርጋሉ ብለው በሚያምኑባቸው ነገሮች ላይ ተስፋቸውን አኑረዋል፡፡ ሰዎች በአንድ ወቅት የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች፣ የቴክኖሎጂ ምጥቀት ወይም የሳይንስ ግስጋሴ አልያም አመክንዮ--ፍጹም ወደ ሆነ ዉሁድና ስምሙ ዓለም ያገባናል የሚል ታላቅ ተስፋ ሰንቀው ነበር፡፡ ነገር ግን እነዚህ ተስፋዎች ሁሌም ቢሆን የተመሰረቱት ጤነኛ ባልሆነ መሰረት ላይ ለመሆኑ በሥቃይ የተሞሉት የታሪክ ተሞክሮዎች በተደጋጋሚ ምስክር በመሆን

አሳይተዋል፡፡ ዛሬ ይህች ዓለም የሱስ ይሆናል ብሎ በተናገረበት ሁናቴ ላይ ትገኛለች፡፡ እነዚያ ከሁለት ሺ ዓመታት በፊት ከየሱስ አንደበት የወጡ ቃላት ሰብዓዊዎቹ ተስፋዎች ምን ያህል በስህተት የተመሩ እንደሆኑ ያሳያሉ፡፡

**ጥቅሱን ያንብቡ፡ ማቴ. 24፡ 25፡፡ እምነታችን እንዲጠነክር ሊረዳ ከሚችለው ከዚህ አባባል ምን መውሰድ እንችላለን?**

## ሰኞ ግንቦት 6

## እስከ መጨረሻው መታገስ

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ማቴ. 24፡9፣ ራእ. 13፡11-17፡፡ የሱስ በማቴዎስ ወንጌል በተናገረውና ዮሐንስ በራእይ መጽሐፍ እንዲጽፍ ካነሳሳው ሃሳብ ጋር ምን ዓይነት ትይዩነት ይስተዋላል?**

---

---

በመጨረሻዎቹ ጊዜያቶች ገቢራዊ ከሚሆኑትና የሱስን ከሚያሳስቡት ጉዳዮች አንዱ መንግሥታት እውነትን እንዲቃወሙና በዓለም ላይ የሐሰት አምልኮዎች እንዲተገብሩ የሚያደርጉ ዓለማቀፋዊ ማሳቻዎች ናቸው፡፡ ለእውነት ጸንተው የሚቆሙ ጥላቻ፣ መከራ--ባስ ሲልም ሞት ይደርስባቸዋል፡፡

**ጥቅሱን ያንብቡ፡ ማቴ. 24፡13፡፡ በዓለማቀፍ ተቃውሞ መሃልም እንኳ ለመዳንም ሆነ ታማኝ ለመሆን ቁልፉ ምንድን ነው?**

---

---

"አእምሮአቸውን በመጽሐፍ ቅዱሳዊው እውነት ያጠነከሩ ወገኖች በታላቁ ውዝግብ መሃል እስከ መጨረሻው ጸንተው ይቆማሉ፡፡"—*Ellen G. White, The Great Controversy, p. 593.* አባባሉ--አእምሮአቸውን በመጽሐፍ ቅዱሳዊው

እውነት ምሽግ ውስጥ ያኖሩ ሁሉ በማንኛውም የመጨረሻው ጊዜ ማታለያ ተጠርገው አይወሰዱም የሚል አንደምታ አለው፡፡ ለዚህ ዘመን የተሰጠውን እውነት መሰረተ ሀሳብ አጥብቀው ካልያዙ በቀር ማታለያዎቹ ለያነሆልሏቸው ይችላሉ፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ማቴ. 7፡24-27፡፡ ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆኖ ለመቀጠል ሌላው ወሳኝ ነገር ምንድን ነው?**

---

---

በአምላካዊው ቃል ዕውቀት ብልህ ሆኖ መሞላት አስፈላጊ ቢሆንም ነገር ግን የሱስ እንደሚለው ወደ ፊት የምንጋፈጠውን መከራ ለመቋቋም ያ ብቻውን በቂ አይደለም፡፡ የተማርነውን ነገር በተግባር ማዋል ከእኛ ይጠበቃል፡፡ ይህ ማለት የሱስ እንዳደረገው ሁሉ እኛም እውነትን መታዘዝ ይኖርብናል፡፡ ከላይ በቀረበው ምሳሌያዊ አነጋገር ሁለቱም ቤት ሠሪዎች የየሱስን ቃል ሰምተዋል፡፡ በሁለቱ መካከል የነበረው ልዩነት የጽናት ጉዳይ ሲሆን ይኸውም የሱስ አስተምሮ የነበረውን መታዘዝ ነው፡፡

**የሚታዘዝ ሰው ጸንቶ ሲቆም የማይታዘዘው ግን የሚወድቀው ለምንድን ነው? አንድ ሰው በእምነቱ ጸንቶ እንዲቆም በማድረጉ ረገድ መታዘዝ የሚያመጣው ለውጥ ምንድን ነው?**

## ማክሰኞ ግንቦት 7

## "የጥፋት ርኩሰት"

ክርስቶስ ስለ መጨረሻው ጊዜ ባደረገው ታላቁ ንግግር ከዳንኤል መጽሐፍ (ዳን. 9፡27፤ 11፡31፤ 12፡11) በመውሰድ ወደ "የጥፋት ርኩሰት" (ማቴ. 24፡15) ያመላከታል፡፡

እግዚአብሔር “ርኩሰት” የሚለውን ቃል ጥቅም ላይ የሚያውለው በሕጉ ላይ ከፍተኛ ጥሰት ሲደርስ ይኸውም እንደ ጣዖት አምልኮ (ዘዳ. 27፡15) ወይም በተመሳሳይ ጾታ መካከል የሚደረግ አጸያፊ ግንኙነት ሲከሰት ነው፡፡ ስለዚህ ይህ “የጥፋት ርኩሰት” አንድ የሆነ ኃይማኖታዊ ክህደትን ያካትታል፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ማቴ. 24፡15፣ ሉቃ. 21፡20፡፡ ጥቅሶቹ የሱስ ከ “ጥፋት ርኩሰት” ጋር በተያያዘ የተናገረውን በተሻለ እንድናስተውል የሚረዱን እንዴት ነው**

---

---

እነዚህ ሁለት ጥቅሶች በየሱስ ትንቢቶች መሰረት ብዙም ሳይቆይ 70 ዓ.ም. ላይ አረማዊው ሮም የሩሳሌም ከተማን ብቻ ሳይሆን ቅዱስ የነበረውንም ቤተ መቅደስ በማውደም ያደረሰውን አስከፊ ጥፋት በማካተት ያቀርባሉ፡፡

የሆነው ሆኖ እንደ የሩሳሌም ውድመት ዓይነት የወደፊቱና የመጨረሻው ጊዜ ክስተቶች ሆነው የሚቆዩና በቅርብ ገቢራዊ የሚሆኑ የዚህ ትንቢት ዳግመኛ ፍጻሜዎች አሉ፡፡ “ክርስቶስ በየሩሳሌም የተመለከተው ባለማመን ልቡ የደነደነው የዐመጸኛው ዓለም ተምሳሌት፤ አምላካዊውን ፍርድ በፍጥነት ለመቀበል ተጣድፎ ነበር”—Ellen G. White, *The Great Controversy,* p. 22.

በዳን. 12፡11 እና 11፡31 የምናገኘው “የጥፋት ርኩሰት” የሚገለጠው በቀጣዩ የሮም ዕድገት ደረጃ ወይም ምዕራፍ በምናገኘው ጳጳሳዊ ሥርዓት ነው፡፡ በዚህ ሥርዓት አማራጭ የአምልኮና የደኅንነት ህግ በመደንገግ ክርስቶስ በሰማያዊው መቅደስ ለእኛ ያደረገልንንና አሁን እያደረገልን ያለውን--ከሥልጣኑ ውጪ የራሱ ለማድረግ ይሻል፡፡

ዳን. 8 በተለይም ከቁ. 9-12 ክስተቶቹን ከራሳቸው የታሪክ ዐውድ ማለትም ሁለት ምዕራፎች ወይም ደረጃ ካለው የሮም ሥልጣን አኳያ በመመደብ እገዛ ያደርጋሉ፡፡ በትንሹ ቀንድ ፈጣን የአግድሞሽ መስፋፋት የተስተዋለበት (ዳን. 8፡9) ይህ

የመጀመሪያ ምዕራፍ የአረማዊውን ሮም ፈጣን ግስጋሴ ያሳያል፡፡ በሁለተኛው ምዕራፍ (ዳን. 8፡10-12) ትንሹ ቀንድ አንዳንድ ከዋክብትን ቁልቁል እየጣለና (የእግዚአብሔርን ሕዝቦች እያሳደደ) ራሱን "ከሰማይ ሰራዊት አለቃ" ይኸውም ከየሱስ እኩል ከፍ ከፍ እያደረገ በፍጥነት ሽቅብ ያድጋል፡፡ ይህ ሁኔታ አረማዊውን ሮም አሽመድምዶ ከእርሱ ላይ ብቅ ያለውንና ዛሬ ድረስ በሮም ጸንቶ ያለውን ጳጳሳዊ ሥርዓት የዕድገት ደረጃ ይወክላል፡፡ (ተመሳሳይ ኃይል የነበራቸው ሁለቱ የዕድገት ደረጃዎች ትንሹ ቀንድ በሚል አንድ ዓይነት ተምሳሌታዊ አገላለጽ የተወከሉበት ምክንያት ይኸው ነው፡፡) በዳን. 7፡9-10 የምናገኘው ፍርድ፣ በዳን. 8፡14 የቀረበው የቤተ መቅደሱ መንጻት እንዲሁም በማቴ. 24፡29 የቀረቡት የሰማይ ኃይላት መናጋት ምልክቶች በመጨረሻዎቹ ቀናት እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ የሚያደርገውን ጣልቃ ገብነት ያሳያሉ፡፡

## ረቡዕ ግንቦት 8

## አሥሩ ልጃገረዶች

የሱስ በማቴ. 24 ስለ ዳግም ምጽአቱ ምልክቶች ሰፊ ንግግር ካደረገ በኋላ በማቴ. 25 ደግሞ ለዚያ ጊዜ እንዴት መዘጋጀት እንደሚገባ ይናገራል፡፡

**ስለ አስሩ ልጃገረዶች በተምሳሌት የሚናገሩትን የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ማቴ. 25፡1-13፡፡ የሱስ ለዳግም ምጽአቱ እንዴት መዘጋጀት እንዳለብን ሊረዳን የሚችል ምን ዓይነት ነገር እየነገረን ነው?**

---

---

የሱስ ስለ አሥሩ ልጃገረዶች በማውሳት የመጀመሪያ ንግግሩን ምዕራፍ ይከፍታል፡፡ " 'ልጃገረዶች' " በሚል ጥቅም ላይ የዋለው ቃል የጌታን አዳኝነት በግል ተቀብለው ራሳቸውን ክርስቲያን ብለው የሚጠሩ ወገኖችን ይወክላል፡፡

እነዚህ ሰዎች በታላቁ ውዝግብ ወቅት ከሰይጣን በኩል አልቆሙም፡፡ ይልቁንም ለሰማያዊው መንግሥት ገጣሚዎች ናቸው (ማቴ. 25፥1)፡፡ ነገር ግን በመጨረሻው ጊዜ ሁሉም አንቀላፉ (ማቴ. 25፥5)፡፡ ክርስቶስ ደግሞ ሳንዘጋጅ ዳግመኛ እንዳይገለጥ--ሁሌም ተግቶ ወይም ነቅቶ መጠበቅ እንደሚገባ አስጠንቅቆአል (ማቴ. 24፥42)፡፡

መብራታቸውን የያዙት አሥሩም ልጃገረዶች ሙሽራውን ለመቀበል ወጡ፡፡ ይህም ሁሉም ዳግም ምጽአቱን አሻግረው እየተመለከቱ እንደሆን ያሳያል፡፡ ሆኖም ሙሽራው በመዘግየቱ በመምጣቱ ላይ እምነት የነበራቸው ወገኖች እንቅልፍ ተጫጫናቸውና ተኙ፡፡ ሳይታሰብ እኩለ ሌሊት ላይ የሙሽራው መምጣት ስለ ተሰማ ሁሉም ከተኙበት ተቀሰቀሱ (ማቴ. 25፥1-6)፡፡

ያልተዘጋጁትና ዝንጉዎቹ ልጃገረዶች ግን በሆነው ነገር ተደነባበሩ፡፡ ለምን? "'መብራታችን ሊጠፋብን ስለሆነ" (ማቴ. 25፥8) በሚል፡፡ ይህ አባባላቸው መብራታቸው እየደበዘዘ መሄዱን እንጂ መጥፋቱን አይገልጥም፡፡ ያላቸው ዘይት አነስተኛ በመሆኑ ክርስቶስን ለመገናኘት የሚያስችለውን ዝግጅት ለማድረግ አይበቃቸውም፡፡

ታዲያ ችግሩ ያለው ምኑ ላይ ነው?

እነዚህ ልጃገረዶች ከክርስቶስ ጋር ጥልቅ የግንኙነት ተሞክሮ ሳይኖራቸው የክርስቶስን ዳግም ምጽአት ይጠባበቁ የነበሩ ክርስቲያኖችን ይወክላሉ፡፡ ጥቂቱ ዘይት--በሕይወታቸው የሚስተዋለው ደብዛዛ የመንፈስ ሥራ በእጅጉ አነስተኛ ከመሆኑ የተነሳ ሊጠፋ መቃረቡን ያሳያል፡፡ የሚያስፈልጋቸው መጠን ብዙ ሆኖ ሳለ እነርሱ ግን በጭላጭ ረክተው ነበር፡፡

"መንፈስ እንደ ራሱ መሻትና እንደፈቃዱ በሰብዓዊው ልብ ውስጥ በመሥራት አዲሱን ተፈጥሮ ያኖራል፡፡ በዝንጉዎቹ ልጃገረዶች የተወከሉት አማኞች ግን ጥልቀት በሌለው ተግባር ረክተው ነበር፡፡ እግዚአብሔርን አያውቁትም፡፡

የአምላካዊውን ባህሪ ምንነት ባለማጥናታቸው ከእርሱ ጋር አንድነት አልነበራቸውም፡፡ በዚህ የተነሳ እንዴት በእርሱ እንደሚታመኑ፣ አመለካከታቸውን በእርሱ ላይ እንደሚያደርጉም ሆነ እንደ ፈቃዱ እንደሚኖሩ አያውቁም፡፡ ለእግዚአብሔር የሚሰጡት አገልግሎት መልክ ብቻ በመያዙ ቁልቁል አሽቆልቁሎአል፡፡"—*Ellen G. White, Christ's Object lessons, p. 411.*

**ዝንጉዎቹ የሠሩት ዓይነት ስህተት እንዳንሠራ ወደ ራሳችን መመልከት የምንችልባቸው መንገዶች የትኞቹ ናቸው? ራስዎን ከእነርሱ በተመሳሳይ የሚያገኙ ከሆነ ከዚህ ሁናቴ ማምለጥ የሚችሉት እንዴት ነው?**

## ሐሙስ ግንቦት 9

## ስጦታዎችዎን ጥቅም ላይ ማዋል

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ማቴ. 25፡13-30፡፡ ለክርስቶስ ዳግም ምጽአት ከመዘጋጀት አኳያ መክሊቶቻችንን ጥቅም ላይ ማዋላችን ምን ዓይነት ሚና አለው?**

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

ምንም እንኳ የሱስ በዚህ ቦታ የሚጠቀመው ምሳሌያዊ አባባል ቀደም ካለው የተለየ ቢሆንም ነገር ግን ሁለቱም የሚናገሩት ለክርስቶስ ዳግም ምጽአት ስለመዘጋጀት ነው፡፡ የሁለቱም ሀሳብ የሚያጠነጥነው ስለተዘጋጁና ስላልተዘጋጁት ነው፡፡ እንዲሁም ከራሳቸው መንፈሳዊ ቸልተኝነት የተነሳ ከዘላለማዊ ጥፋት ጋር መጋፈጣቸውን ሁለቱም ምሳሌያዊ አባባሎች ያሳዩናል፡፡

ከአሥሩ ልጃገረዶች ጋር በተያያዘ የቀረበው ዘይት መንፈስ ቅዱስን ይወክላል፡፡ በማቴ. 25፡15 "ታላንት" በሚል የቀረበው ቃል ደግሞ የተወሰደው ከግሪክኛው *ታላንታ* ሲሆን "የወርቅ ቦርሳ" የሚል ፍቺ አለው፡፡ "ታላንት ሁሉንም

የተፈጥሮ ስጦታዎች ጨምሮ የተለያዩ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ይወክላል፡፡"—*The SDA Bible Commentary, vol. 5, p. 510.*

በተምሳሌታዊ አባባሎቹ የቀረቡት ሁሉም አገልጋዮች ከጌታቸው ንብረት ተቀብለዋል፡፡ እዚህ ላይ እነርሱም "'ለእያንዳንዱ እንደ ችሎታው በመደልደል' " (ማቴ. 25፡15) ዐደራ የተቀበሉ የጌታቸው ንብረት መሆናቸውን ልብ ይሏል (ማቴ. 25፡14)፡፡ ንብረቱ የተሰጣቸው በዐደራ እንደመሆኑ፤ የራሳቸው ላልሆነው ንብረት ዐደራ ተቀባይ መጋቢዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ ጌታቸው ተመልሶ በመጣ ጊዜ " 'የሰጣቸውን ገንዘብ ተሳሰበ' " (ማቴ. 25:19)፡፡

የመንፈሳዊ ስጦታዎች ምንጩ መንፈስ ቅዱስ ነው (1ቆሮ. 12:1–11፣ 28–31፣ ኤፌ. 4:11)፡፡ አነስተኛ ስጦታ እንዳላቸው ለሚያስቡ ወገኖች መልካም የምስራች አለ፡፡ መቼም ያለ ሰጪ ስጦታ መቀበል አይቻልም፡፡ ስለዚህ እነዚህ ሰዎች ታላቅ ስጦታ የሆነውን መንፈስ ቅዱስ በመቀበል ስጦታቸውን መውሰድ ይችላሉ፡፡

ስጦታዎች አንዴ በክርስቶስ የእኛ ሆነው የተሰጡን ቢሆንም ነገር ግን የልከኛው ንብረት ባለ ዐደራ መሆን መንፈስ ቅዱስን በመቀበልና ራስን ለእርሱ በማስገዛት ላይ መተማመን ያደርጋል፡፡ ትርፋማ ያልነበረው ባለ ዐደራ አገልጋይ ስህተት እዚህ ላይ ነበር፡፡ ግለሰቡ የሚያገላብጠው ዐደራ ቢሰጠውም እርሱ ግን ከመሰወር ውጪ ፈጽሞ አላንቀሳቀሰውም፡፡ በለጋስነት የተሰጠውን ዐደራ በሆነ መንገድ ለማበልጸግ ምንም ጥረት አላደረገም፡፡ በዚህ የተነሳ "'አንተ ክፉ፣ ሰነፍ አገልጋይ' " (ማቴ. 25፡26) በማለት የሱስ ሲኮንነው ይስተዋላል፡፡

***የሱስ ይህን ተምሳሌታዊ አባባል የተጠቀመው ከመጨረሻው ጊዜ እና ከእርሱ መመለስ ዐውድ ነበር፡፡ ለመጨረሻዎቹ ቀናት ለመዘጋጀት ስጦታዎቻችንን ጥቅም ላይ ማዋላችን ወሳኝ መሆኑን አስመልክቶ ይህ ምን ያስተምረናል?***

## አርብ ግንቦት 10

**ተጨማሪ ሀሳብ፡** “አንድ ታላንት የተቀበለው ሰው ‘መሬት ቆፍሮ የጌታውን ገንዘብ ደበቀ’፡፡ ግለሰቡ ከሁሉም አነስተኛውን ስጦታ ቢቀበልም ሊያበለጽገው ግን አልወደደም፡፡ አባባሉ የተሰጠኝ ስጦታ አነስተኛ ነው በሚል ሰበብ ራሳቸውን ከክርስቶስ አገልግሎት ለማግለል የሚሞክሩትን ያስጠነቅቃል፡፡ ጥቂት ላቅ ያሉ ነገሮችን ቢያደርጉ አብልጠው በደስታ መንቀሳቀስ በቻሉ ነበር፡፡ ጥቃቅን ነገሮችን ብቻ ማስተናገዳቸው አንዳችም ድርሻ እንደሌላቸው አድርገው ራሳቸውን እንዲቆጥሩ መንስኤ ሆኗቸዋል፡፡ በዚህ ምክንያት ስህተት እየሠሩ ይገኛሉ፡፡ ጌታ ስጦታዎችን ሲሰጥ በባህሪ ላይ ፍተሻ ያደርጋል፡፡ የተሰጠውን ታላንት ለማበልጸግ ችላ ያለው ግለሰብ እርሱ ራሱ ታማኝ አገልጋይ አለመሆኑን አስመስክሯል፡፡ አምስት ታላንት ተሰጥቶት ቢሆን ኖሮ መሬቱን ምሶ አንዱን እንደቀበረ ከመሰወር ውጪ አያበለጽገውም ነበር፡፡ በአንዱ ታላንት ላይ ያሳየው አግባብ የጎደለው አጠቃቀም የሰማይን ስጦታ መናቁን አመላክቶአል፡፡

“‘ በትንሽ ነገር ታማኝ የሆነ በትልቁም ይታመናል’ ሉቃ. 16፡10፡፡ ብዙውን ጊዜ ትናንሾቹ ነገሮች ዝቅ ተደርገው ስለሚታዩ ተገቢው ዋጋ አይቸራቸውም፡፡ ነገር ግን ለአብዛኛው የሕይወት እውነተኛ ግብረገብ ስንቅ የሚሆኑት እነርሱ ናቸው፡፡ በእርግጥ በክርስትና ሕይወት ፋይዳ ቢስ የሚባሉ ስጦታዎች የሉም፡፡ የትናንሾቹን ነገሮች አስፈላጊነት ዝቅ እያደረግን የምንመለከት ከሆነ ባህሪ የማነጽ ሥራችንን በአደጋ የተሞላ እናደርገዋለን፡፡”—Ellen G. White, *Christ’s Object Lessons*, p. 356.

## የመወያያ ጥያቄዎች፡

1.ሰዎች ማንኛውም ነገርም ሆነ ሰው ፍጹም በሆነ ሰላምና ውህደት የሚሠራበት ዓለም (utopia) በዚህ ምድር ገቢራዊ ይሆናል ብለው እንዲያምኑ ያደረጓቸው አንዳንዶቹ ርዕዮተ ዓለሞችና ጽንሰ ሃሳቦች ምንድን ናቸው? እነዚህ ጽንሰ ሃሰቦች ምን ነበሩ? ዋጋ ቢስ ሆነው የቀሩት ለምንድን ነው?

2.እግዚአብሔር አድርጉ ብሎ የነገረንን መታዘዛችን እምነታችንን ማጠንከር የሚችለው እንዴት ነው? ይህ ማለት እምነት ያለ ሥራ "ሙት" (ያዕ. 2፡26) የሆነው ለምንድን ነው? "የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁ" (ራእ. 14፡12) ሕዝቦችን ወደፊት የሚጠብቃቸውን አስቸጋሪ ሁናቴ ከግምት በማስገባት--ገና ነው ብለን ለምናስበው ግን በደጃፋችን ላለው ሁናቴ ከወዲሁ ዝግጅት ማድረጋችን በጣም አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?

3.ስለ አሥሩ ልጃገረዶች ጠለቅ አድርገው ለማሰብ ይሞክሩ፡፡ የእነርሱ ታሪክ በቀጥተኛም ሆኖ በሌሎች ፈርጀ ብዙ መንገዶች ለእኛ እንደ ማስጠንቀቂያ ሆኖ የቀረበው ለምንድን ነው? እንደ ዝንጉዎቹ ልጃገረዶች ራሳችንን እያታለልን ላለመሆኑ እንዴት እርግጠኞች መሆን እንችላለን?

4.ቢቻል "የተመረጡትን" ለማሳት--ሲል ምን ማለቱ ነው? "የተመረጡ" ለሚለው ቃል ያለን ግንዛቤ ምን ይመስላል? (ማቴ. 24፡24፣ ሮሜ 33፣ ቆላ. 3፡21)፡፡ በመጨረሻዎቹ ጊዜያቶች የሚስተዋሉት የማሳቻ መንገዶች ምን ያህል ታላቅ መሆናቸውን ይህ ምን ይነግረናል?

# ስምንተኛ ትምህርት

ከግንቦት 11 – 17

## ፈጣሪን ማምለክ

### ሰንበት ከሰዓት

***ለዚህ ሳምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ራእ.** 14:6-7፣ ማቴ. 24:14፣ **ገላ.** 3:22፣ ሉቃ. 23:32–43፣ ዘፍ. 22:12፣ ራእ. 14:8–12፡፡*

**የሳምንቱ ጥናት መሪ ጥቅስ፡-**

**"ከዚያም ሌላ መልአክ በሰማይ መካከል ሲበር አየሁ፤ እርሱም በምድር ላይ ለሚኖሩ ለሕዝብ፣ ለነገድ፣ ለቋንቋና ለወገን ሁሉ የሚሰበከውን የዘላለም ወንጌል ይዞ ነበር" (ራእ. ራእ. 14፡6)።**

እኛ እንደ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ክርስቲያንነታችን በመጽሐፍ ቅዱሳዊው ወቅታዊ እውነት ጽንሰ ሀሳብ እናምናለን (2ጴጥ. 1፡12)፡፡ ይህ ጽንሰ ሃሳብ እግዚአብሔር አስፈላጊ በሆነበት ትክክለኛው ጊዜ ወቅታዊነት ያለውን እውነት ገልጦ ይሰጣል የሚል አንደምታ አለው፡፡ ጌታ በዘመናት እየጨመረ የሚሄድ ብርሃን ለሕዝቡ መስጠቱ የአደባባይ ምስጢር ነው፡፡ የመጀመሪያው የወንጌል ኪዳን የተሰጠው በዘፍ. 3፡15 ሲሆን ይኸውም በሴቲቱ ዘር አማካይነት ለወደቁት ጥንዶች ተስፋ በተሰጣቸው ጊዜ ነበር፡፡ "በእውነት ታላቅና ብርቱ ሕዝብ ይሆናል፤ የምድር ሕዝቦችም ሁሉ በእርሱ ይባረካሉ" (ዘፍ. 18፡18) በሚል ለአብርሃም የተሰጠው ኪዳን የወንጌልን ተስፋ በሙላት የሚገልጽ ራእይ ነው፡፡ "የሰው ልጅ ሊያገለግልና ሕይወቱን ለብዙዎች ቤዛ አድርጎ ሊሰጥ መጣ እንጂ ሊገለገል አልመጣም" (ማር. 10፡45) በሚል የተገለጠው የየሱስ የመጀመሪያ ምጽአት ከመቼውም የላቀ የወንጌል እውነት

መገለጥ ለመሆኑ አንድና ሁለት የለውም፡፡

የሦስቱ መላእክት መልእክት የሆነውን ራእ. 14፡6-12 ከክርስቶስ መገለጥ አስቀድሞ ባሉት የመጨረሻዎቹ ቀናት ለሚኖሩ ሕዝቦች የተሰጠ ወቅታዊ እውነትነት መሆኑን እናምናለን፡፡ እንዲሁም እንደ ክርስቲያን የአጠቃላዩ ተስፋ ፍጻሜ አድርገን እንቀበላለን፡፡

በዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችን በመጨረሻው የመከራ ዘመኖች ታማኝ እንደሆኑ ለመጽናት ምኞታቸው ለሆኑ ወገኖች ወሳኝ እውነት በያዘው በተለይ በመጀመሪያው መልአክ መልእክት ላይ ልዩ ትኩረት እናደርጋለን፡፡

## እሑድ ግንቦት 12

## ዓለማቀፋዊው የወንጌል ይዘት

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ማቴ. 14፡6፣ 24፡14፣ 28፡19፡፡ በመልእክቶቹ የምናገኘው ተመሳሳይ ጭብጥ ምንድን ነው? እንደ ቤተ ክርስቲያን ለቆምንለት ዓላማ ወንጌልን ወጥቶ መስበክና መመስከር ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ማስተዋል እንድንችል እነዚህ ጥቅሶች በአንድነት የሚረዱን እንዴ ነው?**

______________________________________________________

______________________________________________________

______________________________________________________

ለምሳሌ የመጀመሪያው መልአክ መልእክት የሆነውን ታላቁን ተልዕኮ (ማቴ. 28፡19) ለዚህ ዘመን እንደ ተሰጠ መልእክት በመቁጠር ከመጨረሻዎቹ ጊዜያቶች "ወቅታዊ እውነት" ዐውድ ልንመለከተው እንችላለን፡፡

እዚህ ላይ ሦስቱም ጥቅሶች "ለሕዝብ፣ ለነገድ፣ ለቋንቋና ለወገን" (ውጪያዊ) የወንጌል ተደራሽነት አጽንኦት እንደሚሰጡ ልብ ይሏል፡፡ በሌላ አባባል እያንዳንዱ ሰው ይህን መልእክት መስማት ያለበት በመሆኑ ዓለማቀፋዊ አንደምታ አለው፡፡

**ጥቅሱን ያንብቡ፡ ገላ. 3፡22፡፡ መላው ዓለም ለምን ወንጌልን መስማት እንዳለበት ማስተዋል እንድችል ጥቅሱ የሚረዳን እንዴት ነው?**

---

---

የኃጢአት ዓለማቀፋዊ ይዘት የተልዕኮአችንንና የጥሪአችንን አለማቀፋዊነት ገልጦ ያሳያል፡፡ እያንዳንዱ "ሕዝብ፣ ነገድ፣ ቋንቋና ወገን" በመሳቱና አምላካዊውን ሕግ በመተላለፉ "የኃጢአት እስረኛ" ሆኖአል፡፡ የአዳም በኤደን መውደቅ እንደ ሰደድ እሳት ወደ መላው ሰብዓዊ ዘር በመተላለፉ በኃጢአት ቫይረስ ተጠቂ ያልሆነ ሕዝብ፣ ነገድ፣ ቋንቋ ወይም ወገን አይገኝም፡፡ ቅጽበታዊውን የኃጢአት ውጤት ሁላችንም እየተጋፈጥን ቢሆንም፤ ነገር ግን ዘላቂው መፍትሔ ባይኖር ኖሮ ከአይቀሬው ውጤት ይኸውም ከዘላለማዊው ሞት ጋር መጋፈጣችን የግድ በሆነ ነበር፡፡

በእርግጥ ትክክለኛው መፍትሔ ይኸውም፡ የየሱስ ህይወት፣ ሞት፣ ትንሳዔ እና የሰማያዊ መቅደስ አገልግሎት ብቸኛው የኃጢአት ችግር መፍትሔ ሆኖ ቀርቦልናል፡፡ እያንዳንዱ ሰው እግዚአብሔር በየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ያበረከተለትን ታላቅ ተስፋ ማወቅ ይኖርበታል፡፡ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስቶች ይህ እውነት ወዳልተሰማባቸው ወደ ሁሉም የዓለም ክፍሎች በመድረስ የየሱስን መልእክት ማካፈል ምኞታቸው የሆነው ለዚህ ነው፡፡

ለሌሎች የወንጌልን መልእክት ማሰራጨት ለአገልጋዩ ብርቱ መንፈሳዊ ጥቅም ያለው ለምንድን ነው? በሌላ አባባል የወንጌልን መልእክት ለሌሎች ተደራሽ ስናደርግ፤ በተመሳሳይ ራሳችንን ድንቅ በሆነ መንገድ ለዳግም ምጽአቱ እያዘጋጀን የሆነበት ምክንያት ምንድን ነው?

## ሰኞ ግንቦት 13

## ከየሱስ ጋር የተሰቀለው ወንበዴ እና “የዘላለም ወንጌል”

በራእ. 14፡6 የቀረበው “የዘላለም ወንጌል” ለዓለም ሊሰበክ የተገባ መልእክት ነው፡፡ ይህ በራሱ አንዳችም ተስፋ ማበርከት ላልቻለውና ላልነበረው ዓለም የተሰጠ የተስፋ መልእክት ነው፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ሉቃ. 23፡32-43፡፡ ታሪኩ በኃጢአት ለወደቀው ዘር የቀረበውን “የዘላለም ወንጌል” ተስፋ የሚገልጸው እንዴት ነው?**

---

---

ከየሱስ አጠገብ ተሰቅሎ ስለነበረው ወንበዴ ኤለን ኋይት ስትጽፍ “ይህ ሰው ልቡ የደነደነ ወንጀለኛ አልነበረም፡፡ የጎሊና ወቀሳውን አፍኖ ለመያዝ ሲል ቀስ በቀስ ወደ ኃጢአት ማጥ በመግባቱ በወንጀለኝነት ተያዘ፡፡ ወንጀለኛነቱ በምርመራ ስለተረጋገጠበት በሥቅላት እንዲሞት ተፈረደበት”—Ellen G. White, *The Desire of Ages*, p. 749.

ከዚያ ምን ተከሰተ? በመስቀል ላይ እያለ ስለ የሱስ ማንነት በውልብታ መመልከት በመቻሉ “‘ኢየሱስ ሆይ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ’ አለው” (ሉቃ. 23፡42)፡፡

የሱስ የሰጠው ምላሽ ምን ነበር? *ወዳጄ፡ ብረዳህ ደስ ባለኝ ነበር፡፡ ነገር ግን የጎሊና ወቀሳህን አፍነህ ወደ ኃጢአት ማጥ መግባት አልነበረብህም*--ነበር ያለው? ወይስ “ጽድቃችሁ ከከፈሪሳውያንና ከኦሪት ሕግ መምህራን ጽድቅ ልቆ ካልተገኘ መንግሥተ ሰማይ መግባት አትችሉም” (ማቴ. 5፡20) በማለት ከቀደሙት መልእክቶቹ አንዱን አካፈለው? ከዚህ ውጪ የሱስ የወንበዴውን ያለፉ ስህተቶች ሊያስታውሰውስ ሞክሮ ነበር?

የሱስ በዚህ ፋንታ እንከን ወደ ነበረበት፣ አንዳችም የጽድቅ ሥራ መሥራት

ወደማይችለውና ቀደም ሲል የስድብ ናዳ ያወርድበት ወደ ነበረው (ማቴ. 27፡44) ወደዚህ ወንጀለኛ መልከት አደረገ፡፡ ከዚያም እንደ አዲስ ሰው እየተመለከተው “እውነት እልሃለሁ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ” አለው (ሉቃ. 23፡43)፡፡ ይህ ማለት፡ ኃጢአትህ፣ ወንጀልህ፣ የነበረብህ እንከን ይቅር እንደ ተባለ አሁን እየነገርኩህ፣ እያረጋገጥኩልህ ነው፡፡

ይህ የመጀመሪያው መልአክ መልእክት መሰረት የሆነው “የዘላለም ወንጌል” ነው፡፡ ያለዚህ እውነት ስለ ሕግ፣ ስለ ሰንበት ወይም ስለ ሞቱ ሰዎች ሁኔታ--ምንም ነገር ማስተማር አንችልም፡፡ የሁሉም የልብ ትርታ ከሆነው “የዘላለም ወንጌል” ውጪ የእነዚህ አስተምህሮዎች መልካምነት ምኑ ላይ ነው?

**ከዚህ ታሪክ ለራስዎ ሊወስዱ የሚችሉት ተስፋ ምንድን ነው?**

## ማክሰኞ ግንቦት 14

## እግዚአብሔርን ፍሩ ክብርም ስጡት

“የዘላለም ወንጌል” ለመላው ዓለም ስለ መታወጁ ከቀረበው መልእክት በኋላ የመጀመሪያው መልአክ መልእክት በዚሁ መልእክት ላይ ይበልጥ እየተስፋፋ ይሄዳል፡፡ የዘላለምን ወንጌል ለዓለም በምናስተጋባበት ወቅት የዚህ ወንጌል አካል የሆኑ ወቅታዊ እውነቶችን ማካተታችን የግድ ይሆናል፡፡ በሌላ አነጋገር የራእ. 14፡7 መልእክት በመጨረሻዎቹ ጊዜያቶች ወቅታዊ እውነት ውስጥ ይካተታል፡፡

**ጥቅሱን ያንብቡ፡ ራእ. 14፡7፡፡ እግዚአብሔርን መፍራትና ለእርሱ ክብር መስጠት ምን ማለት ነው? ያን የምናደርገው እንዴት ነው? እነዚህ ጽንሰ ሃሳቦች ከወንጌል ጋር ገጣሚ የሚሆኑት እንዴት ነው?**

እግዚአብሔርን መፍራት እና ለእርሱ ክብር መስጠት የማይገናኙ ጽንሰ ሃሳቦች አይደሉም፡፡ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊው እሳቤ አኳያ እግዚአብሔርን በእውነት የምንፈራ ከሆነ ክብር እንሰጠዋለን፡፡

ስለዚህ አንደኛው በቀጥታ ወደ ሌላኛው ማምራቱ የግድ ይሆናል፡፡

**የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡፡ ጥቅሶቹ "እግዚአብሔርን ፍሩ" የሚለውን ሃረግ ፍቺ ማስተዋል እንድንችል እንዴት ይረዱናል? ለእርሱ ክብር ከመስጠት ጋር የሚዛመደውስ እንዴት ነው? ዘፍ. 22:12፣ ዘፀ. 20:20፣ ኢዮ. 1:9፣ መክ. 12:13፣ ማቴ. 5:16፡፡**

---

---

ከላይ በቀረቡት ጥቅሶች እግዚአብሔርን መፍራት የሚለው ጽንሰ ሃሳብ እርሱን ከመታዘዝ ጋር ተያያዥነት አለው፡፡ ትክክል የሆነውን ነገር ስናደርግ ለእርሱ ክብር እናመጣለን፡፡ ምንም እንኳ እግዚአብሔርን መፍራት ከአድናቆት ወይም ከአክብሮት ጋር ተያያዥነት እንዳለው በተደጋጋሚ ቢነገርም፤ ከዚያም በጥልቀት መሄድ ግን ይኖርበታል፡፡ እግዚአብሔርን እንድንፈራ ተነግሮናል፡፡ እኛ እንደ አምላካዊው ፈቃድ ከመራመድ በመሰናከል ኃጢአት በመሥራታችን ሞት የሚገባቸው ፍጡራን ለመሆን በቃን፡፡ በየጊዜው በሚስተዋሉ አስገራሚ የክፉው ድርጊቶች እና ከጻድቁና ፍትሐዊው አምላክ እጅ ምን እንደሚገባቸው በማሰብ ያልተደመመ ማን አለ? ይህ እንግዲህ እግዚአብሔርን መፍራት ነው፡፡ ደግሞም በመጀመሪያ ይቅርታ ለመቀበል ወደ መስቀሉ እንድናመራ የሚያደርገን ይኸው ፍርሃት ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ከበደል የሚያነጻንን አምላካዊ ኃይል ፍለጋ ነው፡፡ መስቀሉ ባይኖር ለዘላለም ጠፍተን በቀረን ነበር (ማቴ. 10፡28)፡፡

እግዚአብሔርን ከመፍራት ጋር በተያያዘ የግል ተሞክሮዎ ምን ይመስላል? ከመንፈሳዊ ህይወታችንና ከእምነታችን ጋር በተያያዘ ትጋት እንዲኖረንና እግዚአብሔር የሚጠይቀንን እንድናደርግ በማስቻሉ ረገድ ሚዛናዊ የሆነ የዚህ ፍርሃት መጠን መልካም የሚሆነው እንዴት ነው?

## ረቡዕ ግንቦት 15

## የፍርዱ ሰዓት ደርሶአል

በመጀመሪያው መልአክ መልእክት እግዚአብሔርን የመፍራትና ለእርሱ ክብር የመስጠት ጽንሰ ሃሳብ ከፍርዱ ጋር ተያያዥነት አለው (ራእ. 14፡7)፡፡ እግዚአብሔር የፍትሕ እና የፍርድ አምላክ መሆኑ ከመጽሐፍ ቅዱስ በእጅጉ ግልጽ አስተምህሮዎች መሃል አንዱ ነው፡፡ ፍትሕና ፍርድ እጅግ አድርጎ ባጠረው በዚህ ዓለም--አንድ ቀን ይመጣል፡፡

ሰዎች እግዚአብሔርን መፍራት ቢኖርባቸው ብዙም አያስደንቅም፡፡

"የዘላለም ወንጌል" የፍርድን ተጨባጭነት በመልእክቱ ያካተተበት ምክንያት ይኸው ነው፡፡ ለመሆኑ በእነዚህ ሁለት መሰረታዊ ነገሮች መካከል ያለው ግንኙነት ምንድን ነው? የወንጌል "መልካም የምስራች" የሚል ፍቺ ካለው፤ እኛ ሁላችን ኃጢአተኞች እና አምላካዊውን ህግ የጣስን ሕዝቦች ብንሆንም፤ ነገር ግን በመስቀል ላይ እንደ ተሰቀለው ወንበዴ ያ የፍርድ ቀን ከተፍ ሲል፤ እንደ ኃጢአተኝነታችንና እንደ መተላለፋችን ይገባን የነበረውን ቅጣት አንቀበልም፡፡ **የሚከተሉትን ጥቅሶች ካነበቡ በኋላ--በራሴ መልካም ሥራዎች ምን ያህል መቆም እችላለሁ? ብለው ራስዎን ይጠይቁ፡ ማቴ. 12:36፣ መክ. 12:14፣ ሮሜ. 2:6፣ 1ቆሮ. 4:5፡፡**

---

---

የፀጉራችንን ቁጥር የሚያውቀው አምላክ እነሆ ዓለምን ሊዳኝ ተቃርቦአል፡፡ እንግዲህ "የዘላለም ወንጌል" በትክክል መልካም የምስራች የሆነው ለዚህ ነው፡፡ አምላካዊው ፍርድ ቢመጣም ነገር ግን በታጠቡት፣ በተቀደሱትና በጸደቁት ታማኝ

የየሱስ ተከታዮች ላይ "ኩነኔ" የለም (1ቆሮ. 6፡11)፡፡ ምክንያቱም የሱስ ክርስቶስ ጽድቃቸው--ጽድቁም ከፍርድ ነፃ የሚያደርጋቸው ነው፡፡

"ሰብዓዊው ዘር በእነዚህ ክሶች ፊት ብቻውን መቆም አይችልም፡፡ በኃጢአት የተነከሩት ያደፉ ልብሶች በደለኝነቱን ይመሰክራሉ፡፡ ነገር ግን በንስሐ እና በእምነት ራሳቸውን ለእርሱ በአደራ ለሰጡ--ስለ እኛ የሚቆመው ጠበቃችን ተፈላጊውን ውጤት የሚያስገኘውን የክስ መልስ ያቀርባል፡፡ በኃያሉ የቀራኒዮ እሴቶች ተሟግቶ ከሳሻቸውን ድል ይነሳል፡፡ የእግዚአብሔርን ሕግ እስከ መስቀል ሞት ድረስ በፍጹም ንጽህና መታዘዙ በሰማይና በምድር ኃይል ሁሉ የእርሱ እንዲሆን አስቻለው፡፡ ስለዚህ ለጥፋተኛው ሰብዓዊ ዘር አባቱን ምኅረትና እርቅ ለመጠየቅ ባለ መብት ሆነ፡፡"—*Ellen G. White, Testimonies for the Church, vol. 5, p. 471.*

**ፍጹም ይቅርታ የሚያስፈልገን መሆኑ ስለ ፍርድ መኖር ምን ያስተምረናል? እግዚአብሔር በየሱስ አማካይነት የሰጠንን ጸጋና ምህረት ምንነት በደል ያደረሱብንን ይቅር በማለት መማር የሚችሉት እንዴት ነው?**

## ሐሙስ ግንቦት 16

## ሰማይንና ምድርን የፈጠረውን ማምለክ

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 14፡6-7፡፡ በመጀመሪያው መልአክ አጠቃላይ መልእክት ውስጥ ለየት ያሉት አላባዎች ምንድን ናቸው? እርስ በርስ ያላቸው ዝምድናስ ምን ይመስላል?

________________________________________

________________________________________

ለዓለም ምስክር እንድንሆንና እግዚአብሔርን እንድንፈራ፣ ለእርሱም ክብር እንድንሰጥ የቀረበልን ጥሪ መነሾ እግዚአብሔርን እንደ ፈጣሪ ማምለክ ነው፡፡

ይህ በእርግጥ ብዙም አያስገርምም፡፡ እነዚህ የወቅታዊው እውነት ሌላኛው ገጽታ የሆኑት--የዘላለም ወንጌል፣ ምስክር እንድንሆን የቀረበልን ጥሪ እና ፍርድ-- መሰረታቸው እግዚአብሔርን እንደ ፈጣሪ ከማመንና ከመቀበል ውጪ ሌላ ምን ሊሆን ይችላል? የእነዚህና የሌሎቹ ሁሉ እውነቶች መነሾ ሁሉንም የፈጠረው ጌታ መሰረታዊ እውነት ነው፡፡ ከማንኛውም ምድራዊ ፍጡር በተለየ ሰው ማለት እና በሕይወት መመላለስ ምን እንደሆነ ለማስተዋል ብሎም በእግዚአብሔር አምሳል ለመሠራት ጌታን እንደ ፈጣሪ በማምለክ ወደ ቀደመው መሰረት እንመለሳለን፡፡ እርሱን እንደ ፈጣሪ በማምለክ የህልውናችን መሰረት፣ መተማመኛችንና የወደፊት ተስፋችን መሆኑን እናሳያለን፡፡ ሰባተኛውን ቀን ሰንበት መጠበቅ አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት ይኸው ነው፡፡ እግዚአብሔር ብቻ ፈጣሪያችን መሆኑንና እርሱን ብቻ ማምለካችንን በተለይ የምናረጋግጥበት መንገድ ነው፡፡ እዚህ ላይ ከወንጌልና ከፍርድ ጎን ለጎን ጌታን እንደ ፈጣሪ እንድናመልክ የቀረበልን ጥሪ በስፋት ይታወቃል፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 14፡8-11፡፡ ጌታን እንደ ፈጣሪ በማስተዋል አምልኮ የማቅረብን አስፈላጊነት እንድናስተውል ጥቅሶቹ ምን ይነግሩናል**

---

---

የመጨረሻዎቹ ጊዜያት ክስተቶች በዓለም ዙሪያ መገለጥ ሲጀምሩ፤ በፈጣሪ ፋንታ ለአውሬውና ለምስሉ እንድንሰግድ የሚደረገው ግፊት እየበረታ ይመጣል፡፡ ለአውሬውና ለምስሉ ስግደት ለሚያቀርቡ የተሰጠውን አስፈሪ ማስጠንቀቂያ በሚገባ ማጤን ከቻልን፤ እግዚአብሔር እንደ ፈጣሪነቱ ብቸኛ ሰብዓዊ አምልኮ እንደሚገባው የተሰጠውን አጽንኦት በተሻለ ማስተዋል እንችላለን፡፡ ብርቱ ቀውስ በሚከሰትባቸው በእነዚያ የመጨረሻዎቹ ቀናት ይህ እውነት ከመቼውም በላይ አንገብጋቢ ሆኖ ይወጣል፡፡

**በእግዚአብሔር አምላክ ስለ ተፈጠረው ለማመን የሚያስቸግር አስገራሚ ዓለም ጊዜ ወስዳችሁ ተወያዩ፡፡ የፍጥረት ሥራ ይህን ሁሉ ስለ ፈጠረው አምልክ ምን ሊያስተምር ይችላል? አምልኮ በብቸኝነት የሚገባው እርሱ ብቻ የሆነው ለምንድን ነው?**

አርብ ግንቦት 17

***ተጨማሪ ሃሳብ፡*** *የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች--በራእ. 14፡7 "ሰማይንና ምድርን፣ ባሕርንና የውሃ ምንጮችን ለፈጠረው ስገዱ" የሚለውን መልእክት "እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን፤ ባሕርንና በውስጡም ያሉትን ሁሉ በስድስት ቀን ፈጥሮ በሰባተኛው ቀን አርፎአልና" (ዘፀ. 20፡11) ከሚለው አራተኛው ትእዛዝ ጋር ያለውን ትስስር ቀደም ባሉት ጊዜያቶች መመልከት ችለው ነበር፡፡*

*ምንም እንኳ በሁለቱ ጥቅሶች ጥቅም ላይ የዋለው ቋንቋ በቅርብ የተሳሰረ ቢሆንም፤ ነገር ግን ጌታ "የውሃ ምንጮችን" መፍጠሩን በሚያመላክተው የራእይ ሃረግ ላይ ለውጥ አለ፡፡*

*ደራሲ ጆን ባልድዊን እንዲህ ሲሉ ይሞግታሉ፡ "'የውሃ ምንጮች' ከሚለው ሃረግ በስተ ጀርባ ሆነ ብሎ የተደረገ መለኮታዊ ፈቃድ ከሌለ በቀር ከዘፀ. 20፡11 ጋር ትይዩ ሆነው በቅደም ተከተል የቀረቡት ነጥቦች ላይ መልእክተኛው ለውጥ እንዲያደርግ የሱስ ለምን ፈቀደ? መልአኩ 'የውሃ ምንጮች' ብሎ በመጥቀስ ፋንታ--ዛፎች፣ ወፎች፣ ዓሦች ወይም ተራሮች በማለት ሌሎች የፍጥረት ሥራዎችን ያልተጠቀመው ለምንድን ነው?*

*"በዓይነቱ ልዩ የሆነው አምላካዊ ፍርድ መድረሱን የሚያስታውቀውና 'የውሃ ምንጮች' በሚል ሃረግ ከመለኮታዊው መልእክት ዐውድ የቀረበው ማስረጃ፤ የአንባቢውን ትኩረት ወደ ቀደመው ዘመን የመለኮት ፍርድ መድረስ ለማመልከት የተደረገ ሊሆን ይችላል. . . እግዚአብሔር 'የውሃ ምንጮች' የሚለውን ሃረግ ጥቅም ላይ ያዋለው ምናልባት የጥፋት ውሃን ጉዳይ በተዘዋዋሪ*

በመንካት የፍርድ አምላክ ለመሆኑ አጽንኦት ለመስጠትና ለዘላለም ታማኝና ቸር አምላክነቱን ለማሳየት ይሆናል፡፡ ጉዳዩ እንዲህ ከሆነና ‘የውሃ ምንጮች’ በሚል የቀረበው ሃረግ ዐውደ ሃሳብ ከጥፋት ውሃ ጋር ተያያዥነት ካለው፤ አንባቢው የጊዜውን መጨረሻ መድረስ አስተውሎ ጉዳዩን በዋዛ እንዳይመለከትና በራእ. 14 የመጀመሪያው መልአክ መልእክት ለተሰጠው መለኮታዊ ፍርድ አጽንኦት እንዲሰጥ ሊያደፋፍረው ይችላል፡፡—John Baldwin, ed., *Creation, Catastrophe, and Calvary: Why a Global Flood Is Vital to the Doctrine of Atonement* (Hagerstown, Md.: Review and Herald® Publishing Association, 2000), p. 27.

***የመወያያ ጥያቄዎች፡***

1.“እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን” (ኢሳ. 53፡6)፡፡ “እኛ ሁላችን”-- የሚሉት ቃላት በዕብራውያን ቋንቋ *ኩላኑ* በሚል ቃል ይታወቃሉ፡፡ በዚያው ጥቅስ ኢሳያስ “የሁላችንንም በደል” በእርሱ ላይ ጫነው ሲል ይነግረናል፡፡ “የሁላችንንም” የሚለው ቃል ፍቺ አሁንም *ኩላኑ* የተሰኘው ቃል ነው፡፡ የኃጢአት ችግር የቱንም ያህል ቢገዝፍ መፍትሔው ከበቂ በላይ መሆኑን ይህ እንዴት ያሳየናል?

2.በመስቀል ላይ ስለ ነበረው ወንበዴ ሌሎች ምን ዓይነት ትምህርቶች ማግኘት እንችላለን? ምናልባት ይህ ወንበዴ በምድራዊ ገዢዎች ይቅር ተብሎ ከመስቀል ቢወርድና እንዲኖር ቢፈቀድለት ምን ዓይነት የተለየ ህይወት ይኖር ነበር ብለው ያስባሉ? ምላሽዎ ክርስቶስ ሕይወታችንን ለመቀየር የሚያስችል ኃይል እንዳለው ምን ይነግረናል?

# ዘጠነኛ ትምህርት ከግንቦት 18- 24

## የመጨረሻው ጊዜ ማታለያዎች

### ሰንበት ከሰዓት

*ለዚህ ሳምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ራእ. 2:13፣ 24፣ 2ቆሮ. 11:13–15፣ መዝ. 146:4፣ ዘፍ. 1–2:3፣ ራእ. 13:1–17፡፡*

**የሳምንቱ ጥናት መሪ ጥቅስ፡-**

**“ታላቁ ዘንዶ፣ የጥንቱ እባብ ተጣለ፤ እርሱም ዲያብሎስ ወይም ሰይጣን ተብሎ የሚጠራው፣ ዓለምን ሁሉ የሚያስተው ነው፤ እርሱ ወደ ምድር ተጣለ፤ መላእክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ” (ራእ. 12፡9)፡፡**

ሰይጣን ከሰማይ ከመባረሩ አስቀድሞ መላእክትን ለማሳት ሠርቶአል፡፡ “በእግዚአብሔር ፊት የነበረውን ስፍራ ለቅቆ እንደ ወጣ ሉሲፈር በመላእክቱ መካከል ያለመርካትና የቅሬታ መንፈስ የመዝራት ጉዞውን ጀመረ፡፡ ባለ ስውር ደባው ሰይጣን ለጊዜው እውነተኛ ዓላማውን ደብቆ፣ ለእግዚአብሔር የሚያቀርበውን የአምልኮ ገጽ ሳይለውጥ፤ ሰማያዊውን አካላት በአንድነት የሚገዛው አምላካዊ ሕግ በፍጡራኑ ላይ አላስፈላጊ እቀባ ያደርጋል በሚል አለመርካት እንዲፈጠር ማነሳሳት ጀመረ፡፡”—Ellen G. White, *The Great Controversy*, p. 495.

በኤድን የአትክልት ስፍራ እውነተኛ ማንነቱን ሰውሮና በእባብ ተመስሎ ሔዋንን አታለለ፡፡ ሰይጣን ይህን ማታለሉን ከጥንት አንስቶ ዛሬ ድረስ-- እንደውም ጻድቃን ሺ ዓመት ከነገሡ በኋላም እንኳ (ራእ. 20፡8) እስከ መጥፊያው ድረስ ይገፋበታል፡፡

እንዳለመታደል ሆኖ እርሱ ከእኛ በላይ ብልህ፣ የላቀ አቅም ያለውና ወደር የማይገኝለት አታላይ ነው፡፡ ስለዚህ ከእርሱ ማታለያ ለመጠበቅ ያለን ብቸኛው አማራጭ የሱስንና አምላካዊውን ቃል አጥብቆ መያዝ ነው፡፡ "አምላካችሁን እግዚአብሔርን የተከተላችሁት እናንተ ሁላችሁ ግን ይኸው እስከ ዛሬ በሕይወት አላችሁ" (ዘዳ. 4፥4)፡፡ ይህ ተቀባይነት ያለው መርኅ እነሆ ዛሬም በእርግጠኝነት እውነት እንደሆነ አለ፡፡

በዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችን እጅግ ውጤታማ የሆኑትን አንዳንድ የሰይጣን ማታለያዎችንና ከእነርሱ እንዴት መጠበቅ እንደምንችል እንመለከታለን፡፡

## እሑድ ግንቦት 19

## ታላቁ ማታለያ

የዚህ ሩብ ዓመት የመጀመሪያው ትምህርት ከምድራችን ባሻገር ወዳለው "ዩኒቨርስ አቀፉ ተቃርኖ" በማምራት አንዳንድ ጠቃሚ ጽንሰ ሃሳቦችን መዳሰሱ ይታወሳል፡፡

የሚያሳዝነው ክርስቲያኖችን ጨምሮ ብዙዎች በዚህ ታላቅ ተቃርኖ ላይ እምነት የላቸውም፡፡ ለዚህ መንስዔው ደግሞ በሰይጣን ነባራዊ ሁኔታ አለማመናቸው ነው፡፡ ስለ ሰይጣን ወይም ዲያብሎስ የሚናገሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ለእነርሱ በምድር ላይ የነበረውን ክፋትና ሥቃይ ሊያብራራ የሚሞክር ቅድመ ሳይንስ ባህልና ወግ ነው፡፡ በሰብዓዊው ፍጡር ላይ ክፉና በተንኮል የተሞላ መሰሪ እቅድ ያለውን ነገር ብዙዎች የሚመለከቱት ከደራሲና ጸሐፊ ተውኔት ዳርት ቫንደር "ስታር ዎርስ" የሣይንስ ልቦለድ ጽንሰ ሃሳብ በተመሳሳይ ነው፡፡

**የሚከተሉትን ከራእይ መጽሐፍ የተወሰዱ ጥቅሶች ያንብቡ፡፡ ስለ ሰይጣን በተጨባጭ መኖርና በተለይ ደግሞ በመጨረሻዎቹ ቀናት ስለሚኖረው ሚና ምን ይነግሩናል? ራእ. 2:13፣ 24፣ 12:3፣ 7–9፣ 12፣ 17፣ 13:2፣ 20:2፣ 7፣ 10፡፡**

---

---

በመጨረሻዎቹ ቀናት ሰይጣን በአያሌ የምድር ሕዝቦች ላይ መጠነ ሰፊ ኃይል እንደሚኖረው የራእይ መጽሐፍ ይነግረናል፡፡ ሰይጣን እነርሱን ከደህንነት መንገድ የማራቅ ሥራ ብቻ አይሠራም ይልቁንም ለየሱስ ታማኝ ሆነው የጸኑትንም ይዋጋል፡፡

ምናልባት ከሰይጣን የማታለያ "ዕቅድ" (2ቆሮ. 2፡11) የላቀው ሰዎች ሰይጣን የለም ብለው እንዲያምኑ አእምሮአቸውን ማሳመን ነው፡፡ ለነገሩ መኖሩን ከማያምኑት ግዙፍ ባላጋራ መጠጊያ ፍለጋ ማን ሊሄድ ይችላል? ራሳቸውን ክርስቲያን ብለው እየጠሩ ላፈጠጠውና ላገጠጠው የሰይጣን መኖር ጽንሰ ሃሳብ ብርቱ ትኩረት አለመስጠታቸው በእጅጉ የሚገርም ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች እንዲህ ያለውን አቋም የያዙበት ምክንያት አንድም አምላካዊውን ቃል ቸል በማለት አልያም በመጽሐፍ ቅዱስ የቀረቡትን የዚህ ዓለም ሥራዎቹንና ድርጊቶቹን አጣምመው በመተርጎም ነው--በተለይ ወደ መጨረሻው ጊዜ እየተቃረብን ስንመጣ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሰይጣን መኖር አያሌ ማስረጃዎች እያቀረበ ነገር ግን ብዙዎች ገሀዱን እውነታ መቃወማቸው፤ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን በትክክል ማስተዋላችን ምን ያህል ቁልፍ እንደሆነ እንድናስታውስ ይረዳናል፡፡ **የራእይ መጽሐፍ በተለይ በመጨረሻዎቹ ቀናት ገቢራዊ ስለሚሆኑት የሰይጣን ብልህ ማሳቻዎች ቢነግረንም፤ በራእ. 12፡11 ምን ዓይነት ታላቅ ተስፋ እናገኛለን? ከዲያብሎስ መጠበቂያ የኃይል ምንጫችን ምንድን ነው?**

## ሰኞ ግንቦት 20

## ሁለቱ ታላላቅ ስህተቶች

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥቅሶች ያንብቡ፡፡ ሰይጣን ስላለው የማሳቻ ኃይል ምን ይነግሩናል?

2ቆሮ. 11:13–15 ____________________________________________

2ቆሮ. 2:9, 10______________________________________________

ራእ. 12:9_________________________________________________

ራእ. 20:10________________________________________________

የሱስ ስለ መጨረሻው ጊዜ ማታለያዎች ተከታዮቹን ማስጠንቀቁን ቀደም ባለው ትምህርታችን ተመልክተናል፡፡ በተለይ ከሰጣቸው ማስጠንቀቂያዎች መሃል የሐሰተኛ ክርስቶሶች እና "'ብዙዎችን የሚያስቱ" ሐሰተኛ ነቢያት መነሳት ይጠቀሳሉ (ማቴ. 24፡5)፡፡

ሆኖም በመጨረሻው ጊዜ እንድንጠነቀቃቸው የተነገሩን አሳቾች ሐሰተኛ ክርስቶሶች እና ሐሰተኛ ነቢያት ብቻ አይደሉም፡፡ በዚህ በታላቁ ውዝግብ ጠላታችን በተቻለው ለማሳት የሚጠቀምባቸው አያሌ ዘዴና ብልሀቶች አሉት፡፡ እኛ እንደ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስን በማወቅና የሚያስተምረውን በመታዘዝ በእነዚህ የማሳቻ ዘዴዎች ላይ ግንዛቤ ሊኖረን ይገባል፡፡

ኤለን ኋይት ስለ ሁለቱ ታላላቅ የማሳቻ ዘዴዎች እንዲህ ትላለች፡ "ሰይጣን በሁለቱ የተሳሳቱ አስተምህሮዎች ማለትም--በ ነፍስ አትሞትም እና በእሁድ ቅድስና ሕዝቡን ያስታል፡፡ የመጀመሪያውና ነፍስ አትሞትም የሚለው አስተምህሮ (ስፐሪቹዋሊዝም) ከሙታን መንፈስ ጋር ስለ መገናኘት ለሚያወሳው አፈንጋጭ ስህተት መሰረት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከሮም ጳጳሳዊ ሥርዓት ጋር ውል አለው፡፡ የዩኤስ አሜሪካ ፕሮቴስታንቶች ሸለቆውን አልፈው የስፐሪቹዋሊዝምን ፍልስፍና አራማጆች ለመጨበጥ ቀዳሚዎች ይሆናሉ፡፡

ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ በተቃራኒ እንጦሮጦስ ወርደው ከሮም ኃይል ጋር እጅ ለእጅ ይያያዛሉ፡፡ ታዲያ ይህ የሦስትዮሽ ኅብረት ተጽእኖ ይህች አገር (ዮኤስ አሜሪካ) የአምልኮ ነፃነትን ረግጣ የሮምን ዱካ ተከትላ እንድትሄድ ያደርጋታል፡፡”—*The Great Controversy*, p. 588.

ኤለን ኋይት ይህን መልእክት ያሰፈረችው ከአያሌ ዓመታት በፊት ቢሆንም “ሁለቱ ታላላቅ ስህተቶች” ዛሬ በክርስትናው ዓለም እንዲህ ተስፋፍተው መመልከታችን የሚደንቅ ነው፡፡

**የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶች ዕውቀት እና እነዚህን እውነቶች ለመታዘዝ የሚኖር ፈቃደኝነት ለዲያብሎስ ማታለያ ዓይነተኛ መሣሪያ የሆነው ለምንድን ነው--በተለይ በመጨረሻዎቹ ቀናት?**

## ማክሰኞ ግንቦት 21

## የነፍስ ሕያውነት

**ከዚህ በታች የቀረቡት ጥቅሶች ስለ “ሙታን ሁኔታ” ምን ይነግሩናል? ጥቅሶቹ ከላይ ከተመለከትናቸው ከሁለቱ ታላላቅ ስህተቶች ለአንደኛው ምን ዓይነት ብርቱ ከለላ ይሰጡናል? መክ.** 9:5-6፣ 10፣ መዝ. 115:17፣ 146:4፣ 1ቆሮ. 15:16–18፣ ዳን. 12:2፡፡

---

---

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ባሉ አሥርተ ዓመታት--ልባቸው መምታት ካቆመና ትንፋሻቸው ከተቋረጠ በኋላ መልሰው በማንሰራራት ወደ ሕሊናቸው ተመልሰዋል--በሚል ስለ “ሞቱ” ሰዎች ሁኔታ የተዘገቡ ብዙ ዕንግዳ ታሪኮች ይሰማሉ፡፡ “ሞቱ” ከተባሉ በኋላ በዚህ ተሞክሮ አለፉ የሚባሉ ብዙዎች አስገራሚ የሚባሉ ታሪኮችን ሲናገሩ ይደመጣሉ፡፡ አንዳንዶች እንዴት በአየር

ላይ ተንሳፈው ቁልቁል የገዛ አካላቸውን እንደተመለከቱ ሲናገሩ፤ ሌሎች ደግሞ ከበድኑ አካላቸው ወጥተው እንደተንሳፈፉ--በእውነት፣ በደግነት፣ በፍቅር እና በአስደናቂ ብርሃን ውስጥ ያለ ማንነት ሲገናኛቸው መመልከታቸውን ተናግረዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሞቱ ዘመዶቻቸውን እንደ ተገናኙ የተናገሩም ብዙዎች ናቸው፡፡

ይህ ክስተት እጅግ የተለመደ ከመሆኑ የተነሳ--*ለሞት የቀረቡ ተሞክሮዎች* (Near Death Experiences (NDEs) የሚል ሳይንሳዊ ስያሜ እስከ ማግኘት ደርሶአል፡፡ ምንም እንኳ ጉዳዩ አወዛጋቢ እንደሆነ ቢቀጥልም ብዙ ክርስቲያኖች ሰው ሲሞት ነፍስ ግን ህልውናዋን እንደጠበቀችና የማገናዘብ ችሎታዋን እንደያዘች በሌላ ዓይነት ሁናቴ መኖሯን ትቀጥላለች ለሚለው አስተምህሮ እንደ ማስረጃ ይጠቀሙበታል፡፡

ነገር ግን *ለሞት የቀረቡ ተሞክሮዎች* በሚል ሳይንሳዊ ስያሜ ያገኘው ይህ ክስተት ሌላው "የሁለቱ ታላላቅ ስህተቶች" መገለጫ ነው፡፡ አንድ ሰው--ሰው ሲሞት ነፍሱ በሌላ ቅርጽ መኖር ትቀጥላለች በሚለው አፈንጋጭ አስተምህሮ እስካመነ ድረስ ግለሰቡ ከፍ ያለውን የምትሀትና ጥንቆላ ማሳቻዎች ለመቀበል በጣም የቀረበ ነው፡፡ እንደነዚህ ዓይነቶቹ ማሳቻዎች--የሱስ አያስፈልግህም የሚለውን ማታለያ በቀላሉ በግልጽ ወይም በስውር ማበረታታት ይችላሉ፡፡ የሚገርመው በተሞክሮው ውስጥ አለፉ የሚባሉ ብዙዎች ሲናገሩ እንደ ተደመጠው--የተገናኟቸው መንፈሳዊ አካላት ወይም የሞቱ ዘመዶቻቸው ስለ ሰጧቸው አጽናኝ ቃላት፣ ፍቅር፣ መልካምነት እንጂ መሰረታዊ የሆኑትን የመጽሐፍ ቅዱስ ምልከታዎች ማለትም--በክርስቶስ ስለሚገኝ ደኅንነት፣ ስለ ኃጢአት ወይም ስለ ፍርድ አንዳች ስለ መተንፈሳቸው የተዘገበ ነገር የለም፡፡ ከህይወት በኋላ አለፍንበት ባሉት ተሞክሮ የክርስትናን ህይወት አጣጣምን ብለው ከተናገሩ፤ በነካ እጃቸው እጅግ መሰረታዊውን የክርስትና አስተምህሮ ለዛ

ሊያጣጥሙም የተገባ ይሆናል ሲሉ አንዳንዶች ይሞግታሉ፡፡ ለሞት የቀረቡ በተባሉት ተሞክሮዎች ውስጥ ያለፉ ከተናሯቸው ነገሮች ውስጥ አብዛኞቹ ኒው ኤጅ በመባል ከሚታወቀው አፈንጋጭ ኃይማኖታዊ ቀኖና ጋር ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ አብዛኞቹ "ሞቱ" የተባሉት ክርስትና ራሱ እዚህ ግባ የሚሉት ዓይነት ሆኖ አናገኘውም፡፡

**ጎሊናችን የሆነ ያልተለመደ ነገር ሹክ ሊለን ቢችል እንኳ--እንደ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ቃል ጋር አጥብቀን መጣበቅ ያለብን ለምንድን ነው?**

## ረቡዕ ግንቦት 22

## ሰንበት እና የዝግመተ ለውጥ ንድፈ ሃሳብ

ሰይጣን ነፍስ አትሞትም በሚለው አስተምህሮው ብዙዎችን በማሳት ስኬት እንዳገኘ ሁሉ፤ በክርስትና ታሪክ መጽሐፍ ቅዱሳዊውን ሰንበት ወደ እሁድ በመለወጥ ምናልባትም የላቀውን ክንውን አግኝቶአል (ስድስተኛውንና ስምንተኛውን ትምህርት ይመልከቱ)፡፡

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ዲያብሎስ ሰባተኛው ቀን ሰንበት በሕዝቡ አእምሮ አነስተኛ ስፍራ እንዲኖረው የሚያደርግ ሌላ የማሳሳቻ ዘዴ ይዞ የመጣ ሲሆን ይኸውም፡ የዝግመተ ለውጥ ንድፈ ሃሳብ በመባል ይታወቃል፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ዘፍ. 1-2፡3፡፡ ገጾቹ ጌታ እንዴት ዓለማችንን እንደ ፈጠረና የፍጥረት ሥራ ምን ያህል ጊዜ እንደ ወሰደበት ምን ይነግሩናል?**

---

---

ጥቅሶቹ ስለ መጽሐፍ ቅዱሳዊው የፍጥረት ሥራ ሁለት ነጥቦችን በስፋት እንዲሁም በጥልቀት ይገልጣሉ፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ--ማንኛውም ነገር በዕቅድና

በስሌት መተግበሩን፡፡ በዘፈቀደ፣ በደመነፍስ ወይም እንደ ዕድል የሆነ አንዳች ነገር አልነበረም፡፡ የፍጥረት ሂደት ባጋጣሚ ወይም በዕድል መተግበሩን የሚጠቁም አንድም ፍንጭ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አልተተወም፡፡

በሁለተኛ ደረጃ--እያንዳንዱ ፍጥረት ከራሱ አምሳያ አኳያ መፈጠሩን በማያሻማ ሁኔታ ይገልጹልናል፡፡ ይህ ማለት እያንዳንዱ የፍጥረት ሥራ ከሌሎቹ ተለይቶና የራሱን ልዩ ባህሪ ይዞ ነው የተፈጠረው፡፡ ሕይወት ያለው ነገር ሁሉ የመጣው ከአንድ የጋራ ህዋስ ነው የሚለውን አስተምህሮ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አናገኘውም፡፡

ቃል በቃል ፍቺ የመስጠት መርኅን የማይከተሉት እንኳ ከዘፍጥረት መጽሐፍ አኳያ የቀረቡትን ሁለት ነጥቦች ይጋራሉ፡፡ በፍጥረት ሥራ በአጋጣሚ የተከሰተ ነገርም ሆነ የጋራ ተፈጥሮአዊ ዝርያ የሚባል አንዳች ነገር የለም፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚመጣው የዳርዊን ዝግመተ ለውጥ ንድፈ ሃሳብ ከያዛቸው የተለያዩ ቅርጾች አኳያ ሁለት ነገሮችን ያስተምራል፡--የውጤቶች ባህሪያት እኩል እና ተመሳሳይ መሆን የመቻል ዕድል እና ለሁሉም ዝርያዎች የጋራ ተፈጥሮአዊ ቅድመ አያት--የሚሉ፡፡

ብዙዎች የዘፍጥረት መጽሐፍን ከመሰረታዊ ባህሪያቱ በሚቃረን የንድፈ ሀሳብ መነጽር ለማየትና ለመተርጎም የሚሞክሩት ለምንድን ነው? እንደ እውነቱ ከሆነ የዝግመተ ለውጥ ንድፈ ሃሳብ ግድፈት ጠራርጎ የወሰደው በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዓለማዊያንን ብቻ አይደለም፤ ይልቁንም ራሳቸውን ክርስቲያን ብለው የሚጠሩ አያሌዎች በዚህ ሁሉ ያፈጠጠ ተቃርኖ መሃል ከክርስትና እምነታቸው ጋር አዋህደው መያዝ እንደሚችሉ ያምናሉ፡፡

የዝግመተ ለውጥ ንድፈ ሀሳብ ከመጨረሻዎቹ ቀናት አንደምታ ሲታይ የማታለሉን አደጋ ይበልጥ ጉልህ ያደርገዋል፡፡ የፍጥረት ሂደት ስድስት ቀናት ሳይሆን 3 ቢሊዮን ዓመታት ገደማ ወስዶ እያለ፤ አንዱ ቀን ማለትም ሰባተኛው

ቀን ሰንበት እንደ መታሰቢያ የሚወሰደው ለምንድን ነው? የዝግመተ ለውጥ ንድፈ ሃሳብ የስድስቱን ቀናት የፍጥረት ሥራ በምናባዊው "ታሪኬ ባጭሩ" ዓይነት ልቦለድ ስለሚተካው ሰንበት ባዶና ትርጉም አልባ ይሆናል፡፡ ደግሞም የፍጥረት ሥራ ስድስት ቀናት ሳይሆን ቢሊዮን ዓመታት ወስዶአል የሚለውን ንድፈ ሃሳብ በውስጣቸው እያመኑ፣ ነገር ግን እሁድን ተቃውመው ለሰንበት ቢቆሙ ሊመጣ ያለውን የስደት ወይም የሞት አደጋ ተጋፍጦ ለመቆም የሚያስችል ጽናት ሊኖራቸው ይችል ይሆን?

## ሐሙስ ግንቦት 23

## አስመሳዩ ሦስት አካል አንድ አምሳል

እግዚአብሔር በሦስት ባህሪያት የመገለጹ ጽንሰ ሃሳብ በመላው የመጽሐፍ ቅዱስ ገጾች ይገኛል፡፡ ሆኖም ራእይ 13 ከመጨረሻው ጊዜ ማታለያና ስደት ዐውድ ዲያብሎስ ሦስት አካል ይዞ ብቅ የሚል ሲሆን እነርሱም፡ ዘንዶው፣ ከባህር የሚወጣው አውሬ እና ከምድር የወጣው አውሬው ናቸው፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 12፡17፣ 13፡1-2፡፡ በእነዚህ ስፍራዎች ምን ተገልጾ እናገኛለን?**

---

---

በዚህ ስፍራ የቀረበውና የአብን ስፍራ በመያዝ የሚያስመስለው ዘንዶ ሁሉም ነገር በእርሱ ቁጥጥር ስር እንደሆነ በግልጽ ይስተዋላል፡፡ ክርስቶስን ለሚያስመስለው ከባሕር የወጣው አውሬ ደግሞ--ኃይል፣ ሥልጣን እና ዙፋን ሲሰጠው ይታያል፡፡ ለመሆኑ ይህ ሁለተኛው ኃይል ክርስቶስን የሚያስመስል ሆኖ የታየው ለምንድን ነው?

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 13፡2-5፡፡ ለመሆኑ የዚህ ከባሕር የወጣ አውሬ ባህሪያት ምንድን ናቸው?**

________________________________________________

________________________________________________

የሱስ ሥልጣን ከአብ እንደተቀበለ (ማቴ. 28፡18) አውሬውም ከዘንዶው ኃይል መቀበሉ፤ ከባህር የወጣው አውሬ እንደ የሱስ ሞት እና ትንሣኤ የሚመስል (ራእ. 13፡3) አስመሳይ ትዕይንት ውስጥ ማለፉ፤ እንዲሁም ይህ አውሬ ሥልጣኑን "ለአርባ ሁለት ወራት" ወይም ለሦስት ዓመት ተኩል ጥቅም ላይ እንዳዋለ የተገለጸ ሲሆን ከስተቱ የክርስቶስን ሦስት ዓመት ተኩል የፈጀ ምድራዊ አገልግሎት ማስመሰልን ያመለክታል፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 13፡11-17፡፡ ከምድር የወጣው አውሬ የተገለጸበት መንገድ ምን ይመስላል?**

________________________________________________

________________________________________________

መንፈስ ቅዱስ ራሱን ሳይሆን የሱስን ከፍ ከፍ እንዳደረገ ሁሉ ይህ ከምድር የወጣ አውሬም ከባሕር የወጣውን አውሬ ፍላጎት የሚያስፋፋና የሚያዳብር ሥራ ይሠራል (ዮሐ. 16፡13-14)፡፡ እንዲሁም መንፈስ ቅዱስ ከሰማይ "እሳት" እንዳወረደ (ሐዋ. 2፡3) ከምድር የወጣውም አውሬ ተመሳሳይ የማስመሰል ድርጊት ይፈጽማል (ራእ. 13፡13)፡፡

"በስተ መጨረሻ ከምድር የወጣው አውሬ በጴንጤቆስጤ ወቅት ገቢራዊ የሆነው ዓይነት የማስመሰል ሥራ ይሠራል፡፡ ለምን ዓላማ? አስመሳዩ ሦስት አካል እግዚአብሔር እንደሆነ የሚገልጽ ማረጋገጫ ለመስጠት"—*Jon Paulien, What the Bible Says About the End-Time (Hagerstown, Md.: Review and Herald® Publishing Association, 1998), p. 111.*

**በንቃት ልንከታተላቸው የሚገቡ ሌሎቹ የመጨረሻው ጊዜ ክስተቶች ምንድን ናቸው? ሌሎች ወገኖች እነዚህን ማታለያዎች መገንዘብ ይችሉ ዘንድ እንዴት ልንረዳቸው እንችላለን?**

## አርብ ግንቦት 24

***ተጨማሪ ሀሳብ፡*** *የዝግመተ ለውጥ ንድፈ ሀሳብን ከመጨረሻው ጊዜ ክስተቶች ዐውድ ጠለቅ ብለን ለመመልከት እንሞክር--በተለይ ከሰንበት ጋር ከሚኖረው ሚና፡፡ የዚህ ንድፈ ሃሰብ አመንጪ የሆነው ቻርለስ ዳርዊን ይህን ሃሳብ ያበረታታበት አንዱ ምክንያት በብርሃን እና በጨለማው ኃይል መካከል እየተካሄደ ያለውን ታላቁን ተቃርኖ ማስተዋል አለመቻሉ ነው፡፡ ዳርዊን ክፋውንና በሥቃይ የተሞላውን ትዕይንት በቸርነት ከተሞላውና አፍቃሪ ከሆነው ፈጣሪ ጽንሰ ሃሳብ ጋር ለማስታረቅ በእጅጉ ተቸግሮ ነበር፡፡ በዚህ ስህተት መንስኤ ምላሽ ፍለጋ ወደ ሌላ አቅጣጫ አማተረ፡፡ ጊዜው በ1800 ዓ.ም. አጋማሽ እና መጨረሻ አካባቢ ነበር፡፡ ነገሩ አጋጣሚ ይሁን ወይም አይሁን--ዳርዊን የዝግመተ ለውጥ ንድፈ ሃሳቡን እየፈተሸና እያደራጀ በነበረበት በዚያን ወቅት እግዚአብሔር ለንድፈ ሃሳቡ አጸፋዊ ምላሽ ለመስጠት የፈለገ ይመስል የሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተ ክርስቲያንን እንቅስቃሴ አስነሳ፡፡ ለአምላካዊው የፍጥረት ሥራ ያላት ድጋፍና መሰረት በስያሜዋ የተገለጠው ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተ ክርስቲያን፤ የዳርዊን ንድፈ ሃሳብ ከተጸነሰበት ተመሳሳይ ጊዜ አንስቶ እነሆ እያደገችና እየተመነደገች መሄዷን ማወቅ በእርግጥም መሳጭ ነው፡፡*

*ምናልባት ኤለን ኋይት ከዚህ እንደሚከተለው የጻፈቻቸውን አጭር መስመሮች ዳርዊን አንብቦና አገናዝቦ ቢሆን ኖሮ ማን ያውቃል--ዓለም ከእንዲህ ዓይነቱ የጅል ስህተት መጠበቅ በቻለች ነበር፡፡ “ምንም እንኳ ምድር በመቅሰፍት ብትመታም፤ ተፈጥሮ አሁን ድረስ የሰው ልጆች መማሪያ መጽሐፍ ነው፡፡*

እዚህም፣ እዚያም በየስፍራው የተሰራጨው ክፉው በጣር ውስጥ የሚገኘውን የብስ፣ ባሕርም ሆነ አየር እያረከሰ በመሆኑ--ተፈጥሮ መልካም የሆነውን ነገር ብቻ መወከል አይችልም፡፡ በአንድ ወቅት የመልካም ዕውቀት መገለጫ የነበረውና የእግዚአብሔር ባህሪ ብቻ የተጻፈበት ተፈጥሮ፤ አሁን ግን የክፉው ዕውቀት የሆነው--የሰይጣንም ባህሪ አረፈበት፡፡ ሰው ዛሬ የመልካሙንና የክፉውን ዕውቀት ገልጦ ካሳየውና የኃጢአትን ውጤት ካመጣው ከተፈጥሮ እንዲጠበቅ በተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ነበር፡፡"—*Education,* p. 26.

ዳርዊን ተፈጥሮን፣ የእግዚአብሔርን ባህሪ እና የምንኖርባትን የወደቀች ምድር በተሳሳተ መንገድ በማስተዋሉ በሐሰት ላይ በተመሰረተ መላ ምት የዝግመተ ለውጥ ንድፈ ሃሳብን ፈጠረ፡፡ የእርሱ ንድፈ ሃሳብ አንደምታዎች በተለይ በመጨረሻው ቀውስ ሰዎችን የሰይጣን ማታለያ ታዳኝ ማድረጋቸው በእጅጉ አሳዛኝ ነው፡፡

## የመወያያ ጥያቄዎች፡

1.ብዙዎች የሰይጣንን መኖር ጽንሰ ሃሳብ የሚቃወሙት ለምንድን ነው? በግልጽ የቀረበውን የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ መቃወም ምን ያህል አደገኛ እንደሆነ ይህ አመለካከት ምን ያስተምረናል?

2.ለሞት በቀረበ ተሞክሮ በማለፍ ከሞት በኋላ ህያው እንደሆንን እንቀጥላለን የሚል ሰው ቢገጥሞት ምን ዓይነት ሀሳብ ሊያካፍሉት ይችላሉ? (የማክሰኞ ትምህርት)

3.በዝግመተ ለውጥ ንድፈ ሀሳብ የሚያምኑ ሰዎች ለመጨረሻዎቹ ቀናት ማታለያዎች በጣም የተጋለጡ ስለ መሆናቸው እርስዎ ሊያቀርቡ የሚችሉት ለየት ያለ ምክንያት ምንድን ነው?

# አስረኛ ትምህርት

ከግንቦት 25 -- ሰኔ 1

# አሜሪካ እና ባቢሎን

## ሰንበት ከሰዓት

***ለዚህ ሳምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፣ ራእ.*** *13:1–12፣ 14:9–11፣ 16:2፣ 19:20፣ 20:4፣ ኤር. 51:6-7፣ 53፣ 57፣ ራእ. 18:1–4፡፡*

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡-**

***" 'በዚያን ዘመን ስለ ሕዝብህ የሚቆመው ታላቁ አለቃ ሚካኤል ይነሳል፡፡ መንግሥታት ከተመሠረቱበት ጊዜ ጀምሮ እስከዚያ ዘመን ድረስ ታይቶ የማይታወቅ ታላቅ የመከራ ጊዜ ይሆናል፡፡ ነገር ግን በዚያን ጊዜ ስማቸው በመጽሐፉ ተጽፎ የተገኘው ሕዝብህ ሁሉ ይድናሉ፡፡"*** **(ዳን. 12፡1)፡፡**

ባለፈው ሣምንት ጥናታችን ስለ አስመሳዩ ስላሴ ማለትም ሰይጣን (ዘንዶው) እና ሁለቱ የምድር ኃይላት የተመለከትን ሲሆን እነዚህ በአንድነት በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ስደት ያደርሳሉ፡፡

ከእነዚህ ኃይላት አንዱ የሆነው ከባሕር የወጣው አውሬ (ራእ. 13፡1-10) ከነብር፣ ከድብ እና ከአንበሳ የተውጣጣ አካል የነበረው ሲሆን (ራእ. 13፡2) እነዚህ ምስሎች በቀጥታ የተወሰዱት ከዳን 7፡4-6 ነው፡፡ በስድስተኛው ሣምንት ጥናታችን--ከባቢሎን (አንበሳ)፣ ሜዶንና ፋርስ (ድብ) እና ግሪክ (ነብር)--በኋላ ሮም የመጨረሻው የምድር ልዕለ ኃያል ሆኖ እንደሚወጣ ተመልክተናል፡፡ ከአረማዊው ሮም ማለትም ከዚህ አራተኛው አውሬ ላይ የሚነሳው ትንሹ ቀንድ ኃይል በቀጥታ ወደ ሮም ጳጳሳዊ ሥርዓትነት ይለወጣል በዳን. 7፡7-8፣ 19-21፣ 23-25፡፡ እንዲሁም በዳን. 7 የተገለጸው አብዛኛው የጳጳሳዊው ሥርዓት ጸባይ

ከባሕር በወጣው አውሬ (ራእ. 13፡1-10) ውስጥ እንደሚታይ ተመልክተናል፡፡ የሆነው ሆኖ ሮም ብቻውን ሳይሆን ሌላም ኃይል እንዳለ ተገልጾአል፡፡ በዚህ ሣምንት አብዛኛው ትኩረታችን በራእ. 13 በተገለጹ ኃይላትና ጉዳዮች ዙሪያ ይሆናል፡፡ እንደ ተለመደው እንዲህ በማለት እንጠይቃለን፡ ለመሆኑ የእነዚህ ሁኔታዎች ፍቺ ምንድን ነው? መዘጋጀት የምንችለውስ እንዴት ነው?

እሁድ ግንቦት 26

## ለሞት የሚያደርሰው ቁስሉ መዳን

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 13፡1-10፡፡ እነዚህ ጥቅሶች ጳጳሳዊው ሥርዓት ቀደም ባሉት ጊዜያትም ሆነ ወደፊት ስለሚኖረው ሚና ለምን እንደሚጠቅሱ ምክንያቶቹን ለመመልከት ይሞክሩ፡፡ በተለይ ምን ያህል በግልጽ የሚታይ ሚና እንዳለው ልብ ይበሉ፡፡ ይህ ከመጨረሻዎቹ ቀናት ክስተቶች አኳያ ምን ማለት ነው?

__________________________________________________________

__________________________________________________________

ምንም እንኳ እግዚአብሔር በተለያዩ ቤተ ክርስቲያኖች የሚያመልኩ ታማኝ ሕዝቦች ቢኖሩትም ነገር ግን ይህ ኃይማኖታዊ ተቋም ቀደም ባለው ታሪክ የተጫወታቸውና ወደፊትም በመጨረሻዎቹ ቀናት በዓይነታቸው ልዩ የሆኑ ሚናዎች እንደሚኖሩት መጽሐፍ ቅዱስ ያመለክታል፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 13፡3፡፡ እዚህ ላይ እየሆነ ያለው ነገር ምንድን ነው? ስለ ሮም ታዋቂነትና ዝና ምን ያስተምረናል?**

__________________________________________________________

__________________________________________________________

የሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የእምነት ማዕከልና በብዙ መንገድ የምዕራቡ ዓለም የፖለቲካ እምብርት ሆና ለምዕተ ዓመታት ዘልቃለች፡፡ ሰላም ለመፍጠር ሲል ወደ ተቆጣው ጳጳስ ግሪጎሪ 7ኛ የመኖሪያ ቅጥር አምባ መጥቶ የነበረው የሮም ንጉሥ ቅዱስ ሔነሪ 4ኛ ታሪክ የቤተ ክርስቲያኗን ኃይልና ሥልጣን ማሳየት ከቻሉ ምሳሌዎች መሃል የሚጠቀስ ነው፡፡ የሚገርመው ይህ የሮማ ንጉሥ የጳጳሱን የመግቢያ ፈቃድ አግኝቶ ወደ ውስጥ እስኪዘልቅ ለሦስት ቀናት የአውሮፓን ክረምት ቁር እና ብርድ ተቋቁሞ በቅጥሩ ደጃፍ እንዲቆይ ተደርጎ ነበር፡፡ ባገኘው ድል ልቡ የታበየው ጀርጅ 7ኛ የነገሥታትን ኩራት ድባቅ መትቶ ልክ ማግባት የእርሱ ተግባር መሆኑን በኩራት ሲናገር ተደምጦ ነበር፡፡

ሆኖም ቤተ ክርስቲያኒቱ በገጠማት ተሐድሶ፣ ወጣ ያለ አስተምህሮ እንዲሁም በፈረንሳይ አብዬት የተነሳ የሮም ፖለቲካዊ እና ኃይማኖታዊ የበላይነት በአሥራ ስምንተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ አከተመለት፡፡ ከጳጳሳቱ አንዱ የነበረው ፒየስ 6ኛ በ1798 በፈረንሳይ ሠራዊት በምርኮ ከተወሰደ በኋላ በ1799 በግዞት እያለ ሞቶአል፡፡

ሆኖም ራእ. 13 “ለሞት የሚያደርሰው ቁስሉ ዳነ” በማለት ስለ ማንሰራራቱ ይናገራል፡፡ ምንም እንኳ ዛሬ ሮም በንጉሥ ግሪጎሪ 7ኛ ዘመን እንደ ነበረው ሥልጣኑን በሙሉ ኃይሉ የሚጠቀምበት ሁኔታ ላይ ባይሆንም ነገር ግን ለዘመኑ ጳጳሳት ክብርና ዝና ምስጋና ይግባውና በኃይማኖትም ሆነ በፖለቲካ ተጽእኖ ፈጣሪ ኃይል ለመሆን በቅቶአል፡፡ (ለአብነት ያህል ሊቀ ጳጳስ ፍራንሲስ በአውሮፓውያኑ ቀመር 2015 ላይ በሁለቱም የአሜሪካ ምክር ቤቶች ተገኝተው ያደረጉት ንግግር በዓይነቱ የመጀመሪያ እና ታሪካዊ ነበር፡፡) በመጽሐፍ ቅዱሳዊው ትንቢት መሰረት ይህ ተጽእኖ እያደገና እየተመነደገ የሚሄድ ነው፡፡ **በተቻለን መጠን የሰዎችን ስሜት ሳንጎዳ እንድንሰብክ ለተጠራንበት መልእክት ታማኝ መሆን የምንችለው እንዴት ነው?**

## ሰኞ ግንቦት 27

## ዩኤስ አሜሪካ በትንቢት

ሮም በራእ. 13 የተገለጸው ዓይነት ተጽእኖ ዛሬም ሆነ ወደፊት ሊኖራት የሚችለው እንዴት ነው? በማለት ብዙዎች ይጠይቃሉ፡፡ ሮም የጦር ሠራዊት ታዝ የነበረበት ጊዜ ካከተመ አያሌ ዘመናት ቢቆጠሩም ምላሹ በዚያው ራእ. 13 ላይ ይገኛል፡፡

**ጠቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 13፡11-12፡፡ የዚህን ኃይል ማንነት ለይተን እንድንገነዘብ የሚረዱን ምልክቶች ምንድን ናቸው?**

---

---

ይህኛውን አውሬ ተከትሎ ወደ ሥልጣን የሚመጣውና ለአርባ ሁለት ወራት ሥልጣን የተሰጠው ኃይል (ራእ. 13፡5) ሮም እንደሆነ ተደርጎ ለረጅም ዘመናት በፕሮቴስታንቶች ታምኖአል፡፡ ጳጳሳዊው ኃይል ተቃዋሚዎቹን የጨቆነባቸው ጊዜያቶች አርባ ሁለቱ ወራት በዳን. 12፡6 "ለዘመን፣ ለዘመናት፣ ለዘመን እኩሌታም" በሚል ከተጠቀሰው ወይም ከሦስት ዓመት ተኩል (ራእ. 12፡44) ወይም ደግሞ ከ1260 ትንቢታዊ ቀናት (ራእ. 12፡6) ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ይህ ትንቢታዊ ጊዜ (አንድ ቀን እንደ አንድ ዓመት በሚለው የትንቢት ፍቺ መርኅ መሰረት) የጀመረው ጳጳሳዊው ሥርዓት ገናና በሆነበት 538 ዓ.ም. ሲሆን፤ ያበቃው ደግሞ ጳጳሱ በምርኮ በተወሰደበት ዓመት--1798 ዓ.ም. ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ ጳጳሳዊው ኃይል ለሞት የሚያደርሰውን ቁስል በመቀበሉ ትንቢቱ ፍጻሜ አገኘ፡፡

በዚህ ጊዜ አካባቢ ማለትም “አርባ ሁለቱ ወራት” (1798) መገባደጃ ላይ ሌላ ኃይል ብቅ ይላል (ራእ. 13፡11፣ 13፡1)፡፡ ይህ ኃይል የወጣው ከምድር ሲሆን ቀደም ብሎ ከባሕር (ከብዙ ሕዝብ መሃል) ከወጣው (ዳን. 7፡2-3) እና ቀደም ካሉት ከአብዛኞቹ ኃይላት ጋር ሲነጻጸር ልዩነት ነበረው፡፡ “‘ያየኸቸው ውሆች፡ ወገኖች፣ ብዙ ሰዎች፣ ሕዝቦችና ቋንቋዎች ናቸው’” (ራእ. 17፡15)፡፡

ይህ ኃይል ሰው ችምችም ብሎ ከማይኖርበት የምድር ክፍል የወጣ እንደመሆኑ፤ እንደ ሌሎቹ ሁሉ የትኛውንም ኃይል ገርስሶ መውጣት አላስፈለገውም፡፡ በእነዚህና በሌሎች ምክንያቶች የተነሳ ይህ ኃይል ዩኤስ አሜሪካ መሆኑን አፍ ሞልቶ መናገር ይቻላል፡፡

“በ1798 የዓለም ልዕለ ኃያል የመሆን ግስጋሴ በመጀመር ገናና የመሆን ተስፋ ሰንቆ የተነሳውና የዓለምን መንግሥታት ትኩረት የሳበው ማን ነበር? የዚህን ኃይል ማንነት ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋሉት ምሳሌያዊ አገላለጾችና አንደምታዎች የሚያጠያይቁ ዓይነት አይደሉም፡፡ የትንቢቱን ዝርዝር መመሪያ በትክክል የሚያሟላው አንድ እና አንድ ብቻ አገር ሲሆን ይኸውም ዩኤስ አሜሪካ ነው፡፡”—Ellen G. White, *The Great Controversy,* p. 440.

ምንም እንኳ መጀመሪያ ላይ ይህ ኃይል የጨዋነት ተምሳሌት በሆነው ሁለት ቀንዶች ባሉት በግ የተገለጸ ቢሆንም፤ ነገር ግን ውሎ አድሮ እንደ “ዘንዶ” (ራእ. 13፡11) ይናገራል፡፡ ይህ ደግሞ ቀደም ባለው ኃይል የሥልጣን ዘመን ገቢራዊ የሆነው ዓይነት የስደት ጊዜ መኖሩን ይጠቁማል፡፡ ሮም አስቀድሞ የተተነበየው ፍጻሜ ያገኝ ዘንድ እንዴት ተጽእኖ ማድረግ ትችላለች? ለሚለው ጥያቄ-- ከጀርባዋ የዩኤስ አሜሪካ ኃያል ድጋፍ ስላላት በቀላሉ ገቢራዊ መሆን ይችላል ሲል ራእ. 13፡11-17 መልስ ይሰጣል፡፡

# ማክሰኞ ግንቦት 28

## ፈታኙ የአምልኮ ጉዳይ

ጌታ በዘመናት በጣኦት እና በሌሎች የሐሰት አምልኮዎች ይወድቁ የነበሩትን ሕዝቦች ያለማቋረጥ መምራትና መታደግ ነበረበት (ማቴ. 4፡8-10)፡፡ በራእ. 13 እንደ ተገለጸው በመጨረሻው ቀውስ ወቅት የአምልኮ ጉዳይ ገንኖ ይወጣል፡፡ እዚህ ላይ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ማንን ማምለክና ማገልገል እንደሚኖርባቸው ምርጫ ማድረጋቸው የግድ ይሆናል (ኢያ. 24፡15)፡፡

ቀደም ብለን "ዳንኤልና የመጨረሻው ጊዜ" በሚል ርዕስ ባጠናነው ሁለተኛው ሰንበት ትምህርታችን "ለወርቁ ምስል" (ዳን. 3፡5) እንዲሰግዱ የታዘዙትን ዕብራውያን ወጣቶች ታሪክ ተመልክተን ነበር፡፡ እንዲሁም ራእ. 13 በመጨረሻው ጊዜ የእግዚአብሔር ሕዝቦች የሚደርስባቸውን ስደት ለመግለጽ ከዚያኛው ምዕራፍ እንዴት ቃላቶችን እንደ ተጠቀመ ተመልክተናል፡፡ ይህ ማለት ዳን. 3 በግምባር ቀደም ያስቀመጠውን መመልከታችን፤ በራእ. 13--መጨረሻዎቹ ቀናት የሚሆነውን ለማወቅ ያስችለናል፡፡ ቀደም ባለው ዘመን ሁሉም ሰው ከወርቅ ለተሠራው ምስል እንዲሰግድ ያለበለዚያ ግን በሚነደው እቶን እሳት ውስጥ እንደሚጣል ብርቱ ትእዛዝ ተሰጥቶ እንደ ነበር ሁሉ በተመሳሳይ ወደ ፊት "ለዚህ ምስል የማይሰግዱ ሁሉ እንዲገደሉ" (ራእ. 13፡15) የሚያዝ ትእዛዝ ይወጣል፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 14:9–11፤ 16:2፤ 19:20፤ 20:4፡፡ የአምልኮ ጉዳይ እጅግ ወሳኝ እንደሚሆን አስመልክቶ ጥቅሶቹ ምን ይነግሩናል?**

---

---

ባቢሎን ሁሌም የምትወሳው በሐሰት አምልኮ ርዕሰ መዲና ተምሳሌትነት ነው፡፡ የባቤል ግንብ ሉሲፈር "ከደመናዎችም ከፍታ በላይ ዐርጋለሁ" (ኢሳ. 14፡14)

እንዳለው ዓይነት የገንቢዎቹን ብርቱ ምኞት ያንጸባረቀ እንደ መሆኑ፤ እግዚአብሔር ከዚህ በኋላ ምድርን በውሃ እንደማያጠፋ (ዘፍ. 9፡8-11) የገባውን ቃል ለመቀበል በመቃወም ራሳቸውን ለማዳን ያደረጉትን ጥረት የሚያሳይ ነበር፡፡

የባቢሎን መንግሥት ከቀድሞው በተመሳሳይ ለሰብዓዊው የእጅ ሥራ ውጤት ከፍ ያለ አክብሮት የሰጠ ነበር፡፡ ናቡከደነፆር “ያሠራኋት ታላቂቷ ባቢሎን ይህች አይደለችምን?” (ዳን. 4፡30) በማለት ራሱን በማወደስ ተመጻደቀ፡፡ ከዚያም በእርሱ እግር የተተካው ልጁ ንጉሥ ቤልሻዛር ሰሎሞን ከሠራው የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የወርቅ መጠጫዎችን በማስመጣት “ንጉሡና መኳንንቱ፣ ሚስቶቹና ቁባቶቹም ጠጡባቸው፡፡ የወይን ጠጁንም እየጠጡ የወርቅና የብር፣ የናስ፣ የብረት፣ የእንጨትና የድንጋይ አማልክት አመለኩ” (ዳን. 5፡3-4)፡፡ እዚህ ላይ የቤተ መቅደሱ እውነተኛ መጠጫዎች በሚያሰክር የወይን ጠጅ መሞላታቸውንና ከዚያ የጠጡ ሁሉ ምን ያህል እንደ ደነዘዙና የማገናዘብ አቅማቸውን እንዳጡ ልብ ማለቱ ተገቢ ነው፡፡ ይህን ተከትሎ ባቢሎን ስትወድቅ በከተማዋ ከነበሩት መሃል ብዙዎቹ ጠፉ፡፡ ውጪያዊው የታይታ እውነት ጭምብል በገዳዩ “የባቢሎን ወይን ጠጅ” ሊያስተን ይችላል፡፡ ሐሰተኛ አምልኮ እና ሐሰተኛ ጽንሰ ሀሳቦች ለሰይጣናዊው መንግሥት ገንዘቡ ናቸው፡፡

**ዛሬ የማንኛውም ሐሰት አምልኮ ተካፋይ ላለመሆናችን ምን ያህል እርግጠኞች መሆን እንችላለን?**

## ረቡዕ ግንቦት 29

## “ታላቂቱ ባቢሎን”

**የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡፡ ጥቅሶቹ ስለ ባቢሎን ምን ያስተምሩናል? ኤር. 51:6-7፣ 53፣ 57፣ ዘካ. 2:7፣ ራእ. 17:5-6፣ 18:2-3፡፡**

---

ባቢሎን በሐሰት አምልኮ ርዕሰ መዲናነት ረጅም ታሪክ እንዳላት በትናንቱ ጥናታችን ተመልክተናል፡፡ ይህ ደግሞ ሕዝቦችን ለሚያስተው ለመጨረሻው ጊዜ ኃይል ገጣሚ ያደርጋታል፡፡

**ዘንዶውን፣ ከባሕር የወጣውን አውሬ እና ቀዩን አውሬ ያስተያዩ (ራእ. 12፡3፣ 13፡1-3፣ 17፡3)፡፡ በመሃላቸው የሚስተዋሉት ተመሳሳይነትና ልዩነቶች ምንድን ናቸው?**

---

ሰባት ራሶችና አስር ቀንዶች ያሏቸው ሦስቱ አውሬዎች በዳን. 7 የቀረቡትን ራሶች እና ቀንዶች አጠቃላይ ድምር ይወክላሉ፡፡ እያንዳንዱ በሌላው እግር የተተካ ሥርዓት አዲሱን አገዛዝ የሚያጸናው በቀደመው ላይ ነበር፡፡ በተመሳሳይ ቀዩ አውሬ የዘንዶውን፣ ከባሕር የወጣውን አውሬ እና (በአረማዊውና ጳጳሳዊው ሮም ቅደም ተከተል ምሳሌ መሰረት) ከምድር የወጣውን አውሬ (ራእ. 13፡11-14) መሰረታዊ ባህርያት አጣምሮ መያዙ “ሦስቱንም የእግዚአብሔር ጠላት ኃይሎች በእውነተኛ ግንባርነት ይመድባቸዋል”—*Jacques B. Doukhan, Secrets of Revelation, The Apocalypse Through Hebrew Eyes (Hagerstown, Md.: Review and Herald® Publishing Association, 2002), p. 162.* በተጨማሪ በራእ. 17 በቀዩ አውሬ ላይ የተቀመጠችው ሴት በኃይማኖትና በፖለቲካ ኃይሎች መካከል የተከለከለውን የአንድነት መሰረታዊ ባህሪ በምሳሌ ያቀርባል፡፡ ይህች ሴት በራእ. 12 ከተገለጸችው ንጹህዋ ጋር ፍጹም ተቃራኒ ናት፡፡

| ንጹህዋ ሴት (ራእ. 12) | አመንዝራዋ ሴት (ራእ. 17) |
|---|---|
| በሰማይ | በውሆች ላይ |
| ፀሐይን የለበሰች | ሐምራዊና ቀይ ልብስ የተጎናጸፈች |
| ዐሥራ ሁለት ከዋክብት ያሉት አክሊል የደፋች | በወርቅ፣ በከበሩ ድንጋዮችና በዕንቁች ያጌጠች |
| በዘንዶው ጥቃት ይደርስባታል | በዘንዶው ትደገፋለች |
| የትሩፋን እናት | የአመንዝራዎች እናት |

የአመንዝራዎች እናት የሆነችው ባቢሎን ራስዋን በማባዛት ሥራ ተጠምዳለች፡፡ ክህደት የፈጸመችው ይህች እናት ቤተ ክርስቲያን አያሌ ክህደት የፈጸሙ ልጆች አሏት፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር በክርስትና ላይ ክህደት ስትፈጽም፣ ስህተት ስታውጅና ግፍ ስትሠራ የኖረችውን ተቋም የእኔ ሊላት አይችልም፡፡ ምንም እንኳ ሰይጣን እውነተኞቹ የእርሱ ሕዝቦች ላይ ጥቃት ቢፈጽምም፤ ለብዙ መቶ ዓመታት ተቋቁመው ማለፍ ችለዋል፡፡

ራእ. 14፡8 ስለ ባቢሎን ውድቀት ወይም በእውነት ላይ ስለሚፈጸም ክህደት ሕዝቡን በማጠንቀቅ፤ ውሎ አድሮ የአውሬውን ምልክት ወደ መቀበል ከሚወስደው የመጨረሻ ማሳቻ (ራእ. 14፡9-11) እንድንጠበቅ ያሳስበናል፡፡ ዛሬም በባቢሎን የሚገኙ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ከእርሷ ወጥተው ከመጨረሻው ጊዜ የእግዚአብሔር ትሩፋን ቤተ ክርስቲያን ጋር በአንድነት ይቆሙ ዘንድ (ራእ. 18፡4) ይህ ማስጠንቀቂያ እጅግ ብርቱ በሆነ ኃይል ለመጨረሻ ጊዜ ለሕዝቡ ይቀርባል፡፡

## ሐሙስ ግንቦት 30

## ሕዝቤ ሆይ፤ ከእርሷ ውጡ

የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት ተማሪዎች የዓለምን ሁኔታ በተለይ ከመጨረሻው ጊዜ ጋር እያስተያዩ በታላቅ ፍላጎትና ጉጉት ለዓመታት ሲፈትሹና ሲመረምሩ ቆይተዋል፡፡ ለምሳሌ ዩኤስ አሜሪካ በዚህ ዙሪያ ስለሚኖራት ሚና አሰብ ያድርጉ፡፡ አንዳንድ አድቬንቲስቶች ወደ ኋላ በ1851 አስገራሚ በሆነ መልኩ የአሜሪካንን ሁናቴ እንደ ሁለተኛው አውሬ ኃይል (ራእ. 13፡11-15) ለይተው መመልከት ችለው ነበር፡፡ በዚያን ዘመን ማለትም በ1800 ኢጋማሽ የዓለም ልዕለ ኃያላን ይባሉ የነበሩት የድሮዎቹ፡ ፐርሺያ፣ ፈረንሳይ፣ ኦስትሪያ-ሐንጋሪ እና እንግሊዝ ነበሩ፡፡ በዚያን ወቅት አሜሪካ የነበራት የወታደር ብዛት 20 ሺ ሲሆን ይህ አሃዝ በዋተርሉ ውጊያ (በ1815) ተሰልፈው ከነበሩት ወታደሮች ጋር ሲነጻጸር አንድ አሥረኛው ብቻ ነበር፡፡ አርባ ዓመት ቀደም ብሎ ማለትም በ1814 እንግሊዝ ወረራ አካሂዳ ዋሽንግቶን ዲሲን አቃጥላ ነበር፡፡ በ1867 ሲቲንግ ቡልስ በሚባል ይታወቅ የነበረ የአሜሪካ ጎሳ መሪና ተከታዮቹ በዩኤስ አሜሪካ ሰራዊት ላይ ውጊያ ከፍተው ሰባተኛውን የአሜሪካ ፈረሰኛ ሬጅመንት አዛዥ ጀነራል ከስተርን ጦር ከጥቅም ውጪ ማድረግ ችለው ነበር፡፡ ምንም እንኳ አንዳንዶች ዩኤስ አሜሪካ አንድ ቀን "የአውሬውን ምስል" በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚያጠናክር ኃይል ይሆናል ብለው ገና በጠዋቱ ለይተው በመመልከት አስተያየታቸውን መስጠት ቢችሉም፤ ነገር ግን በዚያን ወቅት ይህ አገር ገና ከምድሪቱ ነባር ቀይ ሕንዶች ጋር ይዋጋ የነበረና ሁሌም ድል የማይቀናው ዓይነት መንግሥት ነበረ፡፡

የዓለም ክስተቶች ይሆናሉ ብለን ባመንበት አቅጣጫ መጓዛቸውን መቀጠላቸው አጠያያቂ ባይሆንም ነገር ግን ወደ መጨረሻው ከመድረሳችን አስቀድሞ ገና ብዙ ነገሮች መገለጥ ይኖርባቸዋል፡፡ ለምሳሌ ስለ "አውሬው ምልክት" ስናወራ ዛሬ ሰዎች አራተኛውን ትእዛዝ እየጠበቁ ቢሆኑ ወይም

ባይሆኑ--ይህን ምልክት የተቀበለ ማንም ስለ አለመኖሩ አጽንኦት መስጠታችን በእጅጉ አስፈላጊ የሚሆነው ለዚህ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ገና ተጨማሪ መገለጥ የሚኖርባቸው ነገሮች አሉ፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 18፡1-4፡፡ በጥቅሱ እየሆነ ያለው ነገር ምንድን ነው? ይህን ነገር አሁን ማስታወሳችን አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው? ለዓለም ስላለን ተልዕኮ ጥቅሶቹ ምን ያስተምሩናል?**

________________________________________________

________________________________________________

እነዚህ ጥቅሶች በፖለቲካ፣ በሥነ ምግባርና በመንፈሳዊነት አብልጦ የዘቀጠውን ዓለም አስቀያሚ ምስል ይሰጡናል፡፡ የሐሰት ኃይማኖታዊ አስተምህሮ በዓለም ላይ የሚያስከትለውን ክፉ ተጽእኖ ይገልጹልናል፡፡ ሆኖም በዚህ መሃል ታላቅ ተስፋ የሚሰጥ ትዕይንት የሚስተዋል ሲሆን ይኸውም ከክብሩ ነጸብራቅ የተነሳ ምድር እንድትበራ ያደረገው ከሰማይ የመጣው ሌላ መልአክ ክስተት ነው፡፡ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ገና ያልተገነዘቡ ታማኝ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ከባቢሎን እንዲወጡ መጠራታቸው ሌላው እንዲያውቁ የተፈለገው ተጨማሪ ነጥብ ነው፡፡ ይህ ማለት ከባቢሎን የወጡት የእግዚአብሔር ሕዝቦች ገና ላልወጡት እስከ መጨረሻው የሚሠሩት ሥራ መኖሩን ያመላክታል፡፡

**ጌታ አሁንም በባቢሎን የሚገኙትን ጥቂት ወገኖች "ሕዝቦቼ" ብሎ መጥራቱ ለእኛ የሚሰጠው ትርጉም ምንድን ነው? ራሳችንን ከሌሎች ጋር ለማዛመድ በምናደርገው ሂደት ይህን ማስታወስ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?**

# አርብ ሰኔ 1

**ተጨማሪ ሀሳብ፡** ሰይጣን በእግዚአብሔር ሕግ ላይ የፈጸመው ጥቃት-- በራሱ በእግዚአብሔር፣ በሥልጣኑና በመንግሥቱ ላይ የተደረገ ጥቃት ነው፡፡ ዓለም በከባድ ቀውስ ውስጥ በምትወድቅባቸው በመጨረሻዎቹ ቀናት ሰይጣን "የእግዚአብሔርን ትእዛዛት" (ራእ. 12፡17፣ 14፡12) የሚጠብቁ ወገኖች ላይ ጥቃት ይከፍታል፡፡ ለዚህ መንስኤው በምድር ላይ በወኪሎቹ አማካይነት ለእርሱ ክብር ለመስጠት የሚቃወሙ ሕዝቦች እነርሱ ብቻ በመሆናቸው ነው፡፡ ቀደም ሲል በእግዚአብሔር ላይ በሰማይ ከፍቶት የነበረው ዘመቻ በዚህም ምድር የቀጠለ ቢሆንም ነገር ግን በሰማይ እንደ ተሸነፈ በዚህም ምድርም ድል ይሆናል፡፡ "በሰማይ ከተጀመረው ታላቁ ተቃርኖ አንስቶ የሰይጣን ዓላማ የእግዚአብሔርን ሕግ መገርሰስ ነው፡፡ በፈጣሪ ላይ ዐመጻ ያደረገው ይህን ዕኩይ ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ ሲል ነበር፡፡ ምንም እንኳ ከሰማይ ወደ ምድር ቢጣልም ያንኑ የውጊያ ስልት እንደገፋበት ይገኛል፡፡ ሰዎችን ማሳትና የእግዚአብሔርን ሕግ እንዲጥሱ መምራት ጽኑና የማያወላውል ዓላማው አድርጎ ገፍቶበታል፡፡ ሁሉም የሕጉ ክፍል እንዲወገድ ማድረግ ወይም አንዱን ብቻ ነጥሎ ማስወገድ-- ውሎ አድሮ የሁሉም ውጤቱ አንድና ተመሳሳይ ነው፡፡ 'ምክንያቱም ሕግን ሁሉ የሚፈጽም ነገር ግን በአንዱ የሚሰናከል ቢኖር፣ ሁሉን እንደ ተላለፈ ይቆጠራል' ያዕ. 2:10"—Ellen G. White, *The Great Controversy,* p. 582.

## የመወያያ ጥየቄዎች፡

1.በሰንበት ትምህርት ጥናት ክፍለ ጊዜ በዓለም ሁናቴዎች ዙሪያ በመነጋገር እነዚህ ሁናቴዎች በምን መልኩ ይሆናሉ ብለን የምናምንባቸውን አቅጣጫዎች እንደሚያመለክቱ ተነጋገሩ፡፡ ገና ያልተገለጡት ክስተቶች የትኞቹ ናቸው? መጽሐፍ ቅዱስም ሆነ የኤለን ኋይት ጽሑፎች በግልጽ የማያስተምሩትን ጊዜ የመወሰን፣ የድፍረት ትንበያዎችንና አክራሪ አመለካከቶችን እያስወገድን--የጊዜውን ምልክቶች ሁሌም በንቃት መጠባበቅ የምንችለው እንዴት ነው?

2.በአምልኮ ጥያቄ ዙሪያ ጊዜ ወስዳችሁ ተነጋገሩ፡፡ አንድን ነገር ማምለክ ሲባል ምን ማለት ነው? የምናመልከው ምንም ይሁን ምን--አምልኮአችን መሆን ያለበት እንዴት ነው?

3.እግዚአብሔር ዛሬም በባቢሎን ሕዝቦች አሉት በሚለው ጽንሰ ሃሳብ ዙሪያ በደንብ ተወያዩ፡፡ “ባቢሎን” የሚለውን (ተምሳሌታዊ) ቃል ፍቺ የምናስተውለው እንዴት ነው? ሰዎች የቱንም ዓይነት ፖለቲካዊ አመለካከት ቢያራምዱ ወይም ኃይማኖታዊ አቋም ቢይዙ--የተሰጠንን መልእክት ለእነርሱ የመስበክ ግዴታችንን መቀጠል እንዳለብን አስመልክቶ ይህ ምን ያስተምረናል?

# አስራ አንደኛ ትምህርት ከሰኔ 2 – 8

## የእግዚአብሔር ማኅተም ወይስ የአውሬው ምልክት?

### ሰንበት ከሰዓት

***ለዚህ ሳምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡*** *ዘፍ. 17:9–11፣ ዘፀ. 31:13-17፣ ራእ. 13:17፣ ኤፌ. 1:13-14፣ ዕብ. 4:9-10.*

**የሀሳብ ማጠንጠኛ ጥቅስ**

**"ሁሉን ቻይ ጌታ አምላክ ሆይ፤ ሥራህ ታላቅና አስደናቂ ነው፡፡ የዘመናት ንጉሥ ሆይ፤ መንገድህ ጽድቅና እውነት ነው፡፡" (ራእ. 15፡3)፡፡**

የዚህ ሣምንት ጥናታችን መግቢያ ጥቅስ የሚጀምረው በሙሴ እና በበጉ መዝሙር ነው፡፡ በባሕሩ አጠገብ ቆመው ይህን መዝሙር የሚዘምሩት "አውሬውን፣ ምስሉንና የስሙን ቁጥር ድል የነሡት" ናቸው (ራእ. 15፡2) ከዚህ አሃዝ መሀል መሆን የምንችለው እንዴት ነው?

በመጨረሻው ዘመን እውነተኞቹ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ከሚለዩባቸው ምልክቶች አንዱ ሰዎች የአውሬውን ምልክት እንዳይቀበሉ የሚያስጠነቅቀውን የሦስተኛውን መልአክ መልእክት ማወጃቸው ነው፡፡ በዚህ ዙሪያ ተጨማሪ ማስጠንቀቂያ የሚሰጥ ጥቅስ አለመኖሩ በምልክቱ ምንነት ዙሪያ ለዓመታት ብዛት ያላቸው ግራ አጋቢ አስተሳሰቦች ሲንጸባረቁ ኖረዋል፡-በግንባር ላይ የሚታተም የምስጢር ቁልፍ፣ የክሬዲት ካርድ ቁጥር ወይም የግለ ታሪክ መታወቂያ ወዘተ፡፡

ከባቢሎን በሚወጡ በፍጥነት የሚያድጉና የሚሰራጩ ግራ አጋቢ ጽንሰ ሃሳቦች ፈጽሞ መደነቅ የለብንም፡፡ ደግሞስ ራሱ የስሙ ፍቺ "ድብልቅልቅ" አይደል? የእግዚአብሔር ትሩፋን ሕዝቦች የሦስተኛውን መልአክ መልእክት በኃይል ማወጅ ይችሉ ዘንድ በቅድሚያ በዚህ ርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ ግልጽ ማስተዋል ሊኖራቸው የግድ ይሆናል፡፡ በዚህ ሣምንት የአውሬው ምልክት ምን እንደሆነና የእግዚአብሔርን ማኅተም በመቀበል እንዴት ማስወገድ እንደሚቻል በተሻለ ለማስተዋል እንሞክራን፡፡

## እሑድ ሰኔ 3

## እግዚአብሔር ሕዝቡን የሚለይበት ምልክት

በብሉይ ኪዳን ዘመን እውነተኞቹ የእግዚአብሔር ሕዝቦች የሚለዩባቸው ሁለት ውጪያዊ ምልክቶች ነበሩ፡፡ ከእነዚህ አንዱ ደግሞ ግርዛት ነበር፡፡ ለመሆኑ መጀመሪያ ይህ ምልክት የተሰጠው ለማን ነበር? ዘፍ. 17፡9-11፡፡

____________________________________________

____________________________________________

____________________________________________

አብርሃም እና ከእርሱ በኋላ የሚመጣው ትውልድ እንዲገረዝና ይህን መገረዝ የደኅንነት ኪዳን ምልክትነት አድርጎ እንዲጠብቅ እግዚአብሔር አዞት ነበር፡፡ ወንዶች ልጆች በተወለዱ በስምንተኛው ቀን መገረዝ ነበረባቸው (ዘሌዋ. 12፡3)፡፡ ሆኖም ይህ ሥነ ሥርዓት ከፍ ያለ ኃይማኖታዊ አንደምታ የነበረው ሲሆን፤ ተምሳሌትነቱ የልብን "መገረዝ" ወይም መታደስ የሚያመለክት ነበር (ዘዳ. 30፡6)፡፡ ስለዚህ ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጽፎአል "አንድ ሰው ለይምሰል በውጫዊው ብቻ ይሁዲ ልሁን ቢል ይሁዲ አይሆንም፤ እውነተኛ ግዝረትም ውጫዊና ሥጋዊ ሥርዓት አይደለም፡፡ ዳሩ ግን አንድ ሰው ይሁዲ የሚሆነው

በውስጣዊ ማንነቱ ይሁዲ ሁኖ ሲገኝ ነው፡፡ ግዝረትም ግዝረት የሚሆነው በተጻፈው ሕግ ሳይሆን፣ በመንፈስ የልብ ግዝረት ሲኖር ነው፡፡ እንዲህ ያለው ሰው ምስጋናው ከሰው ሳይሆን ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው፡፡ (ሮሜ 2፡28-29)፡፡

እነዚህ በአዲስ ኪዳን የምናገኛቸው ጥቅሶች፡--1ቆሮ. 7፡19፣ ገላ. 5፡6 እና 6፡15 ግርዘት--ለኃጢአት በመሞት በአዲስ ሕይወት የመነሳት፣ የመለወጥና “አዲስ ፍጥረት” የመሆን ተምሳሌት በሆነው ጥምቀት መተካቱን ያሳዩናል፡፡ (ሮሜ 6፡3-4)፡፡ የግርዘት አስፈላጊነት ያከተመ መሆኑንና ጉዳዩ ያለው “በፍቅር ውስጥ በሚሠራ እምነት” እና “የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መጠበቅ” ላይ መሆኑን የሚናገረው ለዚህ ነው፡፡

እግዚአብሔር ሕዝቡ እንዲለይበት የሰጠው ሁለተኛው ውጪያዊ ምልክት ምን ነበር? ምልክቱ የተሰጠበት ምክንያት ምን ነበር? (ዘፀ. 31፡13፣ 17፣ ሕዝ. 20፡12፣20)፡፡______________________________________________

____________________________________________________________

ሰንበት በምልክትነት የተሰጠው ከፍጥረት አንስቶ መሆኑን ልብ ይሏል (ዘፍ. 2፡2-3)፡፡ ሆኖም የግርዘት ሥርዓት ግን ከአብርሃም ይጀምራል፡፡ በዚህ የተነሳ የሱስ የዘፍጥረት መጽሐፍን እንደ ማስረጃ በመውሰድ “ሰንበት ለሰው ተፈጠረ እንጂ ሰው ለሰንበት አልተፈጠረም” (ማር. 2፡27) በማለት ተናግሮአል፡፡ ይህ በፍጥረትም ሆነ (የእጆቹ ሥራ በመሆናችን) በመዋጀት (የሚያጸድቀንና የሚቀድሰን እርሱ በመሆኑ) የእርሱ መሆናችንን ያሳያል፡፡ በዚህ የተነሳ ምንም እንኳ ጳውሎስ የመገረዝ አስፈላጊነት ማከተሙን ቢናገርም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መጠበቅ ግን (ሰንበትን ጨምሮ) ዛሬም አስፈላጊ እንደሆነ ይናገራል (ዕብ. 4፡9)፡፡

**ልብዎ በእውነት መገረዙን አስተሳሰቦም ሆነ ውጥንዎ የሚያሳየው እንዴት ነው?**

## ሰኞ ሰኔ 4

## አውሬውና ሐሰተኛው አምልኮ

የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡፡ "የአውሬውን ምልክት" እንዴት ማስወገድ እንደሚቻል አስመልክቶ ምን ያስተምሩናል? ራእ. 13:17፣ 14:9፣ 10፡16:2

---

---

---

ከምህረት ጋር ያልተቀላቀለውን የእግዚአብሔር ቁጣ ተቀብለውና በሰባቱ የመጨረሻ መቅሰፍቶች ተመትተው በመጨረሻም በእሳት ሀይቅ ውስጥ የሚጣሉት--የአውሬውን ምልክት ላለመቀበል ጸንተው በድል አድራጊነት በብርጭቆው ባሕር አጠገብ ለእግዚአብሔርና ለበጉ የምስጋና ውዳሴ ከሚያቀርቡት ጋር ያላቸው ልዩነት እንዴት ግዙፍ ነው!

ለመሆኑ ይህ ማንም ቢሆን ሊቀበለው የማይሻው ምልክት ምንድን ነው? ከላይ የቀረቡት ጥቅሶች ጉዳዩን ከሐሰት አምልኮ ጋር በግልጽ ያገናኙታል፡፡ ቀደም ባለው ትምህርት በዳን. 7 የአራተኛውን አውሬ ኃይል እንደተመለከትነው በቀጣይ የለውጥ ምዕራፉ (በተጨማሪ ከባሕር የወጣ አውሬ በሚል በራእ 13 የተገለጸው) "ጊዜና ሕግን ለመለወጥ ይሞክራል" (ዳን. 7፡25)፡፡ ለመለወጥ ያሰበው አንድ ሕግ ሲሆን እርሱም አራተኛው ሕግ ይኸውም ሰንበት ነው፡፡ ከአሥሩ ትእዛዛት ውስጥ በቀጥታ ስለ ጊዜ የሚናገርና እግዚአብሔርን እንደ ፈጣሪ የሚያቀርብ ብቸኛው ትእዛዝ ይህ ብቻ ነው "ሰማይንና ምድርን፣ ባሕርንና በውስጡም ያሉትን ሁሉ በስድስት ቀን ፈጥሮ በሰባተኛው ቀን አርፎአል" (ዘፀ. 20፡11)፡፡

የመጀመሪያው መልአክ መልእክት መለስ ብለን ወደዚህ ትእዛዝ እንድንመለከት በማድረግ የአውሬው ኃይል ሕግን ለመለወጥ መሞከሩንና ጌታን ብቻ እንደ ፈጣሪ ማምለክ እንዳለብን በግልጽ ያስቀምጥልናል፡፡ በእርግጥ በራእ. 12-14 ስለ አምልኮ ከሚናገሩት ሰባት ቁጥሮች መካከል በእውነተኛ አምልኮ ዙሪያ የሚናገረው ይህኛው (14፡7) ብቻ ነው፡፡ ሌሎቹ ስድስት ቁጥሮች ለአውሬውና ለምስሉ የሚቀርቡ የሐሰት አምልኮዎችን ያስጠነቅቃሉ (ራእ. 13:4፣ 8፣ 12፣ 15፣ 14:9፣ 11)፡፡ ሦስተኛው መልአክ በዚህ የሐሰት አምልኮ ተሳታፊ የሚሆኑ ሰዎች ዕጣ ፈንታ ምን ሊሆን እንደሚችል እንደ ገለጠ፤ ወዲያውኑ እግዚአብሔርን በእውነት የሚያመልኩ እንዲህ በሚሉ ሃረጎች ተወስተዋል፡ "የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁና ለኢየሱስም ታማኝ ሆነው በትዕግሥት የሚጸኑ ቅዱሳን የሚታወቁት በዚህ ነው" (ራእ. 14፡12)፡፡

በሌላ አነጋገር የእነዚህ ሦስት መልእክቶች እወጃ መላውን የሰው ዘር በሁለት ጎራ ይከፍላል፡--ሰባተኛውን ቀን ሰንበት ጨምሮ ሁሉንም ትእዛዞች በመጠበቅ ፈጣሪን የሚያመልኩ እና አውሬውንና የእርሱን ምስል የሚያመልኩ፡፡ ከዚያም ይህ ሐሰተኛ ቅርጽ የያዘ አምልኮ ሰንበትን በመጠበቅ ፈጣሪን እናምልክ የሚል አማራጭ ይዞ ይመጣል፡፡

**በአምልኮና በታማኝነት መካከል ስላለው ግንኙነት በደንብ ለማሰብ ይሞክሩ፡፡ ለእግዚአብሔር ያለንን ታማኝነት ለማሳየት በእጅጉ አስፈላጊ የሆኑት የአምልኮ ገጽታዎች የትኞቹ ናቸው?**

**ማክሰኞ ሰኔ 5**

## የእግዚአብሔር ማኅተም

እንደ ፊርማ ሁሉ ማኅተምም ሰነድን ሕጋዊ ለማድረግ ይጠቅማል፡፡ በጥንት ዘመን ሕጋዊነትን ወይም ባለቤትነትን ለማሳየት ጥቅም ላይ ይውል የነበረው ማኅተም ለስላሳ በሆነ ሰም ወይም ሸክላ ላይ ይረገጥ ነበር፡፡

**የእግዚአብሔር ማኅተም ምንድን ነው? ጥቅም ላይ የሚውለውስ እንዴትና መቼ ነው? ኤፌ. 1፡13-14፣ 4፡30፣ 2ጢሞቴ. 2፡19፣ ራእ. 7፡1–4፣ 14፡1፡፡**

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

የእግዚአብሔር ማኅተም የባለቤትነቱና የሕዝቡ ከለላነት ምልክት ነው፡፡ ጳውሎስ መታተምን ከመለወጥና የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ከመቀበል ጋር አያይዞ ይገልጸዋል፡፡ ጳውሎስ ይህን ለሁሉም አማኞች የተሰጠ ስጦታ “ዋስትና” ወይም “መያዣ” ብሎ የሚጠራው ሲሆን ይኸውም ፍጹም የመዋጀታቸውና የሱስ ዳግም ሲገለጥ የሚቀበሉት ወራሽነት ነው፡፡

የራእይ መጽሐፍ ከዳግም ምጽአቱ ቀደም ብሎ ገቢራዊ ስለሚሆን ሌላ የመታተም ሥዕል ይሰጠናል፡፡ ይህ የመጨረሻ ማኅተም የሚሰጠው ለ144,000 ሲሆን ይኸውም የኋለኛው የመንፈስ ቅዱስ ዝናብ በሚዘንብበት ወቅት ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች በግንባራቸው ላይ የተጻፈ የእግዚአብሔር ስም (ወይም ፊርማ) አላቸው፡፡ መንፈስ ቅዱስ በሕይወታቸው በሚሠራው ሥራ አማካኝነት የእግዚአብሔርን ጸባይ ማንጸባረቅ ችለዋል፡፡

**የእግዚአብሔርን ማኅተም ከአውሬው ምልክት ጋር ያስተያዩ፡፡ በሁለቱ መካከል ምን ዓይነት ልዩነቶች ተጠቅሰዋል? ራእ. 7፡3፣ 14፡9፡፡**

አምላካዊው ማኅተም ለእውነተኛዎቹ የእግዚአብሔር አምላኪዎች ሲሰጥ፤ አውሬውን የሚያመልኩ ደግሞ ምልክቱን ይቀበላሉ፡፡ ማኅተሙ የሚያርፈው በግንባር ላይ ብቻ ሲሆን፤ ይህም ሰብዓዊው ፍጡር ነፃ የመምረጥ ችሎታውን ተጠቅሞ እግዚአብሔር ባዘዘው መሰረት እርሱን ማምለኩን ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩል ምልክቱ በግንባር ወይም በእጅ ላይ ይሰጣል፡፡ ይህ ደግሞ ሰዎች በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት አውሬውን ሊያመልኩ እንደሚችሉ ያሳያል፡፡ እግዚአብሔርን በእውነት እያመለኩ እንደሆነ በማሰብና በአእምሮአቸው ተስማምተው ወይም በጉዳዩ ሳያምኑ ግን ካልተመሳሰሉ ሊደርስባቸው የሚችለውን የከፋ ውጤት በመፍራት--ካልተመሳሰሉ መግዛትም ሆነ መሸጥ ካለመቻላቸው በተጨማሪ በስተመጨረሻ ስለሚገደሉ (ራእ. 13፡17-15)፡፡

"ከዓለም ጋር ሕብረት የሚፈጥሩ ዓለማዊውን ቅርጽ በመውሰድ የአውሬውን ምልክት ለመቀበል ይዘጋጃሉ፡፡ ራሳቸውን የሚክዱ፣ በእግዚአብሔር ፊት በታማኝነት የሚቀርቡና እውነትን በመታዘዝ ነፍሳቸውን የሚያነጹ፤ ሰማያዊውን ቅርጽ በመውሰድ የእግዚአብሔርን ማኅተም በግንባራቸው ለመቀበል ይዘጋጃሉ""—*Ellen G. White, Testimonies for the Church, vol. 5, p. 216.*

## ረቡዕ ሰኔ 6

## የአውሬው ምልክት

ለመሆኑ ይህ ከእኛ ልናርቀው የሚገባው ምልክት ምንድን ነው? ቀደም ባለው ትምህርታችን እንደ ተመለከትነው በዳን. 7 የቀረበው የአራተኛው አውሬ ኃይል በቀጣይ የለውጥ ምዕራፉ (በተጨማሪ በራእ. 13 ከባሕር በወጣው አውሬ የተገለጸው) "ጊዜና ሕግን ለመለወጥ ይሞክራል" (ዳን. 7፡25)፡፡ ለመለወጥ ያሰበው አንድ ሕግ ሲሆን እርሱም አራተኛው ሕግ ይኸውም ሰንበት ነው፡፡

ከአሥሩ ትእዛዛት ውስጥ በቀጥታ ስለ ጊዜ የሚናገርና እግዚአብሔርን እንደ ፈጣሪ የሚያቀርብ ብቸኛው ትእዛዝ ይህ ብቻ ነው “ሰማይንና ምድርን፣ ባሕርንና በውስጡም ያሉትን ሁሉ በስድስት ቀን ፈጥሮ በሰባተኛው ቀን አርፎአል” (ዘፀ. 20፡11)፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ የመጀመሪያው መልአክ መልእክት አንባቢውን የአውሬው ኃይል ሊለውጥ ወደ ሞከረው ወደዚህ ተመሳሳይ ትእዛዝ በማመላከት፤ እንደ ፈጣሪነቱ ልናመልከው የሚገባ ጌታን ብቻ እንደሆነ ግልጽ ያደርግልናል፡፡ ከዚያም በዚህ ምትክ “አውሬውንና የእርሱን ምስል” (ራእ. 14፡9) በሚያመልኩ ዕጣ ፈንታ ላይ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፡፡ የእግዚአብሔር ታማኝ ሕዝቦች በቁ. 12 ተገልጸዋል፡፡

**ጥቅሱን ያንብቡ፡ ራእ. 14፡12፡፡ ከዚህ ጥቅስ ዐውደ ሀሳብ በመነሳት ይህ የእግዚአብሔር ታማኝ ሕዝቦች የተገለጹበት መንገድ ሰንበት ለምን የመጨረሻዎቹ ክስተቶች ማዕከል እንደሆነ ማስተዋል እንድንችል እንዴት ይረዳናል?**

---

ጥቅሱ እንደሚከተለው ይነበባል፡ “የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁና ለኢየሱስም ታማኝ ሆነው በትዕግሥት የሚጸኑ ቅዱሳን የሚታወቁት በዚህ ነው፡፡” (ራእ. 14፡12)፡፡ በጥቅሱ እንደተመለከትነው እግዚአብሔርን እንደ ፈጣሪ እና እርሱ ብቻ ሊመለክ እንደሚገባው አድርጎ ወደ እግዚአብሔር የሚያመላክተው አራተኛው ትእዛዝ ሰንበት “የእግዚአብሔር ትእዛዛት” አካል ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ብዙዎች “የአውሬው ምልክት” ከእሑድ አምልኮ ጥያቄ ጋር በቀጥታ መያያዙን በመመልከት አስመሳዩ “ሰንበት” በመጽሐፍ ቅዱስ ያልታዘዘና አራተኛውን ትእዛዝ ከመጠበቅ በተቃራኒ የቆመ መሆኑን ቢመለከቱ የሚገርም አይሆንም፡፡

በዚህ አባባል መሰረት ዛሬ በእሁድ ቀን አምልኮ የሚያደርጉ ክርስቲያኖች የአውሬውን ምልክት ተቀብለዋል ማለት ይቻላል? በጭራሽ፡፡ በራእ. 13፡15 እንደቀረበው ይህን የአውሬውን የሐሰት አምልኮ ለመቀላቀል የሚቃወሙት ይገደላሉ፡፡ እንደውም በስተመጨረሻ አምልኮው የሕይወትና የሞት ጉዳይ ይሆናል፡፡ በእርግጥ ይህ ክስተት ገና ወደዚያ ነጥብ ባለመድረሱ የመጨረሻው ፈተና እስኪመጣ የአውሬው ምልክት አይሰጥም፡፡ ስለዚህ አሁን የአውሬውን ምልክት የተቀበለ ማንም የለም፡፡

**የእግዚአብሔር ትእዛዛት፡፡ የየሱስ እምነት፡፡ እውነተኛ ክርስቲያን ለመባል እነዚህ ባህሪያት ዛሬም ቢሆን ወሳኝ ገጽታ ያላቸው ለምንድን ነው?**

## ሐሙስ ሰኔ 7

## ሰንበት እንደ ማኅተም

በአዳምና ሔዋን የጀመረውና በዘመነ እስራኤል የቀጠለው ሰባተኛው ቀን ሰንበት፤ በምድር ታሪክ የእግዚአብሔር እውነተኛ ሕዝቦች ምልክት መሆኑን ተመልክተናል፡፡ እንዲሁም በየሱስ እና በደቀ መዛሙርት ፊት አውራሪነት በአዲስ ኪዳኗ ቤተ ክርስቲያን መቀጠሉን ተመልክተናል፡፡ የእግዚአብሔር የመጨረሻው ቀን ሕዝቦች መለያ ምልክት “የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁና ለኢየሱስም ታማኝ” መሆናቸው ነው፡ (ራእ. 14፡12)፡፡

**ሰንበት በጣም አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው? ለክርስቲያኖች ያለው የተለየ ትርጉም ምንድን ነው? ዘፀ. 20:8–11፤ ዕብ. 4:9-10፡፡**

ሰንበት በአስሩ ትእዛዛት አማካይ ስፍራ ላይ የሚገኝ ሲሆን፤ ይህ ትእዛዝ የሥልጣኑ ምልክት ወይም ማኅተም በመሆን በፈጣሪ ተሰጥቶአል፡፡ የስሙን መለያ ይዞአል፡ "የእግዚአብሔር የአምላክህን"፡፡ የሥልጣኑን ግዛት መለያ ይዞአል፡ "ሰማይንና ምድርን፤ ባሕርንና በውስጡም ያሉትን"፡፡ እንዲሁም የሥልጣኑን ምንጭ መለያ ይዞአል፡ "እግዚአብሔር በስድስት ቀን ፈጥሮ፤ በሰባተኛው ቀን አርፎአልና"፡፡

እግዚአብሔር በየሱስ ሁሉንም ነገር እንደፈጠረ አዲስ ኪዳን ይናገራል (ዮሐ. 1፡1-3፣ ቆለ. 1፡16፣ ዕብ. 1፡1-2)፡፡ ምድራችንን በስድስት ቀናት ፈጥሮ በሰባተኛው ቀን ያረፈ የሱስ ነው፡፡ ስለዚህ የሱስ አርብ ከሰዓት በመስቀል ላይ ከተሰቀለ በኋላ "ተፈጸመ!" (ዮሐ. 19፡30) ማለቱ ጥልቅ ትርጉም አለው፡፡ እርሱ የፍጥረት ሥራውን ጨርሶ በሰንበት እንዳረፈ ሁሉ፤ እኛን ለመዋጀት ሲል በእኛ ቦታ በመሞት ለኃጢአታችን መሥዋዕት የመሆን ሥራውን እንደ ፈጸመ፤ የሱስ በሰንበት በመቃብር አረፈ፡፡ በመሆኑም ሰንበት መጀመሪያ በፍጥረት ከዚያም በመስቀል ያለ ጥርጥር የተባረከ ነው፡፡ የዕብራውያን መጽሐፍ እንደሚናገረው ክርስቲያን በሰንበት ሲያርፍ "እግዚአብሔር ከሥራው እንዳረፈ እርሱም ደግሞ ከሥራው ያርፋል" (ዕብ. 4፡10)፡፡ ከመጀመሪያው አንስቶ እስከ መጨረሻ ክርስቶስ የሠራውን ሥራ በእምነት በመቀበል የዳንን እንደመሆናችን ሰንበት እኛ ራሳችንን ማዳን እንደማንችል የሚያሳይ ፍጹም ምሳሌ ነው (ዕብ. 12፡2)፡፡

**ሰንበት ከሥራችን የማረፋችን ተምሳሌት ከሆነ እሑድን መጠበቅ ምን ይወክላል? ከባቢሎን መሰረታዊ ባህሪ ጋር ገጣሚ የሚሆነውስ እንዴት ነው?**

## አርብ ሰኔ 8

**ተጨማሪ ሀሳብ፡** “የእግዚአብሔር ሕዝቦች በግንባራቸው ሲታተሙ በዐይን መታየት የሚችል ምንም ዓይነት ማኅተም ወይም ምልክት አይኖርም፡፡ ነገር ግን በአእምሮአቸውም ሆነ በመንፈሳዊ ህይወታቸው በእውነት ላይ ተመስርተው ስለሚቆሙ መናወጥ አያገኛቸውም፡፡ የእግዚአብሔር ሕዝቦች እንደ ታተሙና ለብጠራው እንደተዘጋጁ ጉዳዩ ገቢራዊ ይሆናል፡፡ በእርግጥ ገቢራዊ መሆን ከጀመረ ውሎ አድሮአል፡፡ እየመጣ ያለውን ነገር እናውቅ ዘንድ. . . እነሆ አሁን አምላካዊው ፍርድ በምድሪቱ ላይ ነው፡፡”—Ellen G. White, *The Faith I Live By*, p. 285.

“ሰንበት አወዛጋቢውን እውነት ማሳያ እንደመሆኑ ታላቅ የታማኝነት መፈተኛ ይሆናል፡፡ የመጨረሻው ፈተና በሰዎች ላይ በሚደርስበት ወቅት እግዚአብሔርን የሚያገለግሉትንና የማያገለግሉትን የሚለየው መስመር ይሰመራል፡፡ ሐሰተኛው ሰንበት ከመንግሥት ሕግ ጋር እጅና ጓንት ሲሆንና ከአራተኛው ሕግ ጋር ተቃርኖ ውስጥ ሲገባ፤ ሰንበት እግዚአብሔርን ለሚቃወመው ኃይል የታማኝነት ማረጋገጫ ይሆናል፡፡ የእግዚአብሔርን ሕግ በመታዘዝ እውነተኛውን ሰንበት መጠበቅ ለፈጣሪ ያለንን ታማኝነት የምናሳይበት ማስረጃ ነው፡፡ አንደኛው ክፍል ለምድራዊ ኃይላት በመታዘዝ የአውሬውን ምልክት ሲቀበል፤ ሌላኛው ለመለኮታዊው ሥልጣን የታማኝነት ምልክት የሆነውን የእግዚአብሔር ማኅተም ይቀበላል”—Ellen G. White, *The Great Controversy,* p. 605.

**የመወያያ ጥያቄዎች፡**

1.አላስፈላጊ ውዝግብ በማይፈጥር መልኩ ስለ አውሬው ምልክት እና ስለ እግዚአብሔር ማኅተም እውነታ ለሌሎች ማሳየት የምንችልባቸው መንገዶች የትኞቹ ናቸው?

2.ሰንበት እና በመንፈስ ቅዱስ መታተም የተዛመዱት እንዴት ነው? ከላይ በቀረበው ሀሳብ "በአእምሮአቸውም ሆነ በመንፈሳዊ ህይወታቸው በእውነት ላይ ተመስርተው ስለሚቆሙ" በሚለው ሀረግ ትርጉም ዙሪያ ተወያዩ፡፡

3.በመንፈሳዊቷ ባቢሎን እሴቶችና አሠራር መለያ ባህሪያት ላይ ተወያዩ፡፡ ባህሪያቱ ከእግዚአብሔር መንግሥት እሴቶች የሚለዩት እንዴት ነው? አንዳንድ የባቢሎን እሴቶች ዛሬ ወደ ቤተ ክርስቲያናችን አድብተው ሲገቡ የሚስተዋሉባቸው መንገዶች የትኞቹ ናቸው? የእግዚአብሔርን መንግሥት እሴቶች በሚያንጸባርቅ የክርስትና ምግባር የእነዚህን ነገሮች ምንነት መለየት መማርና መፍትሔ ማምጣት የምንችለው እንዴት ነው?

# አስራ ሁለተኛ ትምህርት ከሰኔ 9 – 15

## ባቢሎን እና አርማጌዶን

### ሰንበት ከሰዓት

***ለዚህ ሳምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ራእ.*** *14:8፣ 16:19፣ ኢሳ. 52:9፣ ራእ. 18:1-10፣ 16:12-16፣ 1ነገሥ. 18:1-40፣ 1ቆሮ. 15:1-2፡፡*

**የሳምንቱ ጥናት መሪ ጥቅስ፡-**

**“በግምባሯም ላይ እንዲህ የሚል የምስጢር ጽሑፍ ተጽፎ ነበር፦ ታላቂቱ ባቢሎን፣ የአመንዝሮችና የምድር ርኩሰቶች እናት።” (ራእ. 17፡5)።**

እስካሁን ባለን ግንዛቤ የራእይ መጽሐፍ ከብሉይ ኪዳን በቀጥታ በተወሰዱ ቋንቋዎችና ምስሎች የተሞላ መሆኑን ተመልክተናል፡፡ ለምሳሌ ባቢሎን የሚለው ስያሜ በራእይ መጽሐፍ ለስድስት ጊዜ ያህል ቢቀርብም፤ ከመቶዎች ዓመታት ቀደም ብሎ ከዓለም ታሪክነት ስላለፈው ልዕለ ኃያል የናቡከደነፆር መንግሥት ግን አይናገርም፡፡ ይልቁንም ዮሐንስ እውነትን ለማሳየት ሲል የብሉይ ኪዳን ተምሳሌታዊ አገላለጾችን ሲጠቀም ይታያል፡፡ የእግዚአብሔርን ሕዝቦች የጨቆነው ግዙፍ ፖለቲካዊና ኃይማኖታዊ ኃይል የነበረው ባቢሎን--በመጨረሻዎቹም ጊዜያቶች ተመሳሳይ ሁናቴ በእግዚአብሔር ሕዝቦች ላይ ለማድረስ ያስባል፡፡

በራእይ መጽሐፍ ብቻ የተጠቀሰ አንድ ቃል ያለ ሲሆን ይኸውም አርማጌዶን ነው፡፡ የዚህ ቃል መሰረት የዕብራይስጥ ሀረግ ሲሆን የጥንቷን እስራኤል አንድ ስፍራ በማያመላክት መልኩ “የጌዶ ተራራ” የሚል ፍቺ አለው፡፡

በዓለም ፍጻሜ ሲቃረብ በሜጊዶ ታላቅ ውጊያ ይካሄዳል ብለው ብዙዎች ያምናሉ፡፡

በዚህ ሣምንት ጥናታችን በባቢሎንና አርማጌዶን ላይ ምልከታ በማድረግ መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህን ምስሎች በመስጠት የሚናገረንን ለመማር እንሞክራለን፡፡

## እሑድ ሰኔ 10

## “የቁጣዋ ወይን ጠጅ”

የሚከተሉትን በባቢሎን ዙሪያ የተሰጡ ስድስት ማመሳከሪያዎች ይመልከቱ፡፡ ራእ. 14:8፣ 16:19፣ 17:5፣ 18:2፣ 10፣ 21፡፡ በብሉይ ኪዳን የቀረበውን የባቢሎን ታሪክ በአእምሮአችን እንደያዝን--ከመጨረሻዎቹ ጊዜያቶች ዐውድ ጥቅሶቹ ስለ ባቢሎን ምን ያስተምሩናል?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

መጽሐፍ ቅዱስ የሁለት ከተሞች ወግ ነው የሚል አባባል አለ--የኢየሩሳሌምና የባቢሎን፡፡ ኢየሩሳሌም የእግዚአብሔርን ከተማና እርሱ በመላው የመጽሐፍ ቅዱስ ገጾች ለሕዝቡ የገባውን ኪዳን ስትወክል (መዝ. 102፡21፣ ኢሳ. 52፡9፣ 65፡19፣ ራእ. 3፡12) ባቢሎን ደግሞ--ጭቆና፣ ሁከት፣ የሐሰት ኃይማኖት እና በእግዚአብሔር ላይ የሚደረግን አመጻ ትወክላለች፡፡

ለምሳሌ ስለ ባቤል ግንብ ያስቡ (ዘፍ. 11፡9)፡፡ “ባቤል” የተሰኘው የዕብራይስጥ ቃል “ባቢሎን” ከተሰኘው ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ጴጥሮስ “ባቢሎን” ካለችው ቤተ ክርስቲያን ሰላምታ መላኩ በ1ጴጥ. 5፡13 ተጠቅሶአል፡፡ ይህ ማለት የዛሬዋ ኢራቅ ከምትገኝበት የጥንቷ ባቢሎን ፍርስራሽ ሳይሆን ብዙም ሳይቆይ የቤተ ክርስቲያን ጨቋኝ ከምትሆነው ከራሷ ከሮም ነው፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 14፡8፣ 18፡3፡፡ ባቢሎን በዓለምና በእግዚአብሔር ሕዝቦች ላይ ስላላት ክፉ ተጽእኖ ምን ይገልጻሉ?**

---

---

በራእይ መጽሐፍ እንደ ተገለጠው ባቢሎንን የሚወክለው ኃይል ክፉኛ መበላሸቱና ይኸው ብልሹ ተጽእኖ ወይም እርከስና በተለያየ መጠንና ደረጃ በመላው ዓለም መሰራጨቱ አያጠያይቅም፡፡ “የዝሙቷን ቁጣ ወይን ጠጅ” (ራእ. 14፡8) የሚለው ሀረግ ሐሰተኛ ኃይማኖታዊ አስተምህሮን፣ የረከሰ መንፈሳዊ ሥርዓትንና እነዚህን ተከትሎ የሚመጣውን የመጨረሻ ውጤት የሚያሳይ ግልጽ ማስረጃ ነው፡፡ ባቢሎን ወደ “ሕዝቦች ሁሉ” (ራእ. 18፡3) ለተሰራጨው የክፉው ኃይል ጉልበት ናት፡፡ ስለዚህ እያንዳንዱ ሰው ከዚህ እርከስና ለመጠበቅ ትኩረት ሊያደርግ ይገባል፡፡

**ብልሹ አሠራር፣ የተመሳቀለ ሁኔታና ጭቆና ወደ ሰፈነባት የዛሬዋ ዓለም ለመመልከት ይሞክሩ፡፡ በየሱስ እና በቃሉ መልሕቅ መጠበቅ እንደሚያስፈልገን አስመልክቶ ይህ ምን ሊያስተምረን ይገባል?**

## ሰኞ ሰኔ 11

## ባቢሎን ወደቀች

ባቢሎን በዓለም ዙሪያ ያላት ብልሹ ተጽእኖ የቱንም ያህል ግዙፍ ቢሆንም ነገር ግን አንድ ቀን እንደሚያበቃላት የራእይ መጽሐፍ ይናገራል፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 18፡1-10፡፡ ስለ “ታላቂቱ ባቢሎን” ምን ይነግሩናል?**

---

---

በባቢሎን ውድቀት ዙሪያ የተነገረው የሁለተኛው መልአክ (ራእ. 14፥8) መልእክት በድጋሚ በራእ. 18፥2 ቀርቦአል፡፡ ይህ ደግሞ ይህ አካል ምን ያህል ብልሹ ሁናቴ ውስጥ እንደ ገባ ያሳያል፡፡

"ጌታ ዳግም ከመገለጡ አስቀድሞ ሰይጣን 'በሐሰተኛ ታምራት በምልክቶችና በድንቅ ነገሮች ሁሉ' ይሠራል፡፡ 'እንዲሁም ይድኑ ዘንድ እውነትን ባለ መውደድ የሚጠፉትን ሰዎች በሚያታልል በተለያየ የክፋት ሥራ ይመጣል፡፡ በዚህም ምክንያት 'በሐሰት እንዲያምኑ' ለስሕተት አሠራር ይተዋሉ፡፡ (2ተሰ. 2፥9-11)፡፡ ይህ ሁናቴ ከንውን ሳያገኝና ቤተ ክርስቲያን ከዓለም ጋር ያላት ሕብረት በመላው የክርስትና ተቋማት ገቢራዊ ሳይሆን የባቢሎን ውድቀት የተሟላ አይሆንም፡፡ ለውጡ እየጨመረ የሚሄድ ዓይነት እንደ መሆኑ፤ ራእ. 14፥8 ፍጹም ክንዋኔ የሚያገኘው ገና ወደፊት ነው፡፡"—Ellen G. White, *The Great Controversy*, pp. 389, 390.

የተጠቀሰው "ፍጹም ክንዋኔ" አሁን ደርሶ ይሁን ወይም አይሁን የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ እኛ የምናውቀው ነገር ቢኖር በእነዚህ ጥቅሶች መሰረት መንፈሳዊቷ ባቢሎን ለታላቁ ክፋቷ አንድ ቀን የእግዚአብሔርን ፍርድ የምትቀበል መሆኑን ነው፡፡ "ኃጢአቷ እስከ ሰማይ ድረስ ተከምሮአልና፤ እግዚአብሔርም ዐመጻዋን አስታውሶአል" (ራእ. 18፥5)፡፡ እንደ ሌሎቹ ሁሉ ይሄኛውም አገላለጽ ብሉይ ኪዳን በጥንታዊቷ ባቢሎን ዙሪያ ጥቅም ላይ ያዋለውን አገላለጽ በማንጸባረቅ (ኤር. 51፥9) የፍርድ ጊዜን አይቀሬነት እንደምታ ያሳያል፡፡

ሊመጣ ያለው ፍርድ ሊያስገርመን አይገባም፡፡ ደግሞስ የጥንቷ ባቢሎን ፍርድ ተቀብላ የለ--(ዳን. 5)? ባቢሎንን ጨምሮ ሁሉም ሰው ለሥራው ምላሽ መስጠት እንደሚኖርበት መጽሐፍ ቅዱስ በጣም ግልጽ አድርጎ ይናገራል፡፡ ሆኖም ክርስቲያኖች በዚያ የፍርድ ቀን ስለ እኛ የሚቆም አማላጅ እንዳለን

ማወቃችን እንዴት አጽናኝ ነው! (ዮሐ. 2፡1፤ ዳን. 7፡22)፡፡ ያለበለዚያ የዕኛም ዕጣ ፈንታ ከባቢሎን የተሻለ መሆን ባልቻለ ነበር፡፡

አሁን ቅጣት ያላገኙ የሚመስሉ አያሌ የፍትህ መጓደሎችና እርኩሰቶች--አንድ ቀን የመጨረሻውን ዋጋ ከእግዚአብሔር እንደሚያገኙ በተሰጠው ተስፋ መጽናናት የሚያገኙት እንዴት ነው?

## ማክሰኞ ሰኔ 12

## አርማጌዶን

ምንም እንኳ አያሌ ክርስቲያኖችን ጨምሮ ብዙዎች በራእይ መጽሐፍ ላይ ያላቸው ግንዛቤ አነስተኛ ቢሆንም ነገር ግን አንዲት ቃል በስፋት ትታወቃለች፡ አርማጌዶን (ራእ. 16፡16)፡፡ ቃሉ በመንፈሳዊው ብቻ ሳይሆን በዓለማዊውም ባህል ምድር በመጨረሻው ዕጣ ፈንታዋ የምታደርገውን መፍጨርጨር ለማሳየት ጥቅም ላይ ውሎአል፡፡ ሆሊውድ አርማጌዶን የሚል ስያሜ የሰጠውን ፊልም ሠርቶ ለተመልካች አቅርቦ ነበር፡፡ ፊልሙ ምድርን ሊያጠፋ ከሕዋው ውስጥ ስለ ተምዘገዘገ ሰማያዊ ግዑዝ አካል ይተርካል፡፡ ምድር ፍጻሜ ሊኖራት የመቻሉ ጽንሰ ሃሳብ በተወሰነ መልኩም ቢሆን በዓለማዊ ሰዎች አእምሮ ውስጥም አለ፡፡

ከራእይ መጽሐፍ ጋር ትውውቅ ያላቸው በጣም ብዙ ክርስቲያኖች አርማጌዶን የዓለም ታሪክ ፍጻሜ በተቃረበበት ወቅት የአሁኗ እስራኤል የጦር ሠራዊት በመካከለኛው ምስራቅ የሚያደርገው ውጊያ እንደሆነ ያምናሉ፡፡ አንደኛው አባባል ከእስያ የሚነሱ 200 ሚሊዮን የሚደርሱ ተዋጊዎች ሰሜን እስራኤልን ያጥለቀልቃሉ ሲል፤ ሌላኛው ደግሞ በዓለም የተለያዩ ክፍሎች የሚነሱ የፖለቲካና ወታደራዊ ግጭቶች የመጨረሻውን የአርማጌዶን ፍልሚያ የሚያደርጉት በሜጊዶን አካባቢ ነው ይላሉ፡፡

ሆኖም መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጠን ትዕይንት ከዚህ ሙሉ በሙሉ የተለየ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ አርማጌዶንን በአገራት መካከል እንደሚነሳ ውዝግብ ሳይሆን እንደ መጨረሻው የዩኒቨርስ አቀፍ ተቃርኖ ጡዘት ይስልልናል፡፡ ምንም እንኳ አያሌ ኤኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች የትዕይንቱ አካል ሆነው ብቅ ቢሉም፤ ፍልሚያው ኃይማኖታዊ እንጂ ኤኮኖሚያዊ ወይም ፖለቲካዊ አይደለም፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 16፡12-16፡፡ እነዚህን ጥቅሶች ብቻ መሰረት በማድረግ ስለ አርማጌዶን እንዴት መማር እንችላለን?**

---

---

በቅድሚያ ጥቅም ላይ የዋሉት ቃላት ምን ያህል ተምሳሌታዊ ባህሪ እንዳላቸው ልብ ይበሉ፡፡ ከዘንዶው አፍ የሚወጡ እንቁራሪት መሰል መንፈሶች፣ ከሐሰተኛው ነቢይ አፍ፣ ከአውሬው አፍ...፡፡ "የአጋንንት መናፍስት" (ራእ. 16፡14) ሁሉን ከሚችል አምላክ ጋር ለውጊያ እንደሚወጡ መወሳቱ፤ የታላቁን ተቃርኖ ትዕይንት ያሳየናል፡፡ በክርስቶስና በሰይጣን ኃይላት መካከል ያለው ዓለማቀፋዊ ውዝግብ--አርማጌዶን በየትኛውም ዓይነት መንገድ ቢሆን ግልጽ ሆኖ ይወጣል፡፡ ውጊያው ሜጊዶን አካባቢ የሚደረግ ተራ ውዝግብ አለመሆኑን ልብ ይሏል፡፡

**ጥቅሱን ያንብቡ፡ ራእ. 16፡15፡፡ በእነዚህ ትዕይንቶች መሃል የሱስ ስለ ዳግም ምጽአቱና በጽድቁ ስለ መሸፈናችን አስፈላጊነት የሚሰጠን የማበረታቻ ቃል በእጅጉ ማራኪ ነው፡፡ ይህ የምንገኝበትን ውጊያ መንፈሳዊ ተፈጥሮ ማስተዋል እንድንችል እንዴት ይረዳናል?**

## ረቡዕ ሰኔ 13

## አርማጌዶን እና የቀርሜሎስ ተራራ፡ ክፍል 1

ለመሆኑ ይህ የአርማጌዶን ታላቅ ጦርነት ምንድን ነው? በመጀመሪያ ከስያሜው ስንነሳ “የሜጊዶ ተራራ” ለማለት የተፈለገ ይመስላል፡፡ ሆኖም ባካባቢው ቀርሜሎስ ተራራ እንጂ ሜጊዶን በሚል ስያሜ የሚታወቅ ተራራ የለም፡፡ ስለዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሑራን የሜጊዶን ተራራ ለቀርሜሎስ ተራራ እንደ ማመሳከሪያ ይመለከቱታል፡፡

ይበልጥ ወደ ዋናው ሃሳብ ስንመጣ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች የኤልያስንና የበዓል ሐሰተኛ ነቢያትን የቀርሜሎስ ተራራ ታሪክ--በራእ. 13 ያለውን ትዕይንት እንደሚገልጥ ተምሳሌት አድርገው ይመለከቱታል፡፡

በትናንቱ ጥናታችን እንደተመለከትነው ራእ. 16፡13 ስለ ዘንዶው፣ ስለ አውሬው እና ሐሰተኛው ነቢይ የሚሰጠው ማስረጃ መልሶ ወደ ራእ. 13--ማለትም በዘጠነኛው ትምህርት ወደ ተመለከትነው አስመሳዩ ስላሴ ይወስደናል፡፡

ሁለተኛው አውሬ ከተፈጥሮ ውጪ የሆኑ ድርጊቶችን በመፈጸም “እሳት ከሰማይ ወደ ምድር እስኪያወርድ ድረስ ታላላቅ ምልክቶችን” (ራእ13፡13) ሲያደርግ፤ የራእ. 13 ክስተቶች በቁ. 13 እና 14 ወደ ከፍተኛ ደረጃ ይደርሳሉ፡፡ በዚህ ወቅት ክስተቶቹ በሰይጣንና በእግዚአብሔር ይኸውም እውነተኛውን አምላክ በሚያመልኩና “ለአውሬው ምስል” (ራእ. 13፡14) በሚሰግዱ መሃል ወደሚደረግ ቀጥተኛ ግጥሚያ ይሸጋገራሉ፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ 1ነገሥ. 18፡1-18፡፡ በራእይ መጽሐፍ እንደ ታየው--ታሪኩ በመጨረሻዎቹ ጊዜያቶች ይፋ የሚሆኑ አንዳንድ ክስተቶችን የሚያንጸባርቀው እንዴት ነው?**

---

የታላቁን ውዝግብ ትዕይንት በውልብታም ቢሆን ከብዙ አቅጣጫዎች በዚህ ስፍራ እንመለከታለን፡፡ ኤልያስ፡ *ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ሕግ በመተዉ የሐሰት አማልክትን እያመለከ ይገኛል*--በማለት ጉዳዩን ግልጽ አድርጎ ያቀርበዋል፡፡ ከፉው በዘመናት ራሱን ማለቂያ በሌላቸው ቅርጾችና መንገዶች ሲገልጽ ቢኖርም፤ ሁሌም ቢሆን ጉዳዩ ይኸው አይደል? "ሰማይንና ምድርን፣ ባሕርንና የውሃ ምንጮችን ለፈጠረው" (ራእ. 14፡7) እንሰግዳለን ወይም ሌላ የሆነ ነገር እናመልካለን፡፡ ከራእ. 13 እና በዚያ ከተገለጡ ትዕይንቶች አንጻር ስንመለከት ሰዎች ጌታን በማምለክ ፋንታ ለአውሬውና ለምስሉ ይሰግዳሉ፡፡ መሃል ሰፋሪ የሚባል ቡድን የለም፡፡ ማንኛውም ሰው በእግዚአብሔር ወይም በሰይጣን በኩል ይሰለፋል፡፡

## ሐሙስ ሰኔ 14

## አርማጌዶን እና የቀርሜሎስ ተራራ፡ ክፍል 2

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ 1ነገሥ. 18፡18-40፡፡ ምን ተከተሰተ? ታሪኩ ያለቀበት መንገድ ምን ይመስላል? በመጨረሻ ላይ ታላቁ ውዝግብ ከፍ ያለ ደረጃ ከሚደርስበትና ከግዙፉ ትዕይንት አኳያ--ወደ ፊት የሚሆነውን እንዴት ያንጸባርቃል?**

---

---

በቀርሜሎስ ተራራ ላይ የተደረገው ውጊያ የእግዚአብሔር ነቢይ በነበረው ኤልያስ እና በ450 የበኣል ካህናት መካከል ተካሄደ፡፡ (የክፉው ኃይል ምን ያህል ከበጎው ይልቅ በቁጥር የበዛ እንደሆነ ልብ ይሏል)፡፡ ትዕይንቱ ማንኛው እውነተኛ አምላክ እንደሆነ የሚያሳይ ነበር፡፡
ሰማይና ምድርን የፈጠረው እግዚአብሔር ወይስ ዓለምን ለማሳት የሚመኘውና (ራእ. 12፡9) "ዘንዶው" በሌላ መንገድ የተገለጠበት በኣል?

እሳት ከሰማይ ወርዶ ለመሥዋዕት ያቀረቡትን ወይፈን እንዲበላው የበኣል ነቢያት ጸሎት አደረጉ፡፡ ከጠዋት አንስተው ቀኑን ሙሉ ላደረጉት ልመና "'ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ ጩኹ እንጂ! ተኝቶም ከሆነ ቀስቅሱት'' (1ነገሥ. 18፡27) እያለ ኤልያስ አፌዘባቸው፡፡ ነቢያቱ በኃይለኛ ስሜት ውስጥ ተውጠው ከአካላቸው ደም እስኪፈስ ገላቸውን በሠይፍና በጩቤ ያቆስሉ ነበር፡፡ ሆኖም ሰውነታቸው በመዛሉና በመድከሙ ያለ አንዳች ውጤት አመሻሽ ላይ አቆሙ፡፡

የኤልያስ መሥዋዕት ሦስት ጊዜ ውሃ እንዲፈስበት በመደረጉ ውሃው ጉድጓዱን ሞላው፡፡ ኤልያስ ለእግዚአብሔር ቀለል ያለ ጸሎት አቀረበ፡፡ ከዚያም እሳት ወርዶ የመሥዋዕቱን እንጨት፣ ድንጋይና ዐፈር ጨምሮ ማንኛውንም ነገር በቅጽበት በላው፡፡ የእውነተኛው አምላክ ኃይል ከበኣል ጋር ሲነጻጸር እውነተኛና የማይሳሳት ሆኖ ተገኘ፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡና ከሐሰተኞቹ የበኣል ነቢያት ጋር ያስተያዩአቸው፡ ራእ. 16፡13፣ 19፡20-21፡፡ እዚህ ላይ ምን ይመለከታሉ?**

---

---

ምንም እንኳ ለጊዜው ስለ አርማጌዶን የምናውቃቸው ነገሮች ውሱን ሊሆኑ ቢችሉም ነገር ግን ውጤቱን እናውቃለን፡--በእግዚአብሔር ጠላቶች ላይ የሚደርሰውን ጥፋት እና የእግዚአብሔርንና የቅዱሳኑን እውነተኝነት፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ 1ቆሮ. 15፡1-2፡፡ ምንም እንኳ ጥቅሶቹ ከአርማጌዶን ዐውድ የተለዩ ቢሆኑም ጳውሎስ እየጠቆመ ያለው ነገር ምንድን ነው? በተለይ የወደፊቱ ከያዘው ብርሃን አኳያ ይህን ማስታወሳችን አግባብ የሆነው ለምንድን ነው? በተጨማሪ የአርማጌዶንን ዐውድ የያዘውን ራእ. 16፡15 ያንብቡ፡፡ ጥቅሶቹ በአንድነት ምን ይነግሩናል?**

## አርብ ሰኔ 15

**ተጨማሪ ሀሳብ፡** "ብዙ ጸሐፊዎች ስለ አርማጌዶን ውጊያ በጻፏቸው ታሪኮች አሰቃቂ ፍጡራንን እና አስቀያሚ ክስተቶችን ቢያካትቱም፤ ከእውነታው ጋር ቅርበት ያላቸው የሚመስሉ ሀሳቦች ሲያንጸረቁባቸው ይታያሉ፡፡ 'እነሆ፤ እንደ ሌባ እመጣለሁ፤ ዕራቁቱን እንዳይሆን ኀፍረቱም እንዳይታይ ነቅቶ ልብሱን የሚጠብቅ ሰው ብፁዕ ነው' (ራእ. 16፡15)--ይህ አርማጌዶን የሚለውን ቃል ከማግኘታችን አስቀድሞ የሚመጣ ጥቅስ፤ ለየሱስ ዳግም ምጽአት እና ለመጨረሻው ጊዜ ክስተቶች እንድንዘጋጅ የሚነግሩንን አያሌ የአዲስ ኪዳን መልእክቶች ያስተጋባል፡፡

"ሌላው በራእ. 17፡14 የምናገኘው ጥቅስ እንዲህ ይላል፡ 'እነዚህ በጉን ይዋጋሉ፤ በጉ ግን ድል ይነሳቸዋል፤ ምክንያቱም እርሱ የጌቶች ጌታና የነገሥታት ንጉሥ ነው፤ ከእርሱ ጋር ያሉ የተጠሩት፣ የተመረጡትና የታመኑትም አብረው ድል ይነሳሉ፡፡' እዚህ ላይ በመጨረሻ እውን በሚሆነው ታላቁ ጦርነት ተቀዳሚ ዓላማቸው ሌሎችን በመሣሪያ ማጥፋት ሳይሆን ለቀረበላቸው መለኮታዊው ጥሪና መመረጥ ታማኝ የሆኑ ተዋጊ ሕዝቦችን እናገኛለን፡፡ ይህ ዛሬም መንግሥታትና የነፃነት ተዋጊዎች እያደረጉ ካለው ውጊያ ጋር ሲነጻጸር በእጅጉ የተለየ ነው፡፡ በተደጋጋሚ እንደ ተናገርኩት የአርማጌዶን ውጊያ የአእምሮ ፍልሚያ ነው፡፡ በተጨማሪ ለታረደው በግ ከልብ የመነጨ ታማኝነት እንድናሳይ የቀረበ የልብ ተግዳሮት ነው፡፡ *(Rev. 5:9, 10, 12; 13:8)."—Jon Paulien, Armageddon at the Door (Hagerstown, Md.: Autumn House Publishing, a division of Review and Herald Publishing Association, 2008), p. 193.*

## የመወያያ ጥያቄዎች፡

1.በራእይ መጽሐፍ የተጠቀሱት አብዛኞቹ ክስተቶች በራሱ በተጠቀሰው ስፍራ ገቢራዊ ይሆናሉ ብሎ የሚያምነውን ሰው ሊረዱት የሚችሉት እንዴት ነው? ይህ ጥቅሶችን ለመፍታት አስቸጋሪ አካሄድ መሆኑን መመልከት እንዲችሉ እንዴት ልናግባባቸው እንችላለን?

2.የባቢሎን ተጽእኖ መላውን ዓለም ያካተተ መሆኑን ቀደም ባለው ትምህርታችን ተመልክተናል፡፡ አንዳንዶቹ የባቢሎን አስተምህሮዎች የትኞቹ ናቸው? እነዚህን አስተምህሮዎች ለይተን በመገንዘብ ማስወገድ የምንችለው እንዴት ነው?

3.በሰኞው ትምህርት የሚከተለው የኤለን ኋይት ጽሑፍ ቀርቦ ነበር፡ "ይህ ሁናቴ ክንውን ሳያገኝና ቤተ ክርስቲያን ከዓለም ጋር ያላት ሕብረት በመላው የክርስትና ተቋማት ገቢራዊ ሳይሆን የባቢሎን ውድቀት የተሟላ አይሆንም" እዚህ ላይ "ቤተ ክርስቲያን ከዓለም ጋር ያላት ሕብረት" ስለሚለው ሀረግ አሰብ ያድርጉ፡፡ ለመሆኑ ይህ የተሰጠን ብርቱ ማስጠንቀቂያ ምን ይመስላል?

# አስራ ሶስተኛ ትምህርት ከሰኔ 16 - 22

## የጌታችን የየሱስ ዳግም ምጽአት

### ሰንበት ከሰዓት

***ለዚህ ሳምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡*** *ኢሳ. 13:6፣ 9፣ ማቴ. 24:30-31፣ ዳን. 2:34-35፣ 2ጢሞቴ. 4:6–8፣ 2ተሰ. 1:7–10፡፡*

**የማስታወሻ ጥቅስ፡-**

**“መብረቅ ከምስራቅ ወጥቶ ምዕራብ ድረስ እንደሚያበራ፣ የሰው ልጅ አመጣጥም እንደዚሁ ይሆናል” (ማቴ. 24፡27)።**

ባለ ቅኔው ቲ.ኤስ. ኤሊዮት “መጀመሪያዬ መጨረሻዬ ነው” የሚል መስመር በአንድ ግጥማቸው ውስጥ፡ ይገኛል፡፡ ይህ ሀረግ እጥር ምጥን ቢልም ብርቱ እውነት ይዞአል፡፡ ጅማሮ ላይ ፍጻሜ አለ፡፡ ሁለት መሰረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮዎችን በያዘው ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት በሚለው መጠሪያ ስማችን ውስጥ ይህ ድምፅ ያስተጋባል፡፡ “ሰባተኛ ቀን” የሚሉት ቃላት የአስርቱ ትእዛዛት አካል የሆኑትን ስድስት ቀናት የፈጀውን የፍጥረት ሥራ ሲወክሉ፤ “አድቬንቲስት” ደግሞ የዘላለማዊው ህይወት ተስፋ ፍጻሜ ወደ ሆነው የየሱስ ዳግም ምጽአት ያመላክታል፡፡

ምድርና ሙላቷ የተፈጠሩበት ጊዜ (ጅማሮአችን) የቱንም ያህል ከየሱስ ዳግም ምጽአት የራቀ ሊሆን ቢችልም (የዚህ ኃጢአተኛ ህልውና መጨረሻ) ክስተቶቹ ግን የተሳሰሩ ናቸው፡፡ እኛን የፈጠረው ያው አምላክ (ዮሐ. 1፡1-3) ራሱ ዳግም ተመልሶ ሲመጣና “ድንገት በቅጽበተ ዐይን፤ መለከት ሲነፋ” (1ቆሮ. 15፡52) የመጨረሻው ደኅንነታችን እውን ይሆናል፡፡

በእርግጥም--በጅማሮአችን ውስጥ ፍጻሜአችን አለ፡፡

በዚህ ሣምንት ጥናታችን የሁሉም ክስተቶች መጨረሻ በሆነው የፍጻሜ ክስተት ይኸውም በጌታችን የሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ዙሪያ እንነጋገራለን፡፡

## እሁድ ሰኔ 17

## የጌታ ቀን

ብዙውን ጊዜ የየሱስን ዳግም ምጽአት የአዲስ ኪዳን አስተምህሮ ብቻ አድርጎ የማሰብ አዝማሚያ ቢታይብንም ነገር ግን ይህ ትክክል አይደለም፡፡ በእርግጥ ከየሱስ የመጀመሪያ ምጽአት፣ ከሞቱ፣ ከትንሣኤው እና ዕርገቱ በኋላ--በዳግም ምጽአቱ ዙሪያ ያለው እውነት በግልጽና በሙላት ተሰጥቶናል፡፡ ነገር ግን በአዲስ ኪዳን አብልጦ የተገለጸውን ያህል ብሉይ ኪዳንም ይህ ወሳኝ እውነት ገቢራዊ ከመሆኑ ረጅም ዓመታት አስቀድሞ ፍንጭ ይሰጠናል፤ ጥላውንም ያሳየናል፡፡ የየሱስን ዳግም ምጽአት አስመልክቶ የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች የገለጡት አዲስ እውነት አልነበረም፡፡ ይልቁንም አስቀድሞ በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጠውን እውነት አበለጸጉት፡፡ ሆኖም በተሰቀለውና ከሞት በተነሳው አዳኝ ብርሃን እነሆ ዛሬ የዳግም ምጽአቱ ተስፋ ይበልጥ መስተዋልና ከፍ ያለ አክብሮት ማግኘት ችሎአል፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ኢሳ. 13:6-9፣ ዘካ. 14:9፣ ዳን. 12:1፡፡ ስለ የሱስ ዳግም ምጽአት ምን ያስተምሩናል?

____________________________________________

____________________________________________

“የጌታ ቀን” ለጠፉት የውድመት፣ የሰቆቃና የሽብር ጊዜ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡ ሆኖም ስማቸው በመጽሐፉ ላይ ለተጻፈ (ፊልጵ. 4፡3፣ ራእ. 3፡5፣ 13፡8) የእግዚአብሔር ሕዝቦች ግን ታላቅ የመዳን ቀን ይሆንላቸዋል፡፡ ይህ በብሉይ ኪዳን “የጌታ ቀን” በሚል የቀረበ ርዕሰ ጉዳይ ለጠፉት የፍርድ ጊዜ-- ለእግዚአብሔር ታማኞች ግን አምላካዊውን ከለላ የሚያገኙበትና የተዘጋጀላቸውን ሽልማት የሚቀበሉበት ዕለት ነው፡፡ ለአብነት ያህል ምንም እንኳ አንዳንዶች “የእግዚአብሔርን የቁጣ ቀን” መጋፈጣቸው አይቀሬ ቢሆንም “ጽድቅንና ትሕትናን” የሚፈልጉ ግን “ከእግዚአብሔር የቁጣ ቀን የሚሰወሩ ይሆናሉ” (ሶፎ. 2፡1-3)፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ማቴ. 24፡30-31፡፡ በየሱስ ዳግም ምጽአት ወቅት በጠፉትና በዳኑት መካከል የሚኖረውን ሁለት ተቃራኒ ሁኔታ የሚያወዳድሩበት መንገድ ምን ይመስላል?**

የመጨረሻዎቹ ክስተቶች እየተገለጡ በሄዱ ቁጥር የቆምንበት ጎራ ይበልጥ ግልጽ እየሆነ ይመጣል፡፡ በትክክለኛው በኩል ለመቆማችን እርግጠኞች መሆን እንችል ዘንድ አሁን ምርጫችን ምን መሆን ይኖርበታል?

## ሰኞ ሰኔ 18

## ዳንኤል እና የየሱስ ዳግም ምጽአት

ምንም እንኳ በመሲህነት ይጠበቅ የነበረው የሱስ በወቅቱ የነበረውን የሮማውያን ቅኝ ግዛት አፈራርሶ እስራኤልን እጅግ ኃያል አገር አድርጎ ይመሰርታል ብለው አይሁዳውያን ቢጠብቁም፤ ነገር ግን የእርሱ የመጀመሪያም ሆነ ሁለተኛው ምጽአት ያረጀውን ኃጢአተኛና የወደቀ ዓለም ለመጠገን አልነበረም፣ አይደለምም! እግዚአብሔር ለታማኝ ሕዝቦቹ ያዘጋጀው ከዚህ እጅግ የላቀና የከበረ ነገር አለው፡፡

ከብሉይ ኪዳን መልእክቶች ሁሉ አዲሷ ምድር ከአሮጌዋ ላይ አድጋ የምትወጣ ሳይሆን አዲስ እና አፈጣጠሯ ላይ መሰረታዊ ለውጥ ያላት የመሆኗን እውነታ የዳን. 2ን ያህል በግልጽ የሚያሳየን የለም፡፡

ዳን. 2 ወደ ዛሬዎቹ ዘመናዊ የአውሮፓ አገራት የሚሰነጣጠቁትን አራቱን የዓለም ታላላቅ መንግሥታት--ባቢሎን፣ ሜዶንና ፋርስ፣ ግሪክ እና ሮም አነሳስና አወዳደቅ ያሳየናል፡፡ ናቡከደነፆር በሕልሙ የተመለከተው ምስል (የአራቱ የዓለም ልዕለ ኃያላን አነሳስ ተምሳሌት) የመጨረሻ ክፍል ወደ አስደናቂ ልዩነት ያመራና በመጨረሻም በየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ፍጻሜ ያገኛል፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ዳን. 2፡34-35፣ 44-45፡፡ ስለዚህ ዓለም ዕጣ ፈንታና ስለ አዲሱ ተፈጥሮ ምን ያስተምሩናል?**

________________________________________________

________________________________________________

________________________________________________

ጥቅሶቹ የየሱስ ዳግም ምጽአት ዕውን በሚሆንበት ወቅት ስለሚሆነው ነገር የሚያቀርቡት ሀሳብ በመጠኑም ቢሆን አሻሚነት አለው፡፡ የሱስ በሉቃ. 20፡ 17-18 መልእክቱ ራሱን ሁሉንም በሚያደቅቀው የማእዘን ራስ ድንጋይ በመመሰል ሲናገር ይደመጣል፡፡ በዳን. 2፡35 እንደምናነበው የወርቁ ምስል፣ ብሩ፣ ሸክላው፣ ብረቱ እና ነሐሱ "ተሰባበሩ፤ በበጋ ወራት በዐውድማ ላይ እንደሚገኝ እብቅም ሆኑ፤ ነፋስም አንዳች ሳያስቀር ጠራረጋቸው" ከየሱስ ዳግም ምጽአት በኋላ በዚህ ምድር የሚቀር አንዳችም ነገር አይኖርም፡፡

በዚህ ምድር የነበረውን አሻራ አንድም ሳይቀር "የመታው ድንጋይ ግን ታላቅ ተራራ ሆነ፤ ምድርንም ሞላ፡፡" ይህ የዳግም ምጽአቱ ውጤት የሆነ መንግሥት "ፈጽሞ የማይፈርስና" "ለዘላለም ጸንቶ" የሚኖር ይሆናል (ዳን. 2፡44)፡፡

በዚህ ምድር የኖረ ማንኛውም ሰብዓዊ ፍጡር ከቀረቡለት ሁለት አማራጮች በአንዱ ላይ ብቻ ይወሰናል፡፡ ከየሱስ ጋር ለዘላለም መኖር ወይም ከአረጀውና ካፈጀው ምድር ጋር እንደ ዐውድማ እብቅ ተጠራርጎ መጥፋት፡፡ በዚህም ሆነ በዚያ--ዘላማዊነት እየጠበቀን ይገኛል፡፡

## ማክሰኞ ሰኔ 19

### ዘላቂውን ተስፋ ማድረግ

**ጥቅሱን ያንብቡ፡ ቲቶ 2፡13፡፡ እንዴት ያለ ታላቅ ተስፋ አለን? ለምን?**

____________________________________________________

____________________________________________________

የአንድ ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር ስለ ዩኒቨርስ አፈጣጠር የሚያምኑበትን መላ ምት ሲገልጹ ከ13 ቢሊዮን ዓመታት በፊት “አንድ ከምንም ነገር በተከሰተ ጥቃቅንና ጥቅጥቅ ግዑዝ አካል ላይ ከፍተኛ ፍንዳታ ደረሰ፡፡” ካሉ በኋላ “ታዲያ ከዚያ ፍንዳታ ውስጥ ይህ የእኛ ዩኒቨርስ ብቅ አለ፡፡” በማለት ንግግራቸውን ደመደሙ፡፡ ለመሆኑ ይህ “ጥቃቅን ጥቅጥቅ ግዑዝ አካል” እንዴት ከምንም ነገር ላይ ተነስቶ መከሰት ቻለ--በሚል ሊነሳ ለሚችለው ጥያቄ ያሉት ነገር ግን አልነበረም፡፡ ብቻ በዚህ መንገድ መሆን ቻለ ብለው ንድፈ ሀሳቡን አምነው ተቀብለውታል፡፡

በዚህ ሣምንት ጥናታችን በመግቢያ ላይ እንደ ተመለከትነው፡ በጅማሮአችን ውስጥ ፍጻሜአችን አለ፡፡ ሆኖም እንደ ፕሮፌሰሩ መላ ምት ከሆነ መጨረሻችን ተስፋ ቢስ ነው፡፡ ከዚህ “ጥቃቅን ጥቅጥቅ ግዑዝ አካል” የተፈጠረ አጽናፈ ሰማይ በስተመጨረሻ ሰብዓዊውን ፍጡር ጨምሮ እርሱና በውስጡ ያለው ሁሉ እንዲጠፋ ተፈርዶበታል፡፡

ሆኖም ከዚህ በተቃራኒ የሚገኘውን የጅማሮአችንን ጽንሰ ሃሳብ የሚያስነብበው መጽሐፍ ቅዱስ--አመክኖአዊ ብቻ ሳይሆን ተስፋ ሰጪም ነው፡፡ የጅማሮ ሁሉ ባለቤት ለሆነው እግዚአብሔር አምላክ ምስጋና ይግባውና የወደፊቱ ተስፋችን መልካም ነው፡፡ ስለ ወደፊት ተስፋ እንድናደርግ የሚረዱን አያሌ ምክንያቶች ያሉን ሲሆን--ይህ ተስፋችን በየሱስ ዳግም ምጽአት ላይ ያርፋል፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ 2ጢሞቴ. 4፡6-8፡፡ ጳውሎስ ስለ ምን እየተናገረ ነው? ተስፋውን እያኖረ ያለውስ በማን ላይ ነው?**

---

---

ምንም እንኳ ጳውሎስ የሚሰዋበት ጊዜ ቢቃረብም፤ ነገር ግን ህይወቱ መዳኑን ያረጋገጠና "በዚያ ቀን" ብሎ ለጠራው የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ተስፋ የሰነቀ ነበር (2ጢሞቴ. 4፡8)፡፡ ተስፋው በየሱስ ዳግም ምጽአት ላይ ማረፉን የሚያውቀው ጳውሎስ፤ የሚጠብቀው "የጽድቅ አክሊል" የራሱ ጽድቅ ሳይሆን (1ጢሞቴ. 1፡15) የየሱስ ጽድቅ መሆኑን ይረዳል፡፡ በቅርቡ ሊደርስበት ያለው አስከፊ ሁናቴ ያላስጨነቀው ጳውሎስ (እስራት እና መሠዋት) የመጨረሻ ተስፋው ብሩህ መሆኑን ያውቅ ነበር፡፡ ለዚህ መንስዔው እንደ ጥላ የሚያልፈውን ሳይሆን ግዙፉን ትዕይነት መመልከት መቻሉ ነበር፡፡

**እርስዎ አሁን ሊገኙ በሚችሉበት ሁናቴ ተስፋ ሳይቆርጡ፤ እንደ ጳውሎስ ተስፋ መሰነቅ የሚችሉት እንዴት ነው? ወደ ትልቁ ትዕይንት መመልከትና ትዕይንቱ የሚሰጠውን ተስፋ የግላችን ማድረግ መማር የምንችለው እንዴት ነው?**

## ረቡዕ ሰኔ 20

## በሰማይ ደመናዎች

ግም ምጽአቱ የቱንም ያህል የሁሉም ነገር ማዕከላዊና ወሳኝ ቢሆንም ሁሉም ክርስቲያኖች ግላዊውን የየሱስ ዳግም ምጽአት ቃል በቃል እንደ ተነገረው ክስተቱን እንደማይመለከቱ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል፡፡ ለምሳሌ አንዳንዶች-- የየሱስ ዳግም ምጽአት እውን የሚሆነው እርሱ ራሱ ወደ ምድር ሲመለስ ሳይሆን መንፈሱ በቤተ ክርስቲያኑ ሲገለጥ ነው በማለት ይሞግታሉ፡፡ በሌላ አነጋገር የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ፍጻሜ የሚያገኘው የክርስትና ግብረገባዊ መርኅዎች በሕዝቡ ሲገለጡ ነው--እንደ ማለት፡፡

ይህ አስተምህሮ ሐሰተኛ ሆኖ መቅረቱ በጀ እንጂ--እውነት ቢሆን ኖሮ ምን ዓይነት ዘላቂ ተስፋ ሊኖረን ይችል ነበር?

**ከዚህ በታች የቀረቡትን ስለ ዳግም ምጽአቱ የሚናገሩ የአዲስ ኪዳን ጥቅሶች ያንብቡ፡፡ ስለ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ተፈጥሮ ምን ይገልጣሉ?**

ማቴ. 24:30________________________________

1ተሰ. 4:16__________________________________

ማቴ. 26:64_______________________________

ራእ. 1:7____________________________________

2ተሰ. 1:7–10________________________________

“ሰማይ እንደ መከፈትና መዘጋት ይል ነበር፡፡ ከእግዚአብሔር ዙፋን የሚወጣው ክብር የሚያንጸባርቅ ይመስል ነበር፡፡ ተራሮች በነፋስ እንደሚወዛወዙ ረጃምም ቁጤማዎች ሆኑ፡፡ ዐለቶች በሁሉም የምድር አቅጣጫዎች ተበተኑ፡፡ በብርቱ የሚያጓራ የዐውሎ ነፋስ ድምፅ ተሰማ፡፡ ባሕሩም በቁጣ ተሞላ፡፡ የጥፋት ተልዕኮ ይዘው እንደሚተሙ የኢጋንንት ድምፀት ዓይነት የቁጣ ጩኸት ተስተጋባ፡፡

ምድር በውቂያኖስ ላይ እንደሚነሳ ብርቱ ሞገድ ዋለለች፡፡ የምድር ገጽ እየተሰባበረ መሰረቶቿ የሚሸሹ መሰሉ፡፡ የተራሮች ሰንሰለት ሰመጡ፡፡ ሰዎች ይኖሩባቸው የነበሩ ደሴቶችም ጠፉ፡፡ እንደ ሶዶም የእርክስና መዲና የነበሩ የባሕር ወደቦች በቁጡ ውሖች ተሰለቀጡ፡፡ ታላቂቷ ባቢሎን በእግዚአብሔር ፊት ታወሰች 'በብርቱ ቁጣው ወይን ጠጅ የተሞላውን ጽዋ ሰጣት' ”—*Ellen G. White, The Great Controversy, p. 637.*

የየሱስ ዳግም ምጽአት ይህችን የምናውቃትን ዓለም ወደ ፍጻሜ የሚያመጣ ግዙፍ ክስተት ነው፡፡ መሆን ሲጀምር ጉዳዩን ሁሉም ሰው ያውቃል፡፡ የሱስ በመጀመሪያ ምጽዓቱ ለእኛ ያደረገው ነገር ኋላ በዳግም ምጽአቱ ሙሉ ለሙሉ የሚታይ ይሆናል፡፡

**በዳግም ምጽአቱ ተጨባጭ ሁናቴ ውስጥ መኖር በዛሬው አኗኗራችን ላይ ተጽእኖ ሊኖረው የሚችለው እንዴት ነው? ለህይወት በትክክል አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን እንድናስታውስ እንዴት ሊረዳን ይችላል?**

## ሐሙስ ሰኔ 21

## በሕይወት ያሉትና ያንቀላፉት

የሱስ ወዳጁ አልዓዛርን ከመቃብር ከማስነሳቱ አስቀድሞ እነዚህን ቃላቶች ተናግሮ ነበር “ 'ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፤ በእኔ የሚያምን ቢሞት እንኳ በሕይወት ይኖራል' ” (ዮሐ. 11፡5)፡፡ የሱስ ይህን የተናገረውን ለማመን የሚያዳግት አስገራሚ ነገር ባለቤትነት ሕዝቡ እንዲቀበል ብቻ አልፈለገም፤ ይልቁንም ከሞተ የሰነበተውንና መሽተት የጀመረውን የአልዓዛር በድን ለማስነሳት ተንቀሳቀሰ (ዮሐ. 11፡39)፡፡

በየሱስ የሚያምኑ እርሱ ራሱ እንደተናገረው በእርግጥ ቢያንቀላፉም ነገር ግን በትንሣኤ ዳግም ይነሳሉ፡፡ የሙታን ትንሣኤ ማለት ከዚህ ውጪ ሌላ ፍቺ የለውም፡፡ የየሱስን ዳግም ምጽአት የተስፋችን ማዕከላዊ ክፍል የሚያደርገው ይኸው ነው፡፡

በመቀጠል በቀረቡት ጥቅሶች መሰረት በክርስቶስ ያንቀላፉ የሱስ ዳግም ሲገለጥ ምን ይሆናሉ? ሮሜ. 6:5፣ 1ተሰ. 4:16፣ 1ቆሮ. 15:42–44፣ 53–55፡፡

___________________________________________________

___________________________________________________

የሱስ ራሱ ከሞት በመነሳት የተለማመደው የታላቁ ዳግም ምጽአት ተስፋ-- በሁሉም የዕድሜ ክልል ሊገኙ የሚችሉ የእርሱ ታማኝ ተከታዮችም የሚለማመዱት እውነታ ነው፡፡ በእርሱ ትንሣኤ የየራሳቸው ተስፋና ማረጋገጫ አላቸው፡፡

**የሱስ ዳግም ሲገለጥ በሕይወት የሚገኙት ላይ ምን ይከሰታል? ፊልጵ. 3፡21፣ 1ተሰ. 4፡17፡፡**

___________________________________________________

___________________________________________________

የሱስ ዳግም ሲገለጥ በሕይወት የሚገኙት ታማኞች አዲስ አካል ይለብሳሉ፡፡ ከእንቅልፍ የተነሱት የለበሱት ዓይነት የማይበሰብስ አካል ይኖራቸዋል፡፡ “በሕይወት ያሉት ጻድቃን ‘በድንገት በቅጽበተ ዐይን’ ተለውጠዋል፡፡ በእግዚአብሔር ድምፅ ከብረዋል፡፡ አሁን ሕያው በመሆናቸው ከመቃብር ከተነሱ ቅዱሳን ጋር ጌታቸውን በአየር ለመገናኘት ይነጠቃሉ”—*Ellen G. White, The Great controversy, p. 645.*

**በዚህ ምድር ከዘላለማዊው ሕይወት አስበልጠው የሚያዩአቸውና አስፈላጊውን ሁሉ መሥዋዕትነት የሚከፍሉላቸው የከበሩ ነገሮች ካሉ ዘርዝረው ያስቀምጡ ለመሆኑ እነዚህ ነገሮች ምንድን ናቸው?**

## አርብ ሰኔ 22

***ተጨማሪ ሀሳብ፡*** የየሱስ ዳግም ምጽአት አሳዛኙ የሰብዓዊው ፍጡር የኃጢአትና ሥቃይ ታሪክ በዚህ ዓለም ስለሚቀጥልበት ሁናቴ ተጨማሪ መግለጫ የሚዘከርበት ትዕይንት አይደለም፡፡ በዚህ ፋንታ የክርስቲያኖች እምነት ታላቅ ተስፋ በከፍተኛ ደረጃ የሚገለጥበት ነው፡፡ የዳግም ምጽአቱ ተስፋ ባይኖር ኖሮ የሰብዓዊው ዘር ታሪክ በሞት እስኪ ደመደም--በብዙ ሥቃይና አስቸጋሪ ሁናቴ ውስጥ ከማለፍ በዘለለ ፋይዳ ቢስ ሆኖ በቀረ ነበር፡፡ ህይወት የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ከሚሰጠን ተስፋ የተነጠለ ሲሆን ዊልያም ሼክስፒር እንዳለው "በጩኸትና ንዴት የተሞላ ፋይዳ ቢስ የጅል ተረት ይሆናል፡፡" ሆኖም የእግዚአብሔር ቃል በተደጋጋሚ እንደሚያረጋግጥልን ይህ ተስፋ አለን፡፡ የሱስ ሕይወቱን ቤዛ አድርጎ በመስጠት (ማር. 10፡45) የዚህ ተስፋ ባለቤቶች እንዳደረገን ሁሉ--ለዚህ ዋጋ ለከፈለበት ብርቱ ጉዳይ ዳግም ይገለጣል፡፡ የሰማይ ከዋክብት ስለ ዳግም ምጽአቱ አይነግሩንም፡፡ ከአንዱ ዛፍ ወደ ሌላው እየበረሩ በማይሰለች ድምፃቸው የሚያዜሙ ዐዕዋፍም ይህን ታላቅ ዜና አያበስሩንም፡፡ ምንም እንኳ እነዚህ ነገሮች መልካም ወደሆነና ተስፋ ሊጣልበት ወደ ሚችል ተጨባጭ ነገር በራሳቸው ሊያመላክቱን ቢችሉም--አንድ ቀን የሱስ ሲገለጥ "መለከት ይነፋል፤ ሙታን የማይበሰብሱ ሆነው ይነሣሉ፤ እኛም እንለወጣለን" (1ቆሮ. 15፡5) ብለው አያስተምሩንም፡፡ " 'የሰው ልጅ በኀይሉ ቀኝ ሲቀመጥ፣ በሰማይ ደመናም ሲመጣ ታዩታላችሁ' " (ማር. 14:62) አይሉንም፡፡

ይልቁንም እነዚህን ነገሮች ማወቅ የቻልነው በእግዚአብሔር ቃል ስለተነገሩንና ቃሉ በሚሰጠን ተስፋ ላይ እምነት ስላለን ነው፡፡

## የመወያያ ጥያቄዎች:

1. አንዳንዶች የየሱስ ዳግም ምጽአት የክርስትና መርኀዎች በክርስቶስ ተከታዮች ዘንድ በሙላት መገለጥ ነው ብለው ያስባሉ፡፡ ዳግም ምጽአቱ እንዲህ እንደ ተባለው ቢሆን ኖሮ ምን ዓይነት ትርጉም ሊኖረው ይችል ነበር? አባባሉ መልካም ሊሆን ቢችልም ነገር ግን በስተ መጨረሻ ያለ ምንም ተስፋ ሊተወን የሚችለው እንዴት ነው?
2. በዘመናችን ዝነኛ የሆነው--ዩኒቨርስ ወይም አጽናፈ ሰማያት ከምንም ነገር መጣ የሚለው መላ ምት የጅል አስተሳሰብ ነው የምንለው ለምንድን ነው? ሰዎች እንዲህ ያለውን አስተሳሰብ የሚያራምዱት ለምንድን ነው? ተከታዮች የሚያፈሩበት ምክንያቱስ ምንድን ነው? አጽናፈ ሰማያትን አስመልክቶ ሁሉንም ነገር የፈጠረውን ዘላለማዊ አምላክ ማመን ይበልጥ አመክኖአዊና ምክኒያታዊ የሆነው ለምንድን ነው?
3. በሐሙስ ትምህርት መጨረሻ ላይ በዚህ ምድር ከዘላለማዊው ሕይወት አስበልጠው የሚያዩአቸውና አስፈላጊውን ሁሉ መሥዋዕትነት የሚከፍሉላቸው የከበሩ ነገሮች ካሉ ዘርዝረው ያስቀምጡ በሚል ለቀረበው ጥያቄ የጻፏቸው ነገሮች ይኖራሉ? ካሉ ተወያዩባቸው፡፡ ከሌሉ፤ ከደኅንነት ሊያግደን የሚችል አንዳችንም ነገር በህይወታችን ላለመኖሩ እንዴት እርግጠኞች መሆን እንችላለን?

## የትንቢት መንፈስ መጻሕፍትን ተርጉሞና አሳትሞ ማሰራጨት ለሚፈልጉ ግለሰቦችም ሆነ ድርጅቶች የተሠጠ

# ማሳሰቢያ

የትንቢት መንፈስ *(Spirit of Prophecy - SOP)* መጻሕፍት በሙሉ የሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት አለም አቀፍ ቤተክርስቲያን ንብረት ናቸው፡፡

እነዚህን ጽሁፎች በከፊልም ሆነ በሙሉ ወደ አማርኛም ሆነ ወደ ተለያዩ የአገሪቱ ቋንቋዎች በማስተርጎምና በማሳተም ለማዳረስ የሚፈልግ ግለስብም ሆነ ድርጅት፣ ሥራውን ከመጀመሩ በፊት ለኢትዮጵያ ዩኒየን ሚሽን የጽሁፍ ክፍል ጥያቄውን በጽሑፍ በማቅረብና በአካልም ቀርቦ በመወያየት ወደ ሰምምነት ከተደረሰ በኋላ ትርጉሙ፣ ህትመቱና ስርጭቱ በድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ተከናውኖ ሥራውን መፈፀም ይቻላል፡፡

በዚሁ መሠረት የትንቢት መንፈስ ጽሁፎችን በማሳተም ወንጌልን ለማዳረስ የሚጥሩ ግለሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች በእጅጉ ይበረታታሉ፡፡

ሆኖም ግን ይህንን በመተላለፍ ያለ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ዓለም አቀፍ ቤተ ክርስቲያን ፈቃድ በቤተክርስቲያኗ ስም የትንቢት መንፈስ ጽሁፎችን አሳትሞ ማሰራጨት፣ በአገሪቱም ሆነ በዓለም ዓቀፍ የሥነ ጽሁፍ ህግ ያስጠይቃል፡፡ በተጨማሪም ድርጅቱ እያስተረጎመ ያለውን መጽሐፍ ሌላ አካል ተመሳሳዩን መጽሐፍ በመተርጎም ላልተፈለገ የጊዜ፣ የጉልበትና የገንዘብ ወጪም ይዳርጋል፡፡

ሰለሆነም የቤተክርስቲያኗ ህግና መተዳደሪያ ደንብ በሚፈቅደው መሠረት ሁላችንም ጽሁፎችን በማሳተምም ሆነ በማሰራጨት የሶስቱን መላዕክት መልዕክት ለማዳረስ እንድንችል ጌታ ይርዳን፡፡

***ድርጅቱ***

# ዓለም አቀፍ አድቬንቲስት ሬዲዮ
# የተስፋ ድምፅ

## ትግርኛ

ጠዋት 12:00 - 12:30
**9530 Khz 31** ሜ.ባንድ
ማታ 1:30 - 2:00
**15130Khz 19** ሜ.ባንድ
አየር ሞገድ

አድራሻ
ስልክ **+251 115 511199**
የውስጥ መስመር **205**
ወይም
**+251 910 145105**

## አማርኛ

ጠዋት 12:30 - 1:00
**15500 Khz 19** ሜ.ባንድ
ማታ 2:00 - 2:30
**17570Khz 16** ሜ.ባንድ
አየር ሞገድ

አድራሻ
ስልክ **+251 115 511199**
የውስጥ መስመር **242**
ወይም
**+251 911 137222**

ፖ.ሳ.ቁ **145** አዲስ አበባ

## ኦሮምኛ

ጠዋት 12:00 - 12:30
**15500 Khz 19** ሜ.ባንድ
ማታ 2:30 - 3:00
**15155 Khz 19** ሜ.ባንድ አየር ሞገድ

አድራሻ
ስልክ **+251 115 511199**
የውስጥ መስመር **237**
ወይም **+251 921 600938**

የተላለፉ ፕሮግራሞችን እንደገና ለማዳመጥ ከመረጃ መረባችን www.awr.org ላይ በመግባት እንደገና ማግኘት ይችላሉ፡፡

**የዓለም አቀፍ አድቬንቲስት ሬዲዮ የ24 ሰዓት የአማርኛ ቋንቋ ስርጭትን በክርስቲያን ቻናል ጣቢያ ውስጥ ከዚህ በታች በተቀመጠው መሰረት ያገኙታል**

HC The Voice of Hope
Frequency: 12574
Symbol Rate: 09700
Polarity: Horizontal
Satellite: Intel Sat 68.5E
LNB: KU BAND

በተጨማሪም
በአሜሪካ ያሉ አድማጮቻችን 712 432 9970
በመደወል እንዲሁም
በእንግሊዝ ያሉ 033 001 03890 በመደወል
ፕሮግራሞቻችንን በማንኛውም ሰዓት
ማዳመጥ ይችላሉ

**የዓለም አቀፍ አድቬንቲስት ሬዲዮ የተስፋን ድምፅ ያዳምጡ ለወዳጆችዎ በማስተዋወቅና በመጋበዝ የበረከቱ ተካፋይ ይሁኑ**